አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር የኣሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ኣተገባበር ፍተሻ ፤ በመቀሌ ከተማ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (በተመረጡ ዘጠነኛ ክፍሎች ናሙናነት)

በ

ህልፍቲ ተካ

2004 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር የኣሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ኣተገባበር ፍተሻ ፤ በመቀሌ ከተማ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (በተመረጡ ዘጠነኛ ክፍሎች ናሙናነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ሥነ ልሣን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ


ህልፍቲ ተካ


2004 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ፍተሻ ፤ በመቀሌ ከተማ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (በተመረጡ ዘጠነኛ ክፍሎች ናሙናነት)**

በ

ህልፍቲ ተካ

2004 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም

[illegible] ______________________

ፊርማ ______________________

ፈታኝ ስም

[illegible] (R/C) ______________________

[illegible] ______________________

ፊርማ ______________________

______________________

# ምስጋና

በቅድሚያ በጉዞየ ሁሉ ከፊቴ በመቅደም ለዚህ እንድበቃ ለፈቀደልኝ ለልዑል እግዚአብሄር ክብር ምስጋና ይግባው። በመቀጠል የዚህን ጥናት ርእስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ ረቂቁን ፅሁፍ እስከ ማንበብ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከተሰጣቸው የስራ ሃላፊነት ጋር ያላቸውን የስራ መደራረብ ተቋቁመው በማስተካከል እና አስተያየት በመስጠት ጥናታዊ ፅሁፉን አሁን የያዘውን ቅርፅ እንዲያገኝ ላደረጉት መምህሬና አማካሪየ ዶ/ር ጌታሁን አማረ ላቅ ያለ ምስጋናየን ማቅረብ እወዳለሁ።

ለጥረቴ መሳካት የሞራል ማበረታቻ በመስጠት፣አስፈላጊ የሆነውን የሀሳብና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ፣የጥናቴን ረቂቅ በማንበብ፣የክፍል ውስጥ መከታተያ ቅፅ፣የፅሁፍና የቃል መጠይቅ ጥያቄዎችን በመገምገምና አስተያየት በመስጠት እገዛቸውን እስከ መጨረሻ ላልተለየኝ መምህሮቼ አቶ ጌታቸው እንዳላማው፣አቶ ሰይድ ይመር እና አቶ ተክለሀይማኖት ገብረፃድቅን ከልብ አመሰግናለሁ።

የጥናቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ መረጃውን በመስጠት ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝ የሐወልቲና ዓይደር ሁ/ደ/ት/ቤቶች ርእሰ መምህራን ፣አማርኛ ቋንቋ መምህራንና በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላቅ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት ለማካሄድ መረጃየን ስሰበስብ ቪድዮ በመቅረፅ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት እና የክፍል ውስጥ መከታተያ ቅፅ በመሙላት እገዛ ላደረጉልኝ ጓደኞቼ ሙሉ ገብረመድህን፣ሳራ ሳህለ፣ዛይድ ታደሰና ምልእተ ዘነበ እንዲሁም ቪድዮ ካሜራ ለሰጠኝ መምህር ደሳለኝ አስገዶም ከልብ የማይጠፋ ምስጋናየን ማቅረብ እወዳለሁ።

የቦታ ርቀት ሳይገባቸበው ወንድማዊ ፍቅራቸውን ያልተለየኝ ወንድሞቼ መብራህቱ ሀይለና ቢንያም ወ/አብ ባሉበት ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ከጎኔ በመሆን የሞራል ድጋፋቸውንና እህታዊ ምክራቸው ያልተለየኝ ጓደኞቼን ዓወት አሰፋ፣ለዘር አሌ እና ፅጌ አበራን ከልብ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ይህን ፅሁፍ በትዕግስት በኮምፒዩተር ፅፈው ለንባብ እንዲበቃ ላደረጉልኝ ወ/ሮ ወይንሸት አሸናፊ ምስጋናየን ይድረሳቸው።

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና---------------------------------------------------------------------------------------i
ማውጫ---------------------------------------------------------------------------------------ii
የሰንጠረዥ ማውጫ----------------------------------------------------------------------------vi
አጠቃሎ-------------------------------------------------------------------------------------vii

ምዕራፍ አንድ
መግቢያ
1.1 የጥናቱ ዳራ-----------------------------------------------------------------------------1
1.2 የጥናቱ ዓላማ---------------------------------------------------------------------------4
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ-------------------------------------------------------------------------4
1.4 የጥናቱ ገደብ----------------------------------------------------------------------------5
1.5 የምህፃረ ቃላትና የምልክቶች ፍቺ--------------------------------------------------------5
1.5.1 የምህፃረ ቃላት ፍቺ-------------------------------------------------------------------5
1.5.2 የምልክቶች ፍቺ----------------------------------------------------------------------5

ምዕራፍ ሁለት
ክለሳ ድርሳናት
2.1 የሰዋስው ምንነት-------------------------------------------------------------------------6
2.2 የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትና ማስተማሪያ ዘዴዎች ---------------------------9
2.3 የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ----------------------------------------------12
2.3.1 መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ----------------------------------------------13
2.3.2 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ--------------------------------------------------------14
2.3.2.1 የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ-----------------------------------------16
2.3.2.2 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራን እና የተማሪዎች ሚና----------17
2.3.2.3 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች----------19

ሀ. የመምህራንና የተማሪዎች ፍላጎት በቀላሉ መቀየር አለመቻል------------19
ለ. የመማሪያ ክፍል ሁኔታ----------------------------------------------------20
ሐ. የተማሪዎች ቁጥር----------------------------------------------------------21
መ. በቂ ጊዜ አለመኖር----------------------------------------------------------21
ሠ. የመማሪያ መፃህፍት (ሞጁል) አዘገጃጀት-------------------------------------22
ረ. የመምህራን ስልጠና ---------------------------------------------------------23
2.3.2.4 የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር---------------------------------------23
ሀ. የቡድን ውይይት----------------------------------------------------------------23
ለ. የግል ስራ ----------------------------------------------------------------------23
ሐ. የቡድን ስራ---------------------------------------------------------------------24
መ. የጥንድ ስራ--------------------------------------------------------------------25
ሠ. ጥያቄና መልስ-------------------------------------------------------------------25
2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት------------------------------------------------------26
ምዕራፍ ሶስት
የአጠናን ዘዴ
3.1 የጥናቱ ዘዴ--------------------------------------------------------------------31
3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች -----------------------------------------------------31
3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ-----------------------------------------------------32
3.3.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ-------------------------------------------32
3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ-----------------------------------------32
3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ---------------------------------------------32
3.3.4 የመምህንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ---------------------------------33
3.3.4.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ-------------------------------------------33
3.3.4.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ-------------------------------------------33
3.4 የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ-----------------------------------------------------34
3.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ------------------------------------------------------35
3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ-------------------------------------------------------------36
3.4.3 ቃለ መጠይቅ------------------------------------------------------------------36
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ---------------------------------------------------------37

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና

4.1 የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት----------38

4.2 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራን ሚና----------51

4.3 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎች ሚና----------66

4.4 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ----------78

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

5.1 ማጠቃለያ----------88

5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች----------91

ዋቢ ፅሁፎች----------94

የቁልፍ ቃላት ፍቺ----------99

አባሪዎች

አባሪ-1፡- የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅፅ----------100

አባሪ-2 ፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-1 ምድብ ‹‹G1››----------103

አባሪ-3፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-1 ምድብ ‹‹H1››----------105

አባሪ-4፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-2 ምድብ ‹‹E1››----------108

አባሪ-5፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-2 ምድብ ‹‹L1››----------110

አባሪ-6፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-3 ምድብ ‹‹A1››----------112

አባሪ-7፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-3 ምድብ ‹‹C1››----------114

አባሪ-8፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-4 ምድብ ‹‹K1››----------118

አባሪ-9፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-1 ምድብ ‹‹G2››----------119

አባሪ-10፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-1 ምድብ ‹‹H2››----------121

አባሪ-11፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-2 ምድብ ‹‹E2››----------123

አባሪ-12፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-2 ምድብ ‹‹L2››----------125

አባሪ-13፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-3 ምድብ ‹‹C2››----------126

አባሪ-14፡- የቪ.ድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-3 ምድብ ‹‹A2››----------128

አባሪ-15፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ መምህር-4 ምድብ ‹‹K2››------------------------------------130
አባሪ-16፡- ለተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ---------------------------------------------132
አባሪ-17፡- ከመምህር ‹‹ሀ›› ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ---------------135
አባሪ-18፡- ከመምህር ‹‹ለ›› ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ----------------140
አባሪ-19፡- ከመምህር ‹‹ሐ›› ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ---------------146
አባሪ-20፡- ከመምህር ‹‹መ›› ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ--------------151
አባሪ-21፡- የመምህራንና የተማሪዎች ተሳትፎ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ---------------------155

# የሰንጠረዥ ማውጫ


| ሰንጠረዥ | | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ከፆታና ብዛት አንፃር በተመለከተ----------------- | 34 |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ከክፍል ምልከታ የተገኘ ውጤት--------------------------- | 39 |
| 3 | መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለተማሪዎች ከቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት---------------------- | 44 |
| 4 | በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራን ሚና በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ ውጤት-------------------------------------------------------- | 52 |
| 5 | በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራንን ሚና በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት------------------------ | 60 |
| 6 | በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎችን ሚና በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ ውጤት------------------------------------------------ | 67 |
| 7 | በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎችን ሚና በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት------------------------ | 73 |
| 8 | በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎችን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት------------------------------------------------------------------------ | 81 |

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ሐወልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ መቀሌ ከተማ በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ሲመረጥ በከተማው ከሚገኙ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁለት እና ከሁለቱ ትምህት ቤቶች ደግሞ አራት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን በዕጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ከሚገቡባቸው የ9ኛ ክፍል ምድቦች በዕጣ ናሙና ሰባት ምድቦች ለክፍል ምልከታ ተወስደዋል፡፡ እንዲሁም ከሰባቱ ምድቦች በብድግ ብድግ ናሙና ዘዴ የተመረጡ 77 ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ መረጃ ሰጪዎችም በክፍል ውስጥ ምልከታ፣በቪድዮ ቀረፃ፣በፅሁፍና በቃል መጠይቅ፣ መረጃዎችን ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በተጠቀሱት መሳሪያዎች በመታገዝ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተጠናክረው ባስገኙት ውጤት መሰረት በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አዘውትረው ይጠቀማሉ፡፡ ይህም መምህራኑ የቡድን ውይይት፣ ጥያቄና መልስ እና የክፍል ስራ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተደጋጋሚ ይተገብራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራኑ በመማር ማስተማር ሂደት የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ፣ቅድመ ትምህርት ጥያቄዎችን በማቅረብ፣ተማሪዎችን በማበረታታት ወዘተ. ሚናቸው የተጫወቱ ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ሚናቸውን ተጫውተዋል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ዓላማ አለማስተዋወቅ፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል በስራው ላይ ያለውን ድርሻ አለማሳወቅ፣ የቡድን ውይይት የሚፈጀውን ጊዜ ቀድሞ አለማሳወቅ፣ የቡድን ውይይት በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መሰራት፣የማይሳተፉ ተማሪዎች እንዲሞክሩ አለማድረግ፣መምህራን ዘዴውን በተመለከተ ስልጠና አለመውሰድ፣የተማሪዎች ቁጥር መብዛት እና የመማሪያ ክፍሎች አቀማመጥ አመቺ አለመሆን የሚሉት ዘዴውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የሚንፀባረቁ ችግሮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቂ ጊዜና የመምህር መምሪያ አለመኖር ችግሮች እንዳሉ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በትምህርት ቤቶቹ አሁን ካለበት በተሻለ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የመፍትሄ ሀሳቦችን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓለማ ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም ወይም ዕውቀትና ክህሎት ተክኖ በቋንቋ መግባባት እንዲችል ማድረግ ነው (ትምህርት ሚኒስቴር 1990)። ይህም ዓላማ በሚገባ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የማስተማሪያ ዘዴን ምንነት በወጉ ማወቅና ውጤታማ ዘዴን መርጦ በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል። አንድ የቋንቋ መምህር አንድን የትምህርት ይዘት በክፍል ውስጥ ከማቅረቡ በፊት ለማስተማር ያዘጋጀውን ይዘት እንዴት ላስተምር የሚለውን ጥያቄ መጀመሪያ መመለስ አለበት (Kelly 1976)። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቋንቋን ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ዘመናት ተነድፈው ሲሰራባቸው ቆይቷል። እነዚህ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ጥንታዊ (Traditional) እና ዘመናዊ (Modern) ተብለው በሁለት ይከፈላሉ (Nunan 1988)።

ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚባለው መምህሩን ማዕከል ያደረገ እና የመማር ማስተማር ሂደቱ በመምህሩ የሚሽፈንበት፣ተማሪዎች ፍዝ ተቀባዮች (Passive Reciptents) ወይም አድማጭ የሚሆኑበት ዘዴ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በመማር ማስተማር ዘዴውም ሆነ የቋንቋ ትምህርቱን በተመለከተ የእውቀት ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደው፣ ውሳኔውን የሚወስነው እና ሀላፊነቱን የሚወስደው መምህሩ ብቻ ነው (Tudor 1993)። በመሆኑም ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች የህይወት ልምዳቸውን ተጠቅመው ለትምህርት በቀረበው ርዕስ ላይ በስፋትና በጥልቀት እንዲወያዩ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲጠይቁ እና ሀሳብ እንዲሰጡ ብዙም እድል አይሰጥም (Plass 1998, Temesgen 2002, ICDR 1999)። እንዲሁም አቀራረቡ ውጤት ተኮር አካሄድን የሚከተል በመሆኑ የተማሪዎች መማር የሚለካው ተማሪዎች ከአንድ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ለመሻገር የሚቀርብላቸውን ፈተና ሲሰሩ በሚያገኙት ውጤት ብቻ ነው (Plass 1998)።

በአጠቃላይ በጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች መምህሩ የሚላቸውን ማዳመጥ እና መፃፍ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ባለፈ በመማር ማስተማሩ ሂደት እርስ በርስ መስተጋብር በመፍጠር እንዲማማሩ መንገድ የሚከፍት አይደለም። በዚህም ምክንያት ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማር ይልቅ ማስተማር ጎልቶ የሚታይበትና ተማሪዎች ፍዝ ተቀባዮች ስለሚሆኑ የመማር ማስተማር ሂደቱ ስልቹ የሚሆንበት ነው።

ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚባለው ደግሞ መምህሩ ተማሪዎችን በማነሳሳት እና አቅጣጫ በማሳየት እንደ ፍንጭ ሰጪ ወይም መንገድ ከፋች በመሆን የመማር ማስተማር ሂደቱን በብዛት ተማሪዎች የሚሸፍኑት እና ንቁ ተሳታፊ (Active Participent) የሚሆኑበት ዘዴ ነው (Nunan 1988)።

በመሆኑም ተማሪዎች የሚገጥማቸውን ችግር ማለፍ የሚችሉበት እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ከትምህርት ቤት ማግኘት እንዲችሉ በመማር ማስተማር ሂደቱ ወቅት ከመምህራን የጎላ ተሳትፎ እና ውሳኔ ይልቅ የተማሪዎችን የነቃ ተሳትፎ ይጠይቃል (Silberman 1996)። ስለዚህ የተማሪዎችን ሁለንተናዊ (የዕውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት) ብቃት ለማዳበር ሂደቱ በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የተገነባ መሆን አለበት። የነቃ ተሳትፎ ለማድረግ ደግሞ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት ከፍ ማለት ወሳኝ ሲሆን ይህን ዓይነቱን ተነሳሽነት ለመፍጠር በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰውና ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ የሆነው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ነው (Plass 1998)። በዚህም ምክንያት ትምህርት ሚኒስቴር ከ 1986 ዓመተ ምህረት ወዲህ በሚሰጠው ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ለውጥ በማድረግ ዘመናዊ (አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ) ተግባራዊ እንዲደረግ ፖሊሲ አውጥቷል (ትምህርት ሚኒስቴር 1986)።

ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው ፖሊሲ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ተቋማት ያለውን የትምህርት አሰጣጥ የሚመለከት ነው። አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ትምህርትና በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የማስተማሪያ ዘዴ ነው። ምክንያቱም ይህ የማስተማሪያ ዘዴ በመማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩበት ማለትም በሚቀርበው የትምህርት ይዘት የመወያየት፣የመከራከር፣

የመጠየቅ እና የመመለስ በአጠቃላይ ሀሳባቸውን እየተለዋወጡ በጋራ የሚሰሩበትን ዕድል የሚያገኙበት ከመሆኑ የተነሳ የቋንቋ እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል (Plass 1998)፡፡ የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ዋና ዓላማ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ማሳተፍ ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን አስተሳሰብ አድማስ ማስፋት እና ለሚማሩት ነገር ሀላፊነትን በራሳቸው መሸከም እንዲችሉ ማስቻል ነው (MOE 1994)፡፡

ስለዚህ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ተማሪዎች ሃላፊነት በመውሰድ የሚሰሩበት ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን የእውቀት አድማስ ለማስፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተሰጡት ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ መምህሩ ተማሪዎችን በማነሳሳት እና ስለሚሰሩት ነገር አቅጣጫ በማሳየት፣ተማሪዎች ደግሞ በመወያየት፣በመመራመር፣በመጠየቅ እና ሀሳብ በመስጠት እየተሳተፉ የራሳቸውን ሚና በመጫወት በራሳቸው የመማር ዕድል የሚያገኙበት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚል ፖሊሲ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ዘዴው ፖሊሲው በሚፈቅደው መሰረት ማለትም ተማሪዎች እንዲወያዩ፣ እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱ፣ እንዲመራመሩና ሀሳብ እንዲሰጡ ወዘተ. በአጠቃላይ የተማሪዎችን ተሳትፎ ማዕከል በማድረግ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ አተገባበሩን በተመለከተ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ከዚህ ቀደምት እነ ሙሉጌታ፣ኤልያስ፣ደረጀና ዑመር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርን በተመለከተ በተለያዩ ኮሌጆች ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ውጤትም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በኮሌጅ ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፤ነገር ግን አተገባበሩ ላይ ችግሮች ይታያሉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ትምህርት ሚኒስቴር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚል ፖሊሲ ያወጣው ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ተቋማት ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከአሁን ድረስ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር አስመልክቶ የተደረገ ጥናት እና የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር ብቻ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር አስመልክቶ የተደረገ ጥናት ለዚህ ጥናት አቅራቢ

አላጋጠማትም፡፡ ስለዚህ አጥኚዋ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አተገባበሩ ቢፈተሽ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብላ በማመንዋ በመቀሌ ከተማ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሐወልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን እንዴት እየተገበሩት እንደሚገኙ ለመፈተሽ ተነሳስታለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሐወልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን እንዴት እንደሚተገብሩት መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አጠቃላይ ዓላማ መሰረት አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል ይጠቀሙበታል?
2. በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና ምንድን ነው?
3. ዘዴውን በመተግበር ሂደት የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ቀጥለው የቀረቡትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

1. መምህራኑ ፖሊሲው በሚፈቅደው መሰረት ዘዴውን እየተገበሩት ካልሆኑ በምን መልክ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው በመጠቆም የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
2. ዘዴውን በመተግበር ሂደት የታዩትን ችግሮች በመለየት የሚመለከተው አካል ማሻሻያ እንዲፈልግ የመፍትሄ ሀሳብ ይጠቁማል፡፡
3. በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ሰዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ በ2004 ዓ.ም. በማስተማር ላይ ከሚገኙ አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሐወልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ አጥኚዋ ካላት አቅም፣ ጊዜ እና ወጪ አንፃር ሁሉንም በጥናቱ ማካተት ከባድ በመሆኑ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ አትኩራለች፡፡ በናሙናነት የተወሰዱት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የሚማሩባቸው ሲሆኑ በዚህ ጥናት የተካተቱት ግን የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና አማርኛ ቋንቋ መምህራን ብቻ ናቸው፡፡ ጥናቱ በነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን እንዴት እንደሚተገብሩት መፈተሽ ላይ የተገደበ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማታው ፕሮግራም የሚያስተምሩ መምህራንና የሚያስተምሩዋቸው ተማሪዎች አያካትትም፡፡ እንዲሁም ይህ ጥናት የቋንቋ ክሂሎችን (መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መፃፍ) እና ስነ ፅሁፍ ፣ የክፍል ደረጃው መማሪያ መፅሀፍ ፣ መርሀ ትምህርት፣ የመምህር መምሪያ እና ሌሎች መማሪያ መሳሪያዎች አይፈትሽም፡፡

## 1.5 የምፃረ ቃላትና የምልክቶች ፍቺ

### 1.5.1 የምፃረ ቃላት ፍቺ

ሐ/ሁ/ደ/ት/ቤት- ሐወልቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ዓ/ሁ/ደ/ት/ቤት- ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

### 1.5.2 የምልክቶች ፍቺ

* ምልክቱ ያላቸው ቃላት ትርጉማቸው በፋት ኖት የተቀመጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡

… ነጠብጣቡ ሆን ተብሎ የቀረ ዓረፍተ ነገር/ የንግግር አካል እንዳለ ይጠቁማል፡፡

“ ” የሰዎች ንግግር መሆኑን ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ የሰዋስው ምንነትን እና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ያሰፈሩዋቸው ብያኔዎችና ተያያዥ ጉዳዮች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው አገርኛ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡

## 2.1 የሰዋስው ምንነት

የሰዋስው ምንነትን አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡ ይታያሉ፡፡ ከነዚህ ብያኔዎች የሚከተሉትን ወስደን ማየት እንችላለን፡፡

“ሰዋስው የቃላትን ህብረትና አገባብ የሚያስተምር ክፍል ነው” Lyons (1968□4)፡፡ እንዲሁም Ur (1988፡5) “ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ እንደ ቃላት እና ሀረጋት የመሳሰሉት የስነ ልሳን አሀዶች ተቀናጅተው አረፍተ ነገር የሚመሰርቱበትን ዘዴ የሚገልፅ ነው” በማለት ገልፀዋል፡፡ በነዚህ ብያኔዎች መሰረት ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላትና ሀረጋት ቋንቋው በሚፈቅደው ስርዓት ተቀናጅተው ዓረፍተ ነገር የሚመሰርቱበትን ክፍል የሚመለከት መሆኑን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

“ሰዋስው የአንድን ቁዋንቁዋ ስርዓት ከድምፅ አሰካኩ እስከ ሀረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው”(ባየ 1987፡8)፡፡ ይህ ብያኔ “በሊዮንስና በኧር” የተገለፁትን ሀሳቦች እንዳሉ በመውሰድ የአንድ ቋንቋ መሰረት ድምፆች በመሆናቸው ሰዋስው ድምፆች ተቀናጅተው ቃላት የሚመሰሩትበትን ስርዓት የሚጨምር መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከተሰጡት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው ዓረፍተ ነገርን ለመፍጠር የቋንቋው መሰረት ከሆኑት ድምፆች እስከ ሀረግ ያሉት ተዋቃሪዎች በትክክል የመቀናጀታቸውን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ሰዋስው የቋንቋን ስርዓት ማጥናትን የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ሰዋስው ገና በህፃንነታችን ቋንቋን ለመልመድ ከምንታገልበት እድሜያችን ጀምሮ አብሮን የሚኖር እውቀትና ረቂቅ ክስተት ነው (Carter 1990)፡፡ ይህ ብያኔ ደግሞ ሰዋስው ሰዎች በቋንቋ ለመግባባት ከጀመሩበት ወቅት ጀምሮ እስከሚያድጉ ከሰዎች ዕድሜ ጋር አብሮ የሚያድግ መሆኑን ያስረዳል፡፡

የተጠቀሱትን የሰዋስው ብያኔዎች መሰረት በማድረግ ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት እና ዕውቀት በማለት በሁለት አሻሚ መንገዶች መክፈል ይቻላል፡፡ አሻሚነቱን በተመለከተ ጌታሁን (1990፡ IV) እንደሚከተለው ይላሉ፡፡

> *...በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለውን ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ‹‹እውቀት›› የሚጠቁምና በሰው ልጅ አእምሮ ያለውን ችሎታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሰዋስው አእምራዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋ ስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለፃ የሚጠቁመው ነው፡፡ ይህ ፍቺ የአንድን ቋንቋ ስርዓት ጥናት የሚመለከት ስለሆነ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው፡፡*

ምሁሩ ከሰጡት ብያኔ መገንዘብ እንደሚቻለው ሰዋስው የሚለውን ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎች መያዙ ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ የመጀመሪያው የሰው ልጅ ስለሚግባባበት ቋንቋ እውቀት መኖሩንና ይህ የቋንቋ እውቀትም በተፈጥሮ ያገኘው ችሎታ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህም ሰዋስው አእምራዊ እሳቤ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የሰው ልጅ ስለሚጠቀምበት የቋንቋ ስርዓት (የድምፆች፣የቃላት፣የሀረጋትና የአረፍተነገር) አወቃቀር፣ አደረጃጀት የሚመለከት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ብያኔዎች መሰረት ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ተዋቃሪዎች የቋንቋውን ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት ማቀናጀትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ሀሳብን በተሟላ ሁኔታ በቋንቋ በመግለፅ መግባባት የሚቻለው የአንድ ቋንቋ ተዋቃሪዎች በዘፈቀደ በመጠቀም ሳይሆን ስርዓት ባለው መንገድ በማደራጀት እና ትርጉም የሚሰጥ መዋቅር በመፍጠር ነው፡፡ በሌላ አቅጣጫ ሰዋስው

ሰዎች ቋንቋውን ለመልመድ የሚያስችል ተፈጥራዊ ስጦታ ይዘው እንደሚወለዱና አብሯቸው የሚዘልቅ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህም ሰዋስውን ለመበየን ሁለት እሳቤዎች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ ለዚህ ጥናት "ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርዓት ጥናት የሚመለከት ነው" የሚለውን ብያኔ እንጠቀማለን፡፡

ሰዋስው የሚለው ቃል በጣም ሰፊና በስሩ የተለያዩ ንኡሳን ዘርፎች የሚያቅፍ ሲሆን ከነዚህ የሰዋስው ዘርፎች ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ የሰዋስው ዘርፍ በመደበኛው ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያለው ነው፡፡

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ሂደት ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚያግዝ፣የታላሚውን ቋንቋ አጠቃቀም የሚመለከት፣ለአፍ መፍቻም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችና መምህራን የሚያገለግል የሰዋስው ዘርፍ ነው (Littlewood 1981)፡፡

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው በተግባቦት ወቅት ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ቋንቋን እንዴት መጠቀም እንደሚቻልና የቋንቋን ሰዋስው ትምህርት ዓላማ ማሳካትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች ቋንቋን እንዴት መማር እንዳለባቸው ለመገመት፣ በሚሰጡት ገለፃ ላይ ስነልሳናዊ አጠቃቀማቸው ለመከታተል እና በተግባቦት ወቅት ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ቋንቋ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለመጠቆም ይረዳል፡፡ ስለዚህ የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ዋና ትኩረት ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ስርዓቱን ጠብቀው እንዲናገሩና እንዲፅፉ ማድረግ ነው http://en.wikipedia.org/wiki/Pedagogical_grammar፡፡

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው የሚሰጠው ተማሪዎች ስለ ቋንቋ ስርዓት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተብሎ ሲሆን ይህም ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ይረዳል፡፡ ምክንያቱም የአንድ ቋንቋ አፍ ፈት ሰው ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ንግግር ሊያደርግ ይችላል፡፡ ነገር ግን ኢ-አፍ ፈት የሆነ ተናጋሪ ቃላትን አቀናጅቶ ዓረፍተ ነገር ለመመስረትም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ የተወሰነ ዕውቀት ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህም ስነ ትምህርታዊ ሰዋሰውን ማስተማር አስፈልጓል http://www.wisegeek.com/what-is-a-pedagogical-grammar.htm፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች የቋንቋን ስርዓት በትክክል መጠቀም የሚችሉበትንና የቋንቋውን ስርዓት ጠብቀው ተግባቦት የሚፈፅሙበትን መንገድ የሚመለከት ነው፡፡ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አብዛኛውን ጊዜ ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግል ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የአንድ ቋንቋ አፍ ፈት ተናጋሪዎች ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ቋንቋ እንዴት እንደሚጠቀሙ የሚረዱበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ የሰዋስው ዘርፍ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት የሚማሩበትን ዕድል በመፍጠር ትክክለኛና ግልፅነት ያለው ተግባቦት የሚያደርጉበትን መንገድ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ተማሪውም ሆነ መምህሩ የቋንቋ እውቀት ከማዳበር አኳያ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

## 2.2 የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትና ማስተማሪያ ዘዴዎች

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ክሂሎች በሚገባ ተግባራዊ ይደረጉ ዘንድ የቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ የሰዋስዋዊ ስርዓት እውቀት ደግሞ የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ ባየ (1987፡8) እንደሚከለው ይገልፃሉ፡፡

> *...ከማንኛውም የክህሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋዋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባ ጥልቅ የሆነ እውቀት አለ፡፡ ይኸውም ከፍ ሲል የጠቀስነው የቋንቋዋው ስርዓት ወይንም ሰዋስው በመባል የሚታወቀው ነው፡፡...የአንድን ቋንቋዋ አጠቃቀም ከነስርዓቱ የሚያውቅ ሰው መኪና አነዳድንና የመኪና አካለትን አሰራር እንደሚያውቅ መካኒክ ሾፌር የሚቆጠር ነው፡፡ እንዲሀ ዓይነቱን ሾፌር ደግሞ የትራፊክን ህግ ጠብቆ እንዲያሽከረክር ከሰለጠነ ሾፌር የበለጠ የመኪናና ያነዳድ፣ ማለትም ያጠቃቀም እውቀት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህም ከተራ አሽከርካሪ ጋር አይመደብም፡፡*

ምሁሩ የሰጡት ገለፃ የሚያመላክተው ቋንቋን የማስተማር ዓላማዎች መመስረት ያለባቸው በክህሎት ትምህርት ላይ ብቻ ሳይሆን በቋንቋ ስርዓትም ጭምር መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋውን አጠቃቀም እውቀት ኑሮት ትምህርት

ቤት ገብቶ የቋንቋውን ስርዓት የተማረ ሰው ቋንቋውን በልምድ ከሚያውቀው ሌላ ሰው የተሻለ እውቀት እንደሚኖረው ነው፡፡ ጌታሁን (1990፡V) ይህን ሀሳብ ሲያጠናክሩ፣

> *አንድ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ትክክለኛ የሆነ ዓረፍተ ነገር ትክክል ካልሆነው ለይቶ ሊነግረን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር ነው ያልነውን ትክክል ለመሆኑም ሆነ ስህተት ነው ያልነውን ስህተት የሆነበትን ምክንያት ሊናገር አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሊናገር የሚችለው ቋንቋውን አቀላጥፎ መናገር የሚችለው ሳይሆን የቋንቋውን ስርዓት የሚያውቀው ባለሙያ ብቻ ነው፡፡*

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት አንድ ሰው ምንም እንኳ ሰዋስው ሳይማር በቋንቋው ለመገልገል የሚያስችል ችሎታ ኖሮት ቢጠቀምበትም ለምን እንደዛ እንዳለ ስርዓቱን የማስረዳት ችሎታ ግን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም የቋንቋን ስርዓት በሚገባ ለማወቅ ሰዋስውን መማር አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና እና ከቋንቋ ክሂሎች ተነጥሎ የማይታይ ነው፡፡ ምክንያቱም በቋንቋ ትምህርት ወቅት ሰዋስውን ማስተማር የቋንቋ ተማሪው የቀረበለትን የሰዋስው መዋቅር በአግባቡ እንዲማርና እንዲጠቀምበት ያስችላል፡፡

የሰዋስው ትምህርት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርቱን ማቅረብ ሲቻል ነው፡፡ የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ርቱዕ (Overt) እና ኢ-ርቱዕ (Covert) በሚባሉ ሁለት መንገዶች መቅረብ ይችላል (Harmer 1978)፡፡

ርቱዕ የማስተማሪያ ዘዴ የሚባለው የሰዋስው ትምህርት አቀራረቡ የቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ብያኔዎች፣ የቃላት ትርጉም ወዘተ. እንዲያጠኑ በማድረግ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት ራሱን የቻለ ይዘት በማዘጋጀት ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ብቻ እንዲያውቁ የሚደረግበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የሰዋስው ትምህርቱ ለቋንቋ ክሂሎች ትኩረት አይሰጥም፡፡ ኢ- ርቱዕ

የማስተማሪያ ዘዴ የሚባለው ደግሞ የሰዋስው ትምህርት አቀራረቡ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ለተማሪዎቹ በግልፅ የሚቀርብበት ሳይሆን እንዲማሩ የተፈለገውን የሰዋስው ይዘት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርብበት ነው። ይህም የሚያመላክተው ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት የሚማሩት ከክሂሎች ተነጥሎ ለብቻው ሳይሆን መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብና መፃፍ ሲማሩ ከክሂሎቹ በስተጀርባ የሰዋስው ትምህርት ተቀናጅቶ የሚቀርብበት ነው።

በቋንቋ መማር ማስተማር ሰዋስውን ለማስተማር ቀጥተኛ (Dedective) እና ኢ-ቀጥተኛ (Indective) በሚባሉ ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል። ቀጥተኛ ዘዴ የሚባለው መምህሩ የቋንቋውን ህግ ለተማሪዎች በመንገር በቀጥታ የሚያስተላልፍበት ሲሆን ኢ-ቀጥተኛ ዘዴ ደግሞ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግ ምሳሌዎችን በማስደገፍ የሚሰሩበትና መምህሩ ተማሪዎችን መንገድ የሚያሳይበት፣ ለመስራት የሚያነሳሳበት ነው http://www.teachingenglish.org.uk/polls/approaches-teaching-grammar።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ርቱዕ (ቀጥተኛ) የማስተማሪያ ዘዴ ሰዋስውን ለማስተማር የመማር ማስተማር ሂደቱ መምህሩ በመንገር ተማሪዎች ደግሞ በማዳመጥ የሚካሄድ ነው። ስለዚህ ሂደቱ መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተከተለ ነው። በሌላ አቅጣጫ ኢ-ርቱዕ (ኢ-ቀጥተኛ) የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ሰዋስውን ሲማሩ ምሳሌዎችን እየሰጡ እና በይዘቶቹ እየተወያዩ በመማር ማስተማር ሂደቱ ማዕከል የሚሆኑበት ነው።

የሰዋስው ትምህርት የቋንቋውን ስርዓት በመንገር፣በመተንተንና በማጥናት ብቻ የሚዳብር ሳይሆን ምልልሶችን አዘጋጅቶ ተማሪዎችን በማሳተፍ፣ የተለያዩ ስዕሎችን በማሳየት፣በይዘቶቹ ተማሪዎች እንደዲወያዩ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ፣እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱ እና የራሳቸው ሚና እንዲጫወቱ በሚያደርግ መልኩ ማስተማርን የሚጠይቅ ነው (Harmer 1978)።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው ሰዋስውን ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ሲቀርቡ በርቱዕ (ቀጥተኛ) እና ኢ-ርቱዕ (ኢ-ቀጥተኛ) የማስተማሪያ ዘዴዎች ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ከግብ የሚደርሰው ለተማሪዎች በመንገር ሳይሆን የመማር ማስተማር ሂደቱ በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የታጀበ ሲሆን ነው፡፡ ለዚህም ኢ-ርቱዕ (ኢ- ቀጥተኛ) ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2.3 የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች

የማስተማሪያ ዘዴ አንድ የቋንቋ መምህር ለማስተማር ያዘጋጀውን ይዘት እንዴት ቢያስተምር የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንደሚሆን እና የቋንቋ እውቀት በተማሪዎች አእምሮ እንዴት እንደሚደራጅ የሚያመለክት ሳይንስ ነው (Richards and Rodgers 1986)፡፡

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያየ ስያሜ ማለትም ጥንታዊ እና ዘመናዊ (Nunan 1988), ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ (Muttussa and Wills), መምህር ተኮር እና ተማሪ ተኮር (ICDR 1999) በማለት ይከፍሉዋቸዋል፡፡ ዘመናዊ (ኢ-ቀጥተኛ፣ተማሪተኮር) የማስተማሪያ ዘዴ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ስያሜ ይሰጡታል፡፡ ለምሳሌ፣ ደረጀ (1999) O,Nill (2005)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ትብብራዊ የትምህርት አቀራረብ፣ ራስ የመገንባት አቀራረብና ተሳታፊ ተኮር የሚል ስያሜ እንደሚሰጡት ይገልፃሉ፡፡ Temesgen (2002) ደግሞ ብዙ ምሁራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ (ተሳትፎአዊ) የትምህርት አቀራረብ እንደሚሉት ይገልፃሉ፡፡

ምሁራኑ ከሰጡት ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን አንድን የትምህርት ይዘት እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው እና የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ የሚመራ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች የተለያዩ ምሁራን የመምህራንና የተማሪዎች ተሳትፎ መሰረት በማድረግ መምህር ተኮር እና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በማለት በሁለት ይከፍሉዋቸዋል፡፡

### 2.3.1 መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ

መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ልማዳዊ የትምህርት አሰጣጥ ሲሆን የመማር ማስተማር ሂደቱ በመምህራን የበላይነት የሚጠናቀቅበት ነው (Nunan 1988)። በመምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የሚፈፅሙት ተግባር መናገርና መፃፍ ብቻ ናቸው (Borich 1984)።

በቀረበው ገለፃ መሰረት መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ ተግባራት ሁሉ እንደዋና ተዋናይ ሆነው የሚሳተፉበት፣ ስለሚሰሩ ስራዎች ለመወሰን ሙሉ ስልጣንና ሀላፊነት የሚያገኙበት፣ክፍለ ጊዜው በመምህራን መናገር እና መፃፍ የሚጠናቀቅበት መሆኑ ነው።

በመምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በቀረበው ርዕስ ጉዳይ ላይ እንዲወያዩ፣ እዲከራከሩ፣እንዲመራመሩ፣እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱ እና ሀሳብ እንዲያፈልቁ የሚደረግበት አጋጣሚ ስለማያገኙ ትምህርቱን የሚያገኙት አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የሚናገሩትን በማዳመጥ እና ማስታወሻ በመያዝ ነው። በመሆኑም ተማሪዎች ፍዝ ተቀባዮች ስለሚሆኑ የመማር ማስተማር ሂደቱ ስልቹ ይሆናል (Plass 1998, Richands and Rogers 2001)።

በአጠቃላይ መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱ ማዕከል የሚሆንበት ከመሆኑ የተነሳ የእውቀት ምንጭ ተደርገው የሚታዩበት ነው። ከዚህም በተጨማሪ መምህራን ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበት፣ ገለፃ በመስጠትና በመቆጣጠር የበላይነት የሚያሳዩበት ፣ተማሪዎች ሁልጊዜ ከግል ስራ ውጭ በህብረት የማይሰሩበት እና መምህሮቻቸው የተናገሩትን ከማዳመጥና ከመፃፍ ውጪ ምንም ዓይነት ተሳትፎ የማያሳዩበት ስለሆነ ተማሪዎች የተነገራቸውን የሚያዳምጡ ተቀባዮች ይሆናሉ።

## 2.3.2 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ከመምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተቃራኒ ተማሪዎች መምህራን የሚነግሩዋቸውን ከማዳመጥ አልፈው በራሳቸው መስራት የሚችሉበትን መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ሀሳብ የገለፁ ሲሆን ከነዚህም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት እርስ በርስ እዲገናኙ ወይም ተራክቦ (interaction) እንዲፈጥሩ ዕድል የሚያገኙበትና ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበት ነው (Bonwell and Eison 1991)፡፡ Silberman (1996) ይህን ሀሳብ በማጠናከር ተማሪዎች እውቀት የሚያገኙት ልክ አንድ ታንከር እስኪሞላ ድረስ ጋዝ እንደሚቀበል ሁሉ የተማሪዎች ጭንቅላት እስኪሞላ ማንኛውንም ዓይነት መረጃ በመድፋት ሳይሆን የነሱ ንቁ ተሳትፎ ሲኖርበት ነው፡፡ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎች ተነሳሽነትና ብቃት የሚካተትበት ነው (ICDR 1999)፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ማስተማር ሲባል ልክ እንደ መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ለተማሪዎች መረጃ ማስተላለፍ ሳይሆን ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ ሲያሳዩ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እውቀት የሚገኘው ትምህርት ቤት ሂዶ የሚነገረውን ጉዳይ በማዳመጥ ብቻ ሳይሆን በሚነገረው ጉዳይ ተሳታፊ በመሆንና እርስ በርስ ሀሳብን በመለዋወጥ ነው፡፡ ይህን ገዳይ በተመለከተ Bedilu (2011:9) (Brown 2004) ን ጠቅሰው እንደሚከተለው ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

> *ተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን አስመልክተው የስነ አእምሮ ባለሞያዎች እና የዕለት ተዕለት የምልከታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በዚህ የማስተማሪያ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች በመምህር ተኮር ዘዴ ከሚማሩት ተማሪዎች በሀሳብና አዲስ ነገር በመፍጠር ደረጃ በጣም የተሻሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዘዴው ተማሪዎች በሰፊው የሚሳተፉበት፣ ያለፉትን የሚያስተውሱበት አዲስ ፅንሰ ሀሳብ እንዲፈጥሩ እድል የሚያገኙበት ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሲሆን በዚህ ወቅት መምህራንና ተማሪዎች የዘዴውን ግብ እና ዓላማ ተገንዝበው ሀላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፡፡*

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደቱ ማዕከል የሚሆኑበት፣ የሚማሩትን ጉዳይ ከራሳቸው ልምድ ጋር በማያያዝ እንዲነጋገሩ (እንዲማማሩ) ዕድል የሚያገኙበት እና አዲስ ፅንሰ ሀሳብ የመፍጠር ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ዘዴ በመሆኑ ከመምህር ተኮር የተሻለ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ሀሳብን በመቀበል ብቻ አድማጮች ከሚሆኑ ይልቅ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ Seifu (2011፡14) Chickering and Gamson (1987)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ደግሞ፣

> *ትምህርት እንደ ስፖርት ተመልካች አትኩሮ በማየትና በመስማት የሚገኝ አይደለም፡፡ ተማሪዎች ስለሚማሩት ይዘት ካለፈ ልምዳቸው እና ከዕለት ተዕለት የህይወት ተሞክሯቸው ጋር በማያያዝ መወያየትና መከራከር አለባቸው፡፡ ምክንያቱም መማር እያደገ የሚሄደው እና ፍሰቱ የሚጨምረው የተማሪዎች ልምድ ሲጨመርበት ነው፡፡ በዚህ ወቅትም መምህሩ ቁሳቁሶች እና አስፈላጊ ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡*

በቀረበው ገለፃ መሰረት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች መምህር የሚያስተምረውን በማዳመጥ እውቀት ተቀባዮች ብቻ ሳይሆኑ በመማር ማስተማር ሂደቱ ስለሚማሩት ይዘት በመወያየት፣ በመከራከርና ወዘተ. የነቃ ተሳትፎ በማንፀባረቅ እውቀታቸውን እያሳደጉ መማር የሚችሉበት ሲሆን የመምህሩ ሚና እንዴት እንደሚሰሩ አቅጣጫ ማሳየት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች መገንዘብ የሚቻለው የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው የሚተላለፍላቸውን ትምህርት በማዳመጥ የሚያገኙትን ግብአት ብቻ በቂ አለመሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የታላሚውን ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስና በእውቀት የተገነቡ ተማሪዎችን ለማፍራት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተመራጭ ዘዴ ነው፡፡

### 2.3.2.1 የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በሚገባ ተግባራዊ ከተደረገ ተማሪዎች ሀላፊነት እንዲሰማቸው ፣የፈጠራ ሰዎች እንዲሆኑ፣ ጥሩ አመለካከት፣ አስተሳሰብ ወዘተ. እንዲኖራቸው በማድረግ የእውቀት አድማሳቸው እንዲሰፋና መስራት እችላላሁ የሚል አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡

1. መምህራን ከተማሪዎች፣ተማሪዎች ከተማሪዎች እና ተማሪዎች ከመሳሪያዎች (materials) ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ያጠነክራል፡፡
2. እያንዳንዱ ተማሪ ንቁ ተሳታፊ ስለሚሆን ጥሩ ውጤት እንዲያመጣ ከማድረጉ በተጨማሪ የታለመውን ዓላማ ከግብ ያደርሳል፣ ማህበራዊ ግንኙነትን እና ክህሎትን እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡
3. ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ሀላፊነት በመውሰድ እንዴት መማር እንዳለባቸው ያሳውቃል፣ የአስተሳሰብን፣የአመለካከትን፣የማመንጨት፣ የማገናዘብ እና ችግሮችን የመፍታት ብቃታቸውን ያዳብራል፡፡
4. ተማሪዎች አብረው እንዲሰሩ ስለሚጋብዝ በመካከላቸው ተራክቦ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ይህም እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ እና እየተዝናኑ እንዲማሩ ያደርጋል፡፡
5. አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ፣ በራስ የመተማመን ብቃትን ለማሳደግ ይረዳል፡፡
6. ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት እንዲጨምር ከማድረጉም ባለፈ ትምህርቱን አይረሴ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
7. የታለመው ዓላማ ከግብ መድረሱን እና አለመድረሱን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ምክንያቱም የአንድ ትምህርት ግቡ ወይም ዓላማው የሚታየው ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በራሳቸው ሀሳብ ማቅረብ ሲችሉ ነው፡፡
8. ተማሪዎች የራሳቸው የመማር፣ የአጠናን እና የጊዜ አጠቃቀም ዘዴ እንዲኖራቸውና እንዲጠቀሙ ያደርጋል (Harmer 1978, Benwell and Eison 1991, Tudor 1993, Silberman 1996, Hoke 2009)፡፡

### 2.3.2.2 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና

#### 1. የመምህራን ሚና

በመማር ማስተማር ሂደት አጥጋቢ ውጤት ለማስገኘት መምህራን የመረጡትን የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅመው ሲያስተምሩ ሚናቸውን በሚገባ መወጣት አለባቸው (Petty 2004)።

የመምህራን ዋነኛ ሚና የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ የሚያደርጉ የማስተማሪያ ዘዴዎች መርጠው በማስተማር ተማሪዎች የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ማድረግ ሲሆን ይህንን ስኬታማ ለማድረግ ደግሞ የመምህራንና የተማሪዎች ተራክቦ የተቃና መሆን ወሳኝነት አለው (Widdwoson 1987)። ስለዚህ የቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅምው ሲያስተምሩ ሚናቸውን በሚገባ ይወጡ ዘንድ ከትምህርት ፖሊሲ ዓላማ አንፃር ማስተማር፣ከተማሪዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት መኖር፣ የተማሪዎች አጠቃላይ አመለካከት መገንዘብና ለትግበራው የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማዘጋጀት አለባቸው (Tudor 1993)።

ስለዚህ የመምህራን ሚና ዘዴውን ለመተግበር የሚያስችሉ ነገሮችን በሟሟላት እና ተማሪዎችን ለመማር በማነሳሳት እውቀት እንዲጨብጡ ማድረግ ነው።

ጠቅለል ባለ መልኩ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ መምህራን የሚጫወቱትን ሚና በተመለከተ ቀጥለው የቀረቡት ይጠቀሳሉ።

- **ተማሪዎችን ማዘጋጀት**፡- ይህ ተማሪዎችን ማነሳሳትና ማነቃቃት፣ የትምህረቱን ዓለማ ማሳወቅ የመሳሰሉትን ያካትታል።
- **ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ለይቶ ማወቅ**፡- ተማሪዎች የመተርጎምና የመረዳት ክህሎት ስላላቸው ራሳቸው እንዲሰሩት ቢደረግም እንኳ እንዴት እንደሚሰሩት መንገዱን ማሳየት እና ተማሪዎች የሚፈልጉትን ሳይሆን የሚያስፈልጋቸውን ለይቶ በማወቅ ሙያዊ እገዛ ማድረግ ከመምህሩ የሚጠበቁ ተግባሮች ናቸው።

- **የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥ፡-** መምህራን ለማስተማር ያዘጋጁትን የትምህርት ይዘት የሚያስተምሩበት ዘዴ መምረጥን የሚመለከት ሲሆን ይህም የተማሪውን ማንነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡
- **ተማሪዎች ሀላፊነት እንዲሸከሙ ማድረግ፡-** በዚህ ወቅት መምህራን ምን ዓይነት ተማሪዎች ድርሻቸውን እየተወጡ ነው? እና ተማሪዎች ለመስራት ምን ያህል አቅም አላቸው? የሚሉትን ነጥቦች መገምገም አለባቸው፡፡
- **ለሚያስተምሩት ይዘት በቂ ዝግጅት ማድረግ፡-** ስለሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት በቂ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመማር ማስተማር ሂደቱን መቆጣጠር፣ ትክክለኛ የቋንቋ ሞዴል ማዘጋጀት፣ ተማሪዎችን ማደራጀት፣ ተማሪዎች ያላቸውን ልምድ እና የሚያደርጉትን ሙከራ አማካሪ መሆን የሚሉት ይገኙባቸዋል (Tudor 1993, Getachew 2001, Widdwoson 1987, Nunan 1988)፡፡

በአጠቃላይ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የሚሳተፉ መምህራንና ተማሪዎች ሲሆኑ፤መምህራን ከተማሪዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር ተማሪዎች ለመማር እንዲነሳሱ፣ አብረው እንዲሰሩና እንዴት እንደሚሰሩ በማማከር ተማሪዎች እንዲወያዩ ፣ሀሳባቸውን እንዲለዋወጡ ፣እንዲከራከሩ ወዘተ.የማድረግ ሚናዎች ይጫወታሉ፡፡

## 2. የተማሪዎች ሚና

በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎች ዋነኛ ሚና ንቁ ተሳታፊ በመሆን መማር ሲሆን ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ደግሞ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት፣ተሳትፎ፣ተነሳሽነትና ሌሎች ተጓዳኝ ነገሮች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው (Widdwoson 1987)፡፡

በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ማቀድና በክፍል ውስጥ (ሀላፊነት መውሰድ፣ ማስታወሻ መያዝ) ፣ የተማሩትን ማጥናት፣ በራሳቸው ችሎታ መሰረት እርስ በርስ መተጋገዝ እና እርስ በርስ ከሚያደርጉት ግንኙነት ተጠቃሚ መሆን መቻል አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራሳቸውን የመማሪያ ስልት፣ የጊዜ ሰሌዳ፣ የአጠናን ዘዴ ማዘጋጀትና በመማር ማስተማር ሂደቱ መወያየት፣መጠያየቅ፣ መከራከር፣ መጠየቅ፣መመለስ ወዘተ.

ከነሱ የሚጠበቁ ተግባሮች ናቸው (Tudor 1993, Azeb 1984, Getachew 2001, Nunan 1988)።

ጠቅለል ባለ መልኩ በአሳታፊ የመማር ማስተማር ትግበራ የተማሪዎች ሚና

- ንቁ ተሳታፊ መሆን
- ጥያቄዎች መጠየቅ እና መመለስ
- ሀላፊነት በመውሰድ መማር
- ሀሳባቸውን ማንፀባረቅ እና
- የሌሎችን ሀሳቦች በማዳመጥ አስተያየት መስጠት ናቸው

http:// www.nicurriculum.org.uk/docs/key_stage_3/ALTM-KS3.pdf።

ከላይ እንደተገለፀው በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን አስተዋፅኦ የሚያደርጉ፤ የመምህሩን ንግግር እየጠበቁ የሚያዳምጡና የሚፅፉ ሳይሆኑ መምህራቸው የሰጡዋቸውን ነገር ለመስራት ሃለፊነት በመውሰድ የሚሰሩ ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው።

### 2.3.2.3 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች

#### ሀ.የመምህራንና የተማሪዎች ፍላጎት በቀላሉ መቀየር አለመቻል

በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የነበረውን አመለካከትና አስተሳሰብ በቀላሉ መቀየር አለመቻል የሚከሰተው፣ባለመግባባት፣ ባለመጣጣም፣ባለማመን፣ በትምህርት የተገኘውን ልምድ ማስወገድ ባለመቻል ወዘተ. ሊሆን ይችላል። ከዚህም የተነሳ መምህራን ከመምህር ተኮር ዘዴ ያገኙት ልምድ አሁን ተግባራዊ እንዲሆን በሚፈለገው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ሊፈጥር ይችላል (Plass 1998)።

ከመምህራን በተገኘው አስተያየት መሰረት መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ ተፅእኖ ከሚያሳድሩባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ተማሪዎች ለአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አወንታዊ አመለካከት አለመኖር፣መምህራን በቂ ጊዜ ስለማይኖራቸው የመማሪያ መፅሀፍ መጨረስ አለመቻል እና ውይይትና አሳይመንት በቡድን ሲሰጡ

ደግሞ በተወሰኑ ተማሪዎች ተሳትፎ ብቻ እንዲሸፈን ዕድል መፍጠር የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡ ተማሪዎች ደግሞ በመምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎች ሚና መምህሩ የተናገረውን መፃፍ፣ ማዳመጥ፣ የተፃፈውን ማጥናትና መፈተን ስለሆነ ቀላል አድርገው ይወስዱታል፡፡ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ወቅት ግን ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲመካከሩ፣ እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱና እንዲገመግሙ ሀላፊነት ስለሚሰጣቸው ያንን ሀላፊነት ላለመውሰድ ሲሉ ተማሪን ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ እንዲተገበር አይፈልጉም፡፡ ይህ የመምህራንና የተማሪዎች ፍላጎት ደግሞ መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ይገፋፋል (Bonwell and Eison 1991)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች እርስ በርስ የሚማማሩበት መምህሩ ደግሞ እንደ አነሳሽ፣መንገድ ከፋች ወይም ፍንጭ ሰጪ የሚሆንበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር መምህራንና ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ ተፅእኖ ያሳድራሉ፡፡ ለዚህ ተፅእኖ መንስኤው ተማሪዎች ሀላፊነትን ለመውሰድ ካላቸው ፍርሃት የተነሳ ሲሆን መምህራን ደግሞ ካለው የጊዜ እጥረት፣ ተማሪዎች ለዘዴው ጥሩ አመለካከት አለመኖር፣ የሚሰጠውን ስራ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዲሰራ እድል ስለሚፈጥር ወዘተ.የሚሉት ናቸው፡፡

### ሰ. የመማሪያ ክፍል ሁኔታ

የመማሪያ ክፍል ሁኔታ ማለትም የቁሳቁሶች አቀማመጥ፣ የክፍሉ አደረጃጀት፣ የመማሪያ ክፍሉ መስፋትና መጥበብ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ወሳኝ ነው (Sqazzin and Graan 1998)፡፡ ጥሩ የመማሪያ ክፍል በሌለበት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር አስቸጋሪ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በሚገባ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በክፍል ውስጥ የሚገኙ መቀመጫ ወንበሮች ቀላልና በቀላሉ ተንቀሳቃሽ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ዘዴውን በመተግበር ሂደት ተማሪዎች ከቦታ ቦታ እንዲቀሳቀሱ ያስችላቸዋል (Silberman 1996)፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለመተግበር ተማሪዎች የሚማሩበት የመማሪያ ክፍልም የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ይህን

የማስተማሪያ ዘዴ በሚገባ ለመተግበር አስፈላጊ ቁሳቁሶች የተሟሉበት፣ዘዴውን ለመተግበር ከሚያስፈልገው የተማሪ ቁጥር አንፃር የተመጣጠነ ወንበርና ዘዴውን ሲተገበር በወንበሮቹ መካከል ለመንቀሳቀስ የሚያስችል በቂ ከፍተት ያለበት መማሪያ ክፍል መሆን አለበት፡፡

### ሐ. የተማሪዎች ቁጥር

በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር በጣም ብዙ ከሆነ ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ ለመመደብ አስቸጋሪ ከመሆኑም ባለፈ ለመቆጣጠር ያስቸግራል (Sqazzin and Graan 1998)፡፡ ስለዚህ ይህ ችግር እንዳያጋጥም በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ከወንበሮቹ ቁጥር ጋር የተመጣጠነና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺነት ያለው መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር እንደየ አገሩ የትምህርት ፖሊሲ የተለያየ ቢሆንም እንኳ በኢትዮጵያ ትምህርት ፖሊሲ መሰረት በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር አርባ መሆን አለበት (ትምህርት ሚኒስቴር 1999)፡፡

በአጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር እንቅፋት ከሚሆኑ ጉዳዮች የተማሪዎች ቁጥር መብዛትና የወንበሮች ቁጥር ከተማሪዎች ቁጥር ጋር አለመመጣጠን (ማነስ) ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል በቡድንና በጥንድ ለመመደብ፣ ተማሪዎችን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ስለሚሆን በአንድ ክፍል ውስጥ ለዚህ ሁኔታ የማያመች ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች መማር የለባቸውም፡፡

### መ. በቂ ጊዜ አለመኖር

ኤልያስ (1997) Cruickshank and etal.(1991) ን ጠቅሰው እንደገለፁት በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ለማስተማር ያዘጋጁትን ይዘት በሚገባ ለማስተላለፍና ተማሪዎች ለማሳተፍ በቂ ጊዜ መኖር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በመማር ማስተማር ሂደት በቂ ጊዜ ከሌለ መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ ጨምረው ባለው ጊዜ ውስጥ በመማሪያ መፅሀፍ ያለውን ይዘት መጨረስ ስለማይችሉ መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ እንዲተገብሩ ይገደዳሉ፡፡

ስለዚህ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር በቂ ጊዜ አለመኖር የራሱ የሆነ ተፅእኖ ስላለው ዜዴውን በሚገባ ለመተግበር የጊዜ ጉዳይ መታሰብ አለበት፡፡

### ሠ. የመማሪያ መፃህፍት (ሞጁል) አዘገጃጀት

Seifu (2011) Girma (2005) ን ጠቅሰው እንደገለፁት የመማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ በሁለት አቅጣጫ ይታያል፡፡ የመጀመሪያው በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶችን መሰረት ያደረገ ሲሆን ይህም የመማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር አመቺ ሆኖ መቅረብና አለመቅረብን ያጠቃልላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በመማሪያ መፅሀፉን እና በመምህሩ መምሪያ መካከል ያለውን መጣጣም የሚመለከት ሲሆን በሁለቱም መካከል መጣጣም ከሌለ ዘዴውን ለመተግበር የራሱ የሆነ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር በሚያመች መልኩ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመማሪያ መፅሀፍ እና በመምህሩ መምሪያ መካከል መጣጣም መኖር አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ዘዴውን በሚገባ መተግበር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

### ረ. የመምህራን ስልጠና

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የመምህራን ስልጠና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ዘዴው ተግባራዊ ሲደረግ የመምህራን ሚና ፍንጭ መስጠት ቢሆንም እንኳ ዘዴውን በሚገባ ለመተግበር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን የሚመለከት ስልጠና መውሰድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራን በኮርስ እቀድ ክህሎት፣ በፍላጎት አሰሳ ክህሎት፣ በትምህርት ክህሎትና የመማር ማስተማር ሂደቱን ከዜዴዎች ጋር ማጣጣም በመሳሰሉት ስልጠና ማግኘት አለባቸው (Tudor 1996)፡፡

ስለዚህ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን ዘዴውን በሚመለከት በቂ ስልጠና ሊወስዱ ይገባል፡፡

### 2.3.2.4 የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር

#### ሀ. የቡድን ውይይት

የቡድን ውይይት በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተግባራዊ ከሚደረጉና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ስር ከሚመደቡ አንዱ ነው። ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ከተማሪዎች ጋርና ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በመመካከር ስለተሰጠው ርእሰ ጉዳይ ሀሳብ የሚለዋወጡበት፣ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ የሚፈልጉበት፣ አመለካከታቸውን የሚገልፁበት፣ መደምደምያ ሀሳብ ላይ የሚደርሱበትና ንቁ ተሳፊ የሚሆኑበት ነው (Getachew 2001)።

የቡድን ውይይት ተማሪዎች እርስ በርስ ሃሳብ በመለዋወጥ የሌሎችን ግንዛቤና አመለካከት ማዳመጥ፣ በጥልቀት መገምገም ፣ለውይይት የቀረበውን ጉዳይ (የተነሱትን ሀሳቦች) መረዳት እና በርእሱ ላይ ሰፊ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖር የማድረግ ሂደት ነው (ICDR 1999)።

ከላይ እንደተገለፀው የቡድን ውይይት ተማሪዎች በቡድን በመሆን ስለተሰጣቸው ርዕስ ጉዳይ እውቀታቸውን፣ክህሎታቸውን እና አመለካከትቸውን በመለዋወጥ የሚማማሩበት ዘዴ ነው።

#### ለ. የግል ስራ

የግል ስራ አንድ ተማሪ እንዲሰራው የተሰጠውን ነገር ከመምህሩ እና ከጓደኞቹ እገዛ ውጭ ብቻውን የሚሰራበት ነው። በግል ስራ ተማሪዎቸ የሚሰሩት ነገር ሁሉ ከመምህርና ከጓደኛ ተፅእኖ ነፃ በመሆን በራሳቸው አቅም ስለሆነ በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው (Harmer 1991)።

የግል ስራ ተማሪዎች ለሚሰሩት ነገር በግላቸው ሀላፊነት በመውሰድ የሚሰሩበትና የግል እውቀታቸው ለሌሎች የሚያንፀባርቁበት ነው። የግል ስራ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በክፍል ስራ መልክ እና በቤታቸው በቤት ስራ መልክ ሊሰጥ ይችላል (Hand Book of Higher Diploma Program 2011)።

የግል ስራ ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ ለመቆጣጠር ፣ የሚሰሩበትን ምንጭ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፣ መረጃው ያገኙበትን ምንጭ ለመለየት፣ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ፣ ጠለቅ ያለ እውቀት ለማግኘት እና ለመማር የተፈለገውን ጉዳይ በቀጥታ ለማግኘት ይረዳቸዋል (Petty 2004)፡፡

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት የግል ስራ ከመምህርና ከተማሪ እገዛ ውጭ በቤት ወይም በክፍል ውስጥ የሚሰራ ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ የግል እውቀቱን ወረቀት ላይ የሚያሰፍርበት እና በግል ጥረቱ ያገኘውን እውቀት ለክፍል ጓደኞቹ የሚያስተላልፍበት ነው፡፡

### ሐ. የቡድን ስራ

የቡድን ስራ ከሁለት በላይ የሆኑ ተማሪዎች አንድ ላይ በመደራጀትና እርስ በርስ በመተባበር መማማርን የሚፈጥሩበት ነው፡፡ የቡድን ስራ አንድን ተግባር ለመስራት ተማሪዎች እርስ በርስ ሀሳባቸውን፣ እውቀታቸውንና አመለካከታቸው የሚለዋወጡበት፣ ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩበት፣ መምህሩ በአስተባባሪነት የሚሰራበትና የአንድ ቡድን አባላት እንደ አንድ ተማሪ ተደርጎ የሚታይበት ነው (Brumfit 1984)፡፡

የቡድን ስራ ተማሪዎች ተሰባስበው ውሳኔ የሚሰጡበት፣ ከተቀባይነትና ከጥገኛነት ነፃ የሚወጡበት እንዲሁም መምህሩ ከመምህር ተኮር ማስተማር የሚላቀቅበት ነው (Doff 1988)፡፡ የቡድን ስራ ቋንቋን በተግባበታዊ ሁኔታ ለማስተማር ከሚረዱ ዘዴዎች አንድ ሲሆን ሂደቱ ጥገኛ የሚሆነው ተማሪዎች የራሳቸውን የቋንቋ ክሂል ተጠቅመው በሚለዋወጡዋቸው መረጃዎች ላይ ነው (Richards and Rodgers 2001)፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸው የተሰጣቸውን ተግባር በቡድን እንዲሰሩ በሚያደርጉበት ወቅት ዕድሜን፣ ውጤትን ፣ጓደኝነትን፣ፍላጎትንና ፆታን መሰረት በማድረግ የቡድን አባላቱን ማደራጀት ይችላሉ (Cohen 1994)፡፡

በአጠቃላይ የቡድን ስራ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ተራክቦ በመፍጠር እንዲማሩት በተዘጋጀው ይዘት ላይ ሀሳባቸውን በመለዋወጥ፣በመወያየት፣ በመጠያየቅና በመከራከር ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቡድን ስራ ቋንቋን በተግባቦታዊ ሁኔታ ለማስተማር ጠቃሚ ከሚባሉት ዘዴዎች አንድ ሲሆን መምህራን የቡድን ስራን

ተግባራዊ ሲያደርጉ አንድ ቡድን ላይ የሚደራጁ ተማሪዎች ለመመደብ ትምህርታዊ መስፈርቶችን ማለትም ጎበዝ ፣መካከለኛና ደካማ እንዲሁም ትምህርታዊ ያልሆኑ ዕድሜ፣ ፆታ ፣ጓደኝነት ወዘተ. መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ይመድባሉ፡፡

### መ. የጥንድ ስራ

በጥንድ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ሁለት ሁለት ሆነው ያልተሟላ ሀሳብ ሲጨርሱ፣ በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ሲወያዩ ፣ በጣም አነስተኛ የሆነ ስራ ሲሰሩ የሚደራጁበት ነው፡፡ በጥንድ ስራ አንድ ተማሪ ካጠገቡ ካለው ተማሪ ወይም ካሁን በፊት አብሮት ካልሰራ ተማሪ ጋር ሊመደብ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ዘዴ ተማሪዎች በጥንድ ሆነው የተሰጣቸውን ተግባር ከሁለት እስከ ሶስት ደቂቃዎች ባሉት ጊዜያት ከተወያዩ በኋላ ከጥንድ ውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስተላልፉ የሚደረግበት ነው (Doff 1988)፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የጥንድ ስራ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው የተሰጣቸውን ተግባር በተሰጣቸው ውስን ጊዜ ውስጥ እንዲፈፅሙ በማድረግ ከጥንድ ውይይቱ ያገኙትን ግብአት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስተላልፉ የሚደረግበት ነው፡፡

### ሠ. ጥያቄና መልስ

ጥያቄና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን ማንኛውንም ዓይነት ጥያቄ ለተማሪዎች በማቅረብ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ የማድረግያ ዘዴ ሲሆን ይህም ተማሪዎችን ለማነሳሳትና መምህራን ለጠየቁት ጥያቄ ከተማሪዎች ምላሽ ለማግኘት ይረዳል (Hand Book of Higher Diploma Program 2011)፡፡

ጥያቄና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ አንድ መምህር አንድን ይዘት ሲያስተምር ስለ አስተማረው ርዕስ ጉዳይ ተማሪዎች ምን እንደተረዱ እና የክፍለ ጊዜው ዓላማ ከግብ መድረሱንና አለመድረሱን ለማረጋገጥ በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ተማሪዎችን በመጠየቅ የሚያሳትፍበት ዘዴ ነው (Getachew 2001)፡፡

የጥያቄና መልስ አተገባበርን ውጤታማ (ስኬታማ) ለማድረግ መምህሩ አጭርና ግልፅ ጥያቄዎች ማዘጋጀት ፣ የተማሪዎችን አቅም ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ ከዚህም

በተጨማሪ ጥያቄውን ከመጠየቁ በፊት ጥያቄውን በሚገባ መግለፅ ፣ ለማሰብ በቂ ጊዜ መስጠት ፣ በተማሪዎች የሚሰጡ ምላሾችን በአትኩሮት ማዳመጥ፣ ለተማሪዎች ጥያቄ ፈጣን ምላሽ መስጠት ፣ ተማሪዎችን ማበረታታት ፣ ለተማሪዎች መልስ ማስተካከያ መስጠት እና ድክመታቸውን ለመሸፈን የተሳሳተ መልስ ላለመስጠት መጠንቀቅ የመሳሰሉትን ተግባራት በሚገባ መተግበር አለበት
http://samples.jbpub.com/9780763749453/49451_CH09_FINAL.pdf፡፡

## 2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርእስ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ግንኙነት ያላቸው ቀደምት አገርኛ ጥናቶች ከጥናታዊ ፅሁፉ ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ይጠቆማል፡፡

ሙሉጌታ በ(1996) "የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮተቤ መመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት መርሃ ግብር እንደታየው" በሚል ርእስ ጥናት ያካሄደ ሲሆን ዓላማው በኮሌጁ የሰርትፍኬት መርሃ ግብር የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ያለውን የአተገባበር ሁኔታ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ አጥኚው የጥናቱን ተተካሪዎች ለመምረጥ የታቀደ ናሙና ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን መረጃዎችን ለመሰብሰብ ደግሞ የክፍል ውስጥ ምልከታን ፣የቪድዮ ቀረፃን፣የተማሪዎች የዕለቱ ማስታወሻን ፣የፅሁፍና የቃል መጠይቅን ተጠቅሟል፡፡

በነዚህ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በኮሌጁ መርሃ ግብር በአማርኛ ኮርሶች ሲተገበር የታየ ቢሆንም መምህራኑ ካሉት የተማሪ ተኮር ዘዴዎች በጥቂቶቹ ላይ እንደተወሰኑ፣ ተማሪዎችም በዘዴው ለመማር ዝግጁ እንዳልሆኑ፣ በአንድ ቡድን የሚመደቡ አባላት ቁጥር እንደሚበዛ፣ሁሉም የብድን አባላት በጋራ ስራዎች እኩል ተሳትፎ አለማድረግና የጊዜ እጥረት የሚሉት ዘዴው በመተግበር ሂደት የሚገጥሙ ችግሮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዚህ ጥናት ርዕስ "የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ፍተሻ ፣በመቀሌ ከተማ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (በተመረጡ ዘጠነኛ ክፍሎች ናሙናነት)" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩት መፈተሹ ከሙሉጌታ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

የሙሉጌታ ጥናት በኮሌጅ ውስጥ የሚማሩ የሰርተፍኬት መርሃ ግብር ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በማትኮሩ፣የሙሉጌታ ጥናት በአንዲት መምህርት ላይ ብቻ ተከታታይ ፍተሻ በማድረግ የተካሄደ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የተለያዩ አማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ሙሉጌታ የጥናቱ ተተኳሪዎች አፋቸውን በተለያየ ቋንቋ የፈቱ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ አፋቸውን በተመሳሳይ ቋንቋ በፈቱ ተጠኚዎች ላይ በማትኮሩ ይለያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሙሉጌታ የጥናቱ ተተኳሪዎች ለመምረጥ የታቀደ የናሙና ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ዕጣ የማውጣት ዘዴ በመጠቀሙ፣ሙሉጌታ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ የክፍል ውስጥ ምልከታን ፣የቪድዮ ቀረፃን፣ የፅሁፍና የቃል መጠይቅን ከመጠቀሙ በተጨማሪ የተማሪዎች የዕለት ማስታወሻ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የተማሪዎች የዕለት ማስታወሻ አለመጠቀሙ፣በጥናቱ ተተኳሪዎች ዓይነትና መጠን እና በጥናት ዘመንና ቦታ የተለየ ነው፡፡

ኤልያስ በ(1997) "በኦሮምያ መምህራን ኮሌጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርእስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በክልሉ ውስጥ በሚገኙት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ መሰረታዊ አማርኛ ኮርሶች በማስተማር የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡

አጥኚው በክፍል ውስጥ ምልከታ፣በቪድዮ ቀረፃ፣በፎቶ ግራፍ ፣በፅሁፍና በቃለ መጠይቅ እንዲሁም በሰነድ ፍተሻ አማካይነት መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው የተማሪ ተኮር አቀራረብ በኮሌጆቹ በአማርኛ መሰረታዊ ኮርሶች ክፍለ ጊዜያት በብዛት ሲተገበር ታይቷል፡፡ ነገር

ግን ከተማሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች፤ ተማሪዎች እንዲሞክሩ ያለማድረግ፣መምህራኑ ሰፊ የንግግር ጊዜን የመውሰድና በሞጁል ዝግጅት ተማሪዎችን ያለማሳተፍ ችግሮች እንዳሉ ያመለክታል፡፡

ይህ ጥናት ከኤልያስ ጥናት ጋር ያለው ዝምድና ሲፈተሽ ሁለቱም ጥናቶች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበርን ማየታቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ ማትኮሩ ከኤልያስ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ልዩነቱ ደግሞ የኤልያስ ጥናት በኮሌጅ ደረጃ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ላይ በማትኮሩ፣የኤልያስ ጥናት መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የዘጠነኛ ክፍል አማራኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር ላይ ብቻ የተገደበ በመሆኑ እና ኤልያስ የጥናቱ ተተኳሪዎች ለመምረጥ የግኝት ናሙና ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ዕጣ የማውጣት ዘዴ በመጠቀሙ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኤልያስ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ የክፍል ውስጥ ምልከታን ፣የቪድዮ ቀረፃን፣የፅሁፍና የቃል መጠይቅን ከመጠቀሙ ባለፈ የሰነድ ፍተሻን የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የሰነድ ፍተሻ አለመጠቀሙ፣በጥናቱ ተተኳሪዎች ዓይነትና መጠን እንዲሁም በጥናት ዘመንና ቦታ ይለያያሉ፡፡

ደረጀ በ(1999) “የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር” በሚል ርእስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በኮሌጁ የተማሪ ተኮር አቀራረብ ያለውን የአተገባበር ሁኔታ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

አጥኚው የጥናቱ ተተካሪዎች ለመምረጥ ስብጥራዊ ናሙና ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን መረጃዎችን ለመሰብሰብ ደግሞ የክፍል ውስጥ ምልከታ ፣የቪድዮ ቀረፃ፣ የቃልና የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሁም የተማሪዎች የውሎ ማስታወሻ ተጠቅሟል፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው “ተማሪ ተኮር አቀራረብ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ተግባራዊ ሲደረግ ታይቷል፡፡ ነገር ግን

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቡድን መሪ፣አወያይና አቅራቢ በመሆን ቢሳተፉም በትምህርት መሳሪያ ግምገማ ፣ በመማሪያ ሞጁል አዘገጃጀት አለማሳተፍ፣ መምህራኑ የተወሰኑት ዘዴዎች ብቻ ተግባራዊ ማድረግ ፣የመማሪያ ክፍል ንፅህና የተጠበቀ አለመሆን፣ የጊዜ እጥረት እና መምህራኑ ስለተለያየ ማስተማሪያ ዘዴ በቂ ግንዛቤ አለመኖር ችግሮች እንደታዩ ያመለክታል፡፡

ይህ ጥናት ከደረጀ ጥናት ጋር ያለውን መመሳሰል ሲመረመር የተማሪ ተኮር አቀራረብን በመፈተሹ ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ የደረጀ ጥናት በኮሌጅ ደረጃ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በማትኮሩ፣የደረጀ ጥናት ቋንቋውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋቸው በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑና የደረጀ ጥናት በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በዘጠነኛ ክፍል የሰዋስው ይዘቶች በማስተማር ላይ ብቻ በማትኮሩ ይለያል፡፡ እንዲሁም ደረጀ የጥናቱ ተተኳሪዎች ለመምረጥ ስብጥራዊ ናሙና ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ዕጣ የማውጣት ዘዴ መጠቀሙ፣ ደረጀ መረጃውን ሲሰበስብ የውሎ ማስታወሻ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ግን አለመጠቀሙ፣በጥናቱ ተተኳሪዎች ዓይነትና መጠን እና በጥናት ዘመንና ቦታ የተለያዩ ናቸው፡፡

ዑመር በ(2002) "የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን የንኡስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር" በሚል ርእስ ያጠና ሲሆን የጥናቱ ዓላማ ደግሞ በሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

አጥኚው የጥናቱን ተተኳሪዎች ለመምረጥ የዕጣ ናሙና ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ምልከታ፣በፅሁፍና በቃል መጠይቅ አማካይነት መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው በኮሌጁ የንዑስ ቡድን ማስተማሪያ ዘዴ የአማርኛ መሰረታዊ ኮርሶችን በማስተማር ሲተገበር ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራንና ተማሪዎች በንዑስ ቡድን ለማስተማርም ሆነ ለመማር የሚያደርጉት ቅድመ ዥግጅት አለመኖር፣መምህራን የአንድ ቡድን አባላት

ለማደራጀት የተጠቀሙት መስፈርት በመታወቅያ ቁጥር ቅደም ተከተል መሆን፣ መምህራን የቡድን ስራ መስጠት እንጂ ስለ ቡድን ስራ ምንነት ለተማሪዎች አለማስረዳት፣ስራውን አለመገምገም፣ ተማሪዎች የተወያዩበትን እንዲያንፀባርቁ አለማድረግ የሚሉትን ደካማ ጎኖች እንደታዩ ያመለክታል።

ይህ ጥናት ከዑመር ጥናት ጋር ያለውን ዝምድና ሲፈተሽ አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ስር የሚካተት ዘዴ አተገባበር በመፈተሹ፣በሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ በማትኮሩ እና በናሙና ዘዴ ነው። ነገር ግን የዑመር ጥናት በኮሌጅ ደረጃ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በማትኮሩ፣ የዑመር ጥናት የንኡስ ቡድን የማስተማር ዜዴ ነጥሎ በመውሰድ አተገባበሩ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ አጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ላይ በማትኮሩ የተለየ ያደርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ ዑመር መሰረታዊ የአማርኛ ኮርስ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ከአማርኛ ክፍለ ጊዜ የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር ላይ ብቻ በማትኮሩ፣ በጥናት ቦታ፣ በጥናት ዘመን እና በጥናቱ ተተኳሪዎች ይለያያሉ።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ነጥብ ተጠቅሷል። በመሆኑም ያላቸውን መመሳሰል ሲታይ ከዑመር ውጪ ሌሎቹ አጥኚዎች ያካሄዱት ጥናት ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ተመሳሳይ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ አጥኚዎች ጥናታቸውን ያካሄዱት በኮሌጅ ደረጃ መሆኑ ተስተውሏል። ስለዚህ በሁለተኛ ደረጃ የተካሄደ ጥናት ስላላጋጠመ ይህን ክፍተት ለመሸፈን ጥናቱ አስፈላጓል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ሐወልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እንዴት እንደሚተገብሩት መፈተሽ ነው፡፡ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች (ተተኳሪዎች) እነማን እንደሆኑ፣ የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ ምን ምን ዘዴዎች በእንዴት ዓይነት መንገድ እንደተመረጡ እና ተግባራዊ እንደተደረጉ የሚያሳየው ዝርዝር መግለጫ እንደሚቀጥለው ቀርቧል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አደራጅቶ ለመተንተን መጠናዊ እና ዓይነታዊ ምርምር ተጠቅሟል፡፡ መጠናዊ ምርምር ስያሜው እንደሚያመላክተው መጠንን የሚያመለክቱና በቁጥር የሚገለፁ መረጃዎች የሚተነተኑበት ሲሆን ዓይነታዊ ምርምር ደግሞ ትረካዊ ወይም ገለፃዊ መንገድን ተከትሎ በማብራራት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ተንትኖ የጥናቱ ውጤት ላንባቢ የሚቀርብበት ነው (ያለው 2001)፡፡ በዚህ ጥናትም በፅሁፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ለመተንተን መጠናዊ ምርምር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቁጥርና በመተኛ የተቀመጡ መረጃዎች ፣በክፍል ምልከታ፣በቪድዮ ቀረፃ እና በቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ለማብራራት ዓይነታዊ ምርምር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## 3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት የተካሄደው በመቀሌ ከተማ በ2004 ዓመተ ምህረት በመማር ማስተማር ላይ በሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ሲሆን መረጃ በመስጠት የተሳተፉትም መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.3.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው አካባቢ በትግራይ ክልል የሚገኘው መቀሌ ከተማ ነው። ትግራይ ክልልና ከትግራይ ክልል ደግሞ መቀሌ ከተማን የተመረጡት ዓላማ ተኮር (Purposive) የናሙና ዘዴ በመጠቀም ነው። ያለው (2001) እንደሚገልፁት ይህ ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ሲሆን እነዚህ ዓይነት ተሳታፊዎች ብመርጥ አስፈላጊውን መረጃ አገኛለሁ ብሎ በማመን የሚመርጥበት የናሙና ዓይነት ነው። ስለሆነም አጥኚዋ በዓላማ ተኮር መቀሌን የመረጠችበት ምክንያት መቀሌ ከተማ የተማረችበትና በመምህርነት ያገለገለችበት አካባቢ በመሆኑ ነው። ስለዚህ አጥኚዋ በአከባቢው የሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች በቂ ትብብር በማድረግ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጡኛል ብላ በማመንዋ መቀሌን መርጣለች።

### 3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በትግይ ክልል መቀሌ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው። በመቀሌ ከተማ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከነዚህ አራት ትምህርት ቤቶች ሶስቱ ዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ የሚማሩባችው ሲሆኑ አንዱ ትምህርት ቤት ደግሞ የመሰናዶ (Preparatory) ወይም አስራ አንደኛ እና አስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ የሚማሩበት ነው። ስለዚህ ይህ ብቸኛ ትምህርት ቤት በጥናቱ ውስጥ አልተካተተም። ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ሁለቱ በናሙናነት የተወሰዱት ዕጣ የማወጣት (Lottory System) የናሙና ዘዴን በመጠቀም ነው። የመረጣ ሂደቱን በተመለከተ የትምህርት ቤቶቹ ስም እኩል መጠንና ቅርፅ ባላቸው ቁርጥራጭ ወረቀቶች ላይ ፅፎ በመጠቅለልና ዕጣ በማውጣት ዕጣው የወጣላቸው ሁለት (67%) ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ተወስደዋል።

### 3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በናሙናነት የተወሰዱ ትምህርት ቤቶች ዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች የሚማሩባቸው ናቸው። ይሁን እንጂ አስረኛ ክፍል ለመልቀቂያ ፈተና በመዘጋጀት ላይ ስለሚያተኩሩ አስፈላጊው መረጃ ይገኛል ተብሎ አልተገመተም። በመሆኑም ይህን

የክፍል ደረጃ መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ተተኳሪዎች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ እነዚህ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ዘዴ ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ሲሆን የክፍል ደረጃው የተመረጠበት ምክንያትም ለጥናቱ አስፈላጊውን መረጃ ያስገኛል ተብሎ ስለተገመተ ነው፡፡ ምክንያቱም ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ካሉበት የክፍል ደረጃ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ የሚሸጋገሩት ክፍል ውስጥ ተምረው፤የተማሩትን ተፈትነው ባስገኙት ውጤት ስለሆነ በመማር ማስተማር ሂደት ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በተሻለ ይከታተላሉ፡፡

## 3.3.4 የመምህንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.3.4.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በተመረጡት ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር አራት አራት በድምር ስምንት ነው፡፡ በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሳተፉ መምህራን ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች አራት ሲሆኑ ዕጣ የማወጣት ዘዴ በመጠቀም ከሁለቱ ትምህርት ቤቶች ሁለት ሁለት በድምሩ አራት (50%) ተመርጠዋል፡፡ የመረጣ ሂደቱን በተመለከተ የመምህሮቹን ስም እኩል መጠንና ቅርፅ ባላቸው ቁርጥራጭ ወረቀቶች ላይ ፅፎ በመጠቅለልና ዕጣ በማውጣት ዕጣው የወጣላቸው አራት መምህራን በናሙናነት ተወስደዋል፡፡

### 3.3.4.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ብዛት በሐወልቲ ሁለተኛ ደረጃ አስራ ስድስት በዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አስራ ሁለት በድምሩ ሀያ ስምንት ነው፡፡ ከእነዚህ ሀያ ስምንት ምድቦችም ለምልከታ የተመረጡት መምህራን የሚገቡባቸው ሰባት ምድቦች በናሙናነት ተወስደዋል፡፡ አወሳሰዱም በሐወልቲ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ከሚገቡባቸው ስምንት ምድቦች አራቱን እና በዓይደር ደግሞ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ከሚገቡባቸው ስድስት ምድቦች ሶስቱን በዕጣ በመምረጥ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለምልከታ በተመረጡ ምድቦች ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ከሐወልቲ ከሁለት መቶ ሰባት፤ አርባ አራት ተማሪዎች እና ከዓይደር ደግሞ ከአንድ መቶ ሀምሳ ሶስት፤ ሰላሳ ሶስት ተማሪዎች በድምሩ ሰባ ሰባት ተማሪዎች

በብድግ ብድግ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በናሙናነት በመውሰድ የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። ከሐወልቲ በናሙናነት ከተወሰዱት አርባ አራት ተማሪዎች ሀያ አንድ ሴት ተማሪዎች ሲሆኑ ሀያ ሶስቱ ደግሞ ወንድ ተማሪዎች ናቸው። በተመሳሳይ ከዓይደር በናሙናነት ከተወሰዱ ሰላሳ ሶስት ተማሪዎች አስራ ሰባት ሴት ተማሪዎች ሲሆኑ አስራ ስድስት ደግሞ ወንድ ተማሪዎች ናቸው።

**ሰንጠረዥ -1 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ከፆታና ብዛት አንፃር**

| ተ.ቁ | ምድብ | ወንድ | ሴት | ድምር | የትምህርት ቤት ስም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | G | 23 | 27 | 50 | ሐወልቲ ሁ/ደ/ት/ቤት |
| 2. | H | 27 | 27 | 54 | |
| 3. | E | 19 | 30 | 49 | |
| 4. | L | 26 | 28 | 54 | |
| 5. | A | 26 | 29 | 55 | ዓይደር ሁ/ደ/ት/ቤት |
| 6. | C | 23 | 27 | 50 | |
| 7. | K | 21 | 27 | 48 | |
| ድምር | | 165 | 195 | 360 | |

ከሰንጠረዥ-1 መገንዘብ እንደሚቻለው በናሙናነት የተወሰዱ ምድቦች ሰባት ናቸው። በሰባቱም ምድቦች የሚማሩ ወንድ ተማሪዎች ብዛት አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሲሆን የሴት ተማሪዎች ብዛት ደግሞ አንድ መቶ ዘጠና አምስት ነው። ይህም በየምድቡ የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ብዛት ከወንዶች የበለጠ እንደሆነ ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪ የሴት ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት ከወንዶች ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት የበለጠ እንደሆነ መረዳት ተችሏል። በአጠቃላይ በሰባቱም ቡድኖች የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት ሶስት መቶ ስላሳ ነው።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ

ጥናቱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎችን ተጠቀሟል።

### 3.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

ምልከታ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመገንዘብ መረጃ የሚሰበስብበት ነው (ያለው 2001)፡፡ በመሆኑም የዚህን ምልከታ ዓላማ ለማሳካት መከታተያ ቅፅ (Checklist) ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ለምልከታው የተዘጋጀው መከታተያ ቅፅ በአማካሪና በሶስት የአማርኛ ቋንቋ ዶክትሬት ተማሪዎች አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ የተሰጠውን አስተያየት በማስተካከል በስራ ላይ ውሏል፡፡ የመከታተያ ቅፁ ያተኮረው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን በመማር ማስተማር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር እና በክፍል ውስጥ አደረጃጀት ላይ ነው፡፡

ምልከታው የተካሄደው በናሙናነት በተመረጡ መምህራንና ምድቦች ላይ ሲሆን እያንዳንዱ ምድብ ከመጀመሪያ ዙር ውጪ ሁለት ሁለት ክፍለ ጊዜያት በድምር አስራ አራት ክፍለ ጊዜያት በመግባት ምልከታ ተካሂዷል፡፡ ምልከታው የተካሄደው ከታህሳስ 11- ጥር 13 /2004 ዓ.ም ባሉት አራት ተከታታይ ሳምንቶች ሲሆን በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜያት ወይም ለአንድ ሰዓት ከሀያ ደቂቃ (01፡20) ነው፡፡ (ለተጨማሪ መረጃ አባሪ ‹‹1››ን ይመልከቱ)

በምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር የቪድዮ ቀረፃ ተካሂዷል፡፡ የቀረፃውን ሂደት በተመለከተ መጀመሪያ የጥናቱን አላማ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በማስረዳትና መምህራኑም ለተማሪዎች እንዲያስረዱ በመንገር የመጀመሪያው ዙር (የሙከራ) ቀረፃ ተካሂዷል፡፡ በመቀጠልም ለአንድ ምድብ ለሁለት ክፍለ ጊዜያት ያህል ቀረፃ ተካሂዷል፡፡ በድምሩም በሰባቱ ምድቦች የሙከራ ቀረፃውን ሳያካትት ለአስራ አራት ክፍለ ጊዜያት ያህል የቪድዮ ቀረፃ በማካሄድ እና እንደ አስፈላጊነቱም ፎቶ ግራፍ በማንሳት መረጃውን የተጠናከረ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ወቅትም አጥኚዋ እና ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ምሩቃን ሰዎች የመከታተያ ቅፁ ሲሞሉ ሌሎች ሁለት ሰዎች ደግሞ በመተጋገዝ የቪድዮ ቀረፃውን አካሂደዋል፡፡ በመጨረሻም በቪድዮ ቀረፃው የተገኙትን መረጃዎች ወደ ፅሁፍ ተቀይረው መምህር-1፣መምህር-2 ወዘተ. በማለት በትንተናው ተካተዋል፡፡

### 3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ

በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የክፍል ውስጥ አደረጃጀትን በተመለከተ ሀያ አራት ጥያቄዎች በማዘጋጀት በናሙናነት የተመረጡ ሰባ ሰባት ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉም ዝግ ጥያቄዎች ሲሆኑ ተማሪዎች እነዚህን ጥያቄዎች አንብበው ከተሰጡት አማራጮች አንዱን ብቻ በመምረጥ መልስ መስጠት እንዲችሉ (5-በጣም እስማማለሁ፣ 4-እስማማለሁ፣ 3-ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 2-አልስማማምና 1-ፈፅሞ-አልስማማም) የሚሉት አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ በአማካሪና በሶስት የአማርኛ ቋንቋ ዶክትሬት ተማሪዎች አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፅሁፍ መጠይቁ የተፃፈበት ቋንቋ ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ሊገባቸው በሚችል መልኩ የተዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ በአቅራቢያው ከሚገኘው ትምህርት ቤት የተወሰኑ ተማሪዎች መጀመሪያ እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች የሰጡትን አስተያየት በመቀበል እና እርማት በማድረግ ተስተካክሎ በብድግ ብድግ የናሙና አመራጥ ዘዴ የተመረጡት ተማሪዎች እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ ተማሪዎች መጠይቁን በሚሞሉበት ወቅትም አጥኚዋ በትምህርት ቤቱ በአካል በመገኘትና አስፈላጊውን መግለጫ በመስጠት እንዲሞሉት አድርጋለች፡፡ በዚህ መልኩ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ሁሉም በሰንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ መልክ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የእያንዳንዱ ሰንጠረዥ መረጃም ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ (ለተጨማሪ መረጃ አባሪ ‹‹16›› ን ይመልከቱ)

### 3.4.3 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ መጠይቁን የሚያካሂደው ሰው መላሹ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ጥያቄዎችን ለመላሹ በማቅረብና በማብራራት፣ መላሹ ደግሞ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሱን በቃል የሚሰጥበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ጠያቂው መላሹ የሚሰጠውን ምላሽ የተቻለውን ያህል በሚገባ ለመያዝ ጥረት ያደርጋል (ያለው 2001)፡፡ በዚህ መሰረትም ከጥናቱ ተተኳሪዎች ውስጥ በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ በናሙናነት የተመረጡ አራት መምህራን ናቸው፡፡ ለነዚህ መምህራን አስር ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ መጠይቁ የተካሄደ ሲሆን የጥያቄዎቹ ይዘትም መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት፣ ዘዴውን ተግባራዊ ሲያደርጉ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና ምን

እንደሚመስል፣ ዘዴውን ሲተገብሩ የሚታዩት አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ምን ምን እንደሆኑ እና ስለ ዘዴው የወሰዱትን ስልጠና ወዘተ. በተመለከተ መረጃ የሚሰጡባቸው ናቸው፡፡

ቃለ መጠይቁ ለተጠያቂዎች ከመቅረቡ በፊት በአማካሪ እና በሶስት የአማርኛ ቋንቋ ዶክትሬት ተማሪዎች አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ ለተሰጠው አስተያየትም ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ መጠይቁ በሐወልቲ ሁ/ደ/ት/ቤት ታህሳስ 05/2004 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን በዓይደር ሁ/ደ/ት/ቤት ደግሞ ታህሳስ 08/2004 ዓ.ም ትምህርት ቤቶቹ ድረስ በመሄድ ከያንዳንዱ መምህር ጋር ከሀምሳ ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት ከአስር ደቂቃ ያህል ተካሂዷል፡፡ የተደረገው ቃለ መጠይቅም በመቅረፀ ድምፅ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ የቃለ መጠይቁ ምልልስ መምህር "ሀ" ፣መምህር "ለ" ወዘተ. በማለት ወደ ፅሁፍ ተቀይሮ ቀርቧል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በተከታታይ ከተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ፣የቪድዮ ቀረፃ፣ የፅሁፍ መጠይቅ እና የቃል መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በዓይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በምልከታ፣በቪድዮ ቀረፃ፣ በፅሁፍና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በየይዘታቸው ተመሳሳይነት ተቀናብረው የሚካተቱበት ነው፡፡ ስለዚህ በነዚህ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች መጀመሪያ ከክፍል ውስጥ የተገኙ መረጃዎች፣በመቀጠል ከቪድዮ ቀረፃ፣ ከዚያም በፅሁፍና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት የተለያዩ ምሁራን ከገለፁዋቸው ሀሳቦች ጋር በማያያዝ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት

Nunan (1988) እንደገለፁት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች መምህራን የሚነግሩዋቸውን ከማዳመጥ አልፈው በራሳቸው መስራት የሚችሉበትን መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ማዕከል ሆነው ቋንቋን እንዲተገብሩት በማድረግ አይረሴ እውቀት ይዘው እንዲወጡ ይረዳል፡፡ በዚህ መሰረትም መምህራን ሰዋስውን በማስተማር ሂደት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ለመፈተሽ በተዘጋጀው የምልከታ መከታተያ ቅፅ (Check list) የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ-2 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ከክፍል ምልከታ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | የተተኮረባቸው ነጥቦች | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በሰዋስው መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ ተደርጓል | 14 | - | |
| 2. | የክፍል ስራ ተሰጥቷል | 7 | 7 | |
| 3. | በሰዋስው መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በጥንድ እንዲወያዩ ተደርጓል | - | 14 | |
| 4. | በትምህርቱ ጣልቃ ጥያቄ የመጠየቅና የመመለስ ዘዴ ተተግብሯል | 14 | - | |
| 5. | መምህሩ ዘዴዎችን በማቀላቀል ተጠቅመዋል | 14 | - | |
| 6. | በክፍለ ጊዜው በብዛት ሲሳተፉ የሚታዩት ተማሪዎች ናቸው | 14 | - | |
| 7. | በክፍለ ጊዜው በብዛት ሲሳተፉ የሚታዩት መምህራን ናቸው | - | 14 | |

የቡድን ውይይት በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ስር ከሚካተቱት ዘዴዎች አንድ ሲሆን ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለመግለፅ፣ የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ እና እርስ በርስ ከሚደረገው የሀሳብ ልውውጥ አዲስ እውቀት የሚያገኙበት ነው (ICDR 1999)፡፡ ከዚህም በመነሳት መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለመከታተል በተዘጋጀው የምልከታ መከታተያ ቅፅ መሰረት በአስራ አራቱ ክፍል ጊዜያት ተማሪዎች በቡድን ሲወያዩ ተስተውሏል፡፡ ከአስራ አራቱ ምልከታዎች በሐወልቲ ሁ/ደ/ት/ቤት ከተደረጉ ስምንት ምልከታዎች በአራቱ የክፍል ስራ የተሰጠ ሲሆን በዓይደር ሁ/ደ/ት/ቤት ደግሞ ከተደረጉ ስድስት ምልከታዎች በሶስቱ በድምሩ በሰባቱ ክፍለ ጊዜያት የክፍል ስራ ተሰጥቷል፡፡

Doff (1988) እንደገለፁት የጥንድ ስራ ተማሪዎች ያልተሟላ ሀሳብ ሲጨርሱ፣ በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲወያዩ፣በጣም አነስተኛ የሆነ ስራ ሲሰሩ የሚደራጁት ሲሆን የተሰጣቸውን ተግባር ከሁለት እስከ ሶስት ደቂቃዎች ባሉት ጊዜያት ከተወያዩ በኋላ ከጥንድ ውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስተላልፉ የሚደረግበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በቡድን እየተወያዩ እንዲሰሩ ካልሆነ በስተቀር በጥንድ ሲሰሩ አልታየም፡፡

ጥያቄና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት እንዲያካፍሉ፣ በተጠየቀው ጥያቄ እንዲመራመሩ፣ የመግለፅ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ እና መምህራን ደግሞ የክፍለ ጊዜው ዓላማ ከግብ መድረሱንና አለመድረሱን እንዲያረጋግጡ ይጠቅማል (Getachew 2001)፡፡ በዚህ መሰረትም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ በብዛት የቡድን ውይይትን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሲሆን በአስራ አራቱ ክፍለ ጊዜያት ጥያቄና መልስ ዘዴ ተግባራዊ ያላደረጉበት ክፍለ ጊዜ የለም፡፡ በመሆኑም መምህራኑ በአንድ ክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ተማሪዎችን ስለ ርእሰ ጉዳዩ የሚያውቁትን እንዲናገሩ በማድረግ፣ የቡድን ውይይት በማሰራት፣ የተለያዩ ጥያቄዎች በቃል በመጠየቅና ተማሪዎችም እንዲመልሱ በማድረግ ስለሚያስተምሩ በሁሉም ክፍለ ጊዜያት ዘዴዎችን በማቀላቀል ሲያስተምሩ ተስተውሏል፡፡ በዚህ ወቅትም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በሁሉም ክፍለ ጊዜያት የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑና በብዛት ሲሳተፉ የሚታዩት ተማሪዎች ናቸው፡፡

ከላይ በምልከታ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ፣ጥያቄ በመጠየቅና በመመለስ እንዲሳተፉ፣የክፍል ስራ እንዲሰሩ የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህም መምህራኑ ዘዴዎችን አቀላቅለው በመጠቀም ሰዋስውን እንደሚያስተምሩ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ መምህራኑ ሰዋስውን በማስተማር በተደጋጋሚ ተግባራዊ የሚያደርጉዋቸው ዘዴዎች የቡድን ውይይት፣ጥያቄና መልስ እና የክፍል ስራ ሲሆኑ በሁሉም ምልከታዎች የተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ጎልቶ ታይቷል፡፡ ከዚህም መምህራኑ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በተደረጉት አስራ አራት ምልከታዎች የጥንድ ስራ ተግባራዊ የተደረገበት ክፍል ጊዜ አልነበረም፡፡ ከዚህ በመቀጠል መምህራኑ ስዋስዋዊ ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ

የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለመፈተሽ ከተደረገው የቪድዮ ቀረፃ የተገኘውን መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ- G1

የመምህሩ ስም- መምህር-1

መምህርቷ ወደ ክፍል ገብተው ሰላምታ ከሰጡ ቡኋላ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው የዕለቱን ትምህርት ርእስና ቀን ፃፉ፡፡ ከዚያም ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ ምን እንደተማሩ ተማሪዎቻቸውን ጠየቁ:: ተማሪዎችም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን በማስታወስ መለሱ፡፡ ቀጥለውም መምህርቷ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ **አብዝር ምዕላዶችን** በመጨመር **ቃላት ማብዛት** መሆኑን በማስተዋወቅ ተማሪዎች በዚህ ዙሪያ የሚያወቁትን እንዲናገሩ እድል ሰጡ፡፡ በማስከተልም "የአማርኛ ቁጥሮች በስንት ይከፈላሉ?፣ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር ለመቀየር የምንጠቀምበት ስልትስ ምንድን ነው?" የሚሉትን ሁለት ጥያቄዎች በመጠየቅ ለአምስት ደቂቃ ያህል በየኔትወርካቸው* እንዲወያዩ አደረጉ፡፡ የተሰጠውን ደቂቃ እንዳለቀም መምህርቷ የኔትወርኮቹን ስም በመጥራት የኔትወርኩ አባላት ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ጋበዙ፡፡ በመቀጠል መምህርቷ አራት ቃላት ጥቁር ሴሌዳ ፅፈው ለእያንዳንዱ ቃል የአማርኛ እና የግእዝ አብዝር ምዕላዶችን በመጨመር በአማርኛ እና በግዕዝ እንዴት እንደሚበዙ አስረዱ፡፡ ከዚያም መምህርቷ በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59-60 በ ‹‹ሀ›› ስር የሚገኙትን ቃላት ቀደም ብሎ በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት እየተወያዩ የክፍል ስራ እንዲሰሩ ተማሪዎቹን አዘዙ፡፡ (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹2›› ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት [i*]

ምድብ-E1

የመምህሩ ስም- መምህር-2

---

ኔትወርክ*፡- በተማሪዎች ውጤት መሰረት እና ተማሪዎች በቅርበት ከሚገናኙበት አንፃር በቡድን ማስተሳሰር፣ ማጣመድ (ማያያዝ) ማለት ነው፡፡ የአንድ ክፍል ተማሪዎች መጀመሪያ ሲገቡ በአንድ ቡድን ተደራጅተው አመቱን ሙሉ አብረው እንዲዘልቁ የሚደረግበት ነው፡፡ (አባሪ ‹‹17››).

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ቀንና የዕለቱን ትምህርት ርእስ ፃፉ፡፡ በመቀጠል "ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ያላቸውን ሰዋስዋዊ ስህተት በመለየት አስተካክላችሁ ፃፉ" የሚለውን ትዕዛዝ ተማሪዎች በቃል እንዲፅፉ አደረጉ፡፡ ከዚያም መምህሩ አራት ዓረፍተ ነገሮች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች እንዲፅፉ አዘዙ፡፡ ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩት ለማሳየትም መምህሩ አንደኛውን ተራ ቁጥር ወስደው አስረዱ፡፡ በመቀጠል የቀሩትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ መመሪያ ሰጡ፡፡ የተሰጠው ደቂቃ ካለቀ በኋላም ተማሪዎች ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ጋበዙ፡፡ ተማሪዎችም ከየኔትወርኩ እጃቸውን በማውጣት ለጥያቄዎቹ ምላሽ ሰጡ፡፡ የተማሪዎች ምላሽ እንዳበቃም መምህሩ የተማሪዎችን ምላሽ አጠናከሩ፡፡ ከዚያም መምህሩ ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን ጥያቄዎች የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ የተፈቀደላቸው ደቂቃ ካበቃ በኋላም መምህሩ ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በቃል ምላሽ እንዲሰጡ አደረጉ፡፡ በመቀጠል ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር እንዴት እንደሚቀየር በመማሪያ መፅሀፋቸው ያሉትን ምሳሌዎች እንዲመለከቱ አዘዙ፡፡ መምህሩ ተማሪዎች ምሳሌዎቹን መረዳታቸው ካረጋገጡ በኋላም በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-ነ›› ያሉትን ቃላት በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ መመሪያ ሰጡ፡፡ (ለዝርዝር ሀተታ **አባሪ ‹‹4››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ አንድ- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-A1

የመምህሩ ስም- መምህር-3

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ለተማሪዎች ሰላምታ በማቅርብ ቁጥር ሰሌዳውን አፅድተው ቀን በመፃፍ በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፉ ገፅ 46 የሚገኘውን "ከግስ አርእስት መመሰረት" የሚለውን ትዕዛዝ በማንበብ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ቀጥለውም "ከግስ አርእስት እንዴት ይመሰረታል? ማለት አዳዲስ ቃላት እንዴት መመሰረት ይቻላል?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት መልስ ሰጡ፡፡ አስከትለውም መምህሩ ተማሪዎችን ምሳሌ እንዲሰጡ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ምሳሌ ሰጡ፡፡ በመቀጠል መምህሩ በተማሪዎች

መማሪያ መፅሀፍ ገፅ 45 በ ሀ፣ለ፣ሐ እና መ ስር የሚገኙትን ቃላት ተማሪዎች ከግስ ወደ አርእስት እንዲቀይሩ የክፍል ስራ ሰጡ፡፡ ከአራት ደቂቃ በኂላም ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን እያወጡ ጥያቄዎችን በቃል መለሱ፡፡ ከዚያም መምህሩ የስምና የግስ ገላጭ ምንነትን በምሳሌ አስረዱ፡፡ በመቀጠል በተማሪዎቹ መማሪያ መፅሀፍ ገፅ 46 ከ ‹‹ሀ-ረ›› ያሉትን የተሰመረባቸው ቃላት የስም እና የግስ ገላጭ በማለት እንዲለዩ የክፍል ስራ ሰጡ፡፡ (ለተጨማሪ ማብራሪያ **አባሪ ‹‹6››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ አንድ- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-K1

የመምህሩ ስም- መምህር-4

መምህርቷ ወደ ክፍል እንደገቡ አንድ ተማሪ ዳስተሩን ተቀብሎ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዳላቸው፡፡ በመቀጠል መምህርቷ የተፀዳውን ጥቁር ሰሌዳ ለሁለት በመክፈል የዕለቱን ትምህርት ርእስና ቀን ፃፉ፡፡ ቀጥለውም ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ ምን እንደተማሩ ተማሪዎቹን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት መልስ ሰጡ፡፡ በመቀጠል መምህርቷ ስላለፈው ትምህርታቸው አጭር ገለፃ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ሰዋስው መሆኑን አስተዋወቁ፡፡ ከዚያም “ምሳሌውን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ነጠላ ቁጥር ቃላት ወደ ብዙ ቁጥር ቀይሩ” የሚለውን ትእዛዝ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ቀጥለውም ቃላት ከነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር እንዴት መቀየር እንደሚቻል ምሳሌዎችን በመውሰድ አስረዱ፡፡ ምሳሌው ግልፅ መሆኑን ካረጋገጡ በኂላ መምህሩ በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-ከ›› ያሉትን ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች እየወጡ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም እየወጡ ሰሩ፡፡ ከዚያም በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ 59 ላይ “የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በፍቺ የሚቀረቡ ሌሎች ቃላትና ሀረጋት ተኩ” የሚለውን ትዕዛዝ በማንበብ በስሩ ከሚገኙ ሁለት ምሳሌዎች በመውሰድ አስረዱ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች መረዳታቸውን ጠየቁና ተማሪዎች መረዳታቸውን ሲገልፁ የቀሩትን በየኔትወርካቸው በመወያየት እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ (ለተጨማሪ መረጃ **አባሪ ‹‹8››ን ይመልከቱ**)

ከቀረበው የቪድዮ ቀረፃ መገንዘብ እንደሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍለ ጊዜው የቅድመ ትምህርት ጥያቄዎችን በማቅረብ የተማሪዎችን ቅድመ እውቀት በመፈተሽ ፣የቡድን ውይይት ፣የክፍል ስራ እና ጥያቄና መልስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ይህም መምህራኑ ሰዋስውን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለማረጋገጥ በፅሁፍ መጠይቅ ላይ ለተማሪዎች ከቀረቡ ዝግ ጥያቄዎች የተገኙትን ምላሾች እንመለከታለን፡፡[†]

**ሰንጠረዥ-3 መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለተማሪዎች ከቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተሰጠ የነጥብ ደረጃ በቁጥርና በመቶኛ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5* | | 4* | | 3* | | 2* | | 1* | | ያልተመለሱ |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | |
| 1. | የሰዋስው ጥያቄዎች በግል እንድንሰራ ይደረጋል | 25 | 32 | 34 | 44 | 9 | 12 | 3 | 4 | 6 | 8 | |
| 2. | የሰዋስው ጥያቄዎችን በቡድን እንድንሰራ ይደረጋል | 21 | 27 | 48 | 62 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | |
| 3. | በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በጥንድ እንድንሰራ ይደረጋል | 49 | 64 | 19 | 24 | 7 | 9 | 2 | 3 | - | - | |
| 4. | የሰዋስው ይዘቶች በክፍል ስራ መልክ አንድንሰራ ይደረጋል | 32 | 42 | 32 | 42 | 8 | 10 | 4 | 5 | 1 | 1 | |
| 5. | የሰዋስው ትምህርት ስንማር ተማሪን እሚያሳትፉጥያቄዎች በቃልም ሆነ በፅሁፍ መልክ ይቀርባሉ | 33 | 43 | 29 | 38 | 13 | 17 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 6. | ሰዋስውን ስንማር አብዛኛውን ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል | 30 | 39 | 32 | 42 | 5 | 6 | 4 | 5 | 6 | 8 | |

ከላይ በሰንጠረዥ-4 ተራ ቁ.1 ተማሪዎች በግላቸው እንዲሰሩ የማድረግ ሁኔታን በተመለከተ ለቀረበው ሀሳብ 25(32%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ ፣34(44%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 9(12%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 3(4%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 6(8%) ያህሉ

[†] 5.* በጣም እስማማለሁ 4.* እስማማለሁ 3.* ለመወሰን ያስቸግረናል 2.* አልስማማም
1.* ፈፅሞ አልስማማም

ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተማሪዎቹ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው 59(76%) ያህሉ ተማሪዎች በክፍልም ሆነ በቤት ስራ መልክ በግላቸው እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑን እንደሚስማሙበት፣ 12(16%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 9(12%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ የግል ስራ መስጠቱንና አለመስጠቱን ለመወሰን እደሚቸገሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም ተማሪዎች ሰዋስውን ሲማሩ የግል ስራ እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያጠናክራል፡፡

በሰንጠረዥ-4 ተራ ቁ.2 ተማሪዎች ሰዋስውን ሲማሩ በቡድን እንዲሰሩ መደረጉን ለመፈተሽ በቀረበው ሀሳብ መሰረት 21(27%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣48(62%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 3(4%)ለመወሰን ያስቸግረኛል፣3(4%) የሚሆኑ ተማሪዎች አልስማማምና 2(3%) ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከተማሪዎቹ መልስ መገንዘብ እንደሚቻለው 69(89%) የሚሆኑት ተማሪዎች የቡድን ስራ እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑን እንደሚስማሙበት፣ 5(7%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 3(4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንዳስቸገራቸው ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ሰዋስውን ሲማሩ በቡድን እንዲሰሩ እንደሚደረግ ያስረዳል፡፡

በሰንጠረዥ-4 ተራ ቁ.3 ተማሪዎች በጥንድ እንዲሰሩ መደረጋቸውን በተመለከተ 49(64%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 19(24%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 7(9%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣2(3%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማም በማለት የመለሱ ሲሆን ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ አልተሰጠም፡፡ ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው 68(88%) ያህሉ ተማሪዎች በጥንድ እንዲሰሩ እየተደረገ መሆኑን እንደሚስማሙት፣2(3%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 7(9%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በጥንድ እንዲሰሩ በማድረግ የጥንድ ስራ ተግባራዊ እንደሚደረግ ያስገነዝባል፡፡

በሰንጠረዥ-4 ተራ ቁ.4 ተማሪዎች የክፍል ስራ እንዲሰሩ መደረጉን እንዲያረጋግጡ ለቀረበላቸው ሀሳብ 32(42%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣32(42%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 8(10%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 4(5%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 1(1%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም 64(84%) የሚሆኑት ተማሪዎች በቀረበው ሀሳብ እንደሚስማሙበት፣ 5(6%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 8(10%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ከዚህ መረጃ ተማሪዎች የሰዋስው ይዘቶችን ሲማሩ የክፍል ስራ እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በሰንጠረዥ-4 ተራ ቁ.5 ተማሪዎች የሰዋስው ይዘቶችን በሚማሩበት ወቅት እነሱን እሚያሳትፉ ጥያቄዎች በቃል ወይም በፅሁፍ መቅረባቸውን በተመለከተ 33(43%) ያህል ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣29(38%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 13(17%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣1(1%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማምና 1(1%) ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተማሪዎቹ መልስ እንደሚስተዋለው 62(81%) ያህሉ ተማሪዎች የሚያሳትፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ይቀርባሉ የሚለውን ሀሳብ እደሚስማሙበት፣ 2(2%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 13(17%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር ሂደት ተማሪዎችን እሚያሳትፉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆናቸው የተገኘውን መረጃ ያስገነዝባል፡፡

በሰንጠረዥ-4 ተራ ቁ.6 በሰዋስው ትምህርት አብዛኛውን ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል ለሚለው ሀሳብ 30(39%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣32(42%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 5(6%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን ያስቸግረኛል በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 4(5%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 6(8%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተማሪዎቹ መልስ ማስተዋል እንደሚቻለው 62(81%) የሚሆኑት ተማሪዎች ዘዴው

ተግባራዊ ይደረጋል የሚለውን ሀሳብ እደሚስማሙበት፣ 10(13%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 5(6%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ነው። ይህም መምህራኑ የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆናቸውን ያመለክታል።

ተማሪዎች ከሰጡት አስተያየት መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ ተማሪዎች በግል (የክፍል ስራ)፣በቡድን፣በጥንድ፣ እንዲሰሩ የሚያደርጉ መሆናቸውን፣ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በፅሁፍና በቃል እንደሚያቀርቡ እና ሰዋስውን ሲያስተምሩ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ ዘዴዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል። ከዚህም ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምዳቸው ከፍተኛ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በሶስቱም መሳሪያዎች አማካይነት የተገኘው መረጃ ተመሳሳይ ሲሆን ይህም መምህራኑ ሰዋስውን በማስተማር ሂደት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆናቸውን ያሳያል። ነገር ግን ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ተማሪዎች በጥንድ እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑን ቢያሳይም በተደረገው የክፍል ምልከታና ከቪድዮ ቀረፃ በተገኘው መረጃ ግን በጥንድ ሲሰሩ አልታየም።

መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለመፈተሽ አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አለ? ምን?፣ሰዋስውን ለማስተማር የሚመርጡት ዘዴ ምን ዓይነት ነው? ለምን? እና ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምድዎ ምን ያህል ነው? ተብለው በቃል ለተጠየቁ ጥያቄዎች መምህራኑ የሰጡዋቸው ምላሾች የሚከተለውን ይመስላል። በቃለ መጠይቁ ተራ ቁ. አንድ አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አለ? ምን? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራኑ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ሳይነጣጠሉ የሚማሩበትን ሁኔታ ስለሚፈጥር ፣በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ከማዳመጥ አልፎ ራሳቸው ትግበራ ውስጥ ገብተው ተጠያይቀው፣ ተነጋግረው፣ ተከራክረውና ሀሳባቸውን ተለዋውጠው ዘላቂ እውቀት እንዲጨብጡ ስለሚረዳ አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ ሙሉ በሙሉ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ገልፀዋል። (ለተጨማሪ ዝርዝር አባሪ ‹‹18››ን ይመልከቱ)

ስለዚህ መምህራኑ በሰጡት ምላሽ መሰረት አማርኛን ሲያስተምሩ ተግባራዊ ሚያደርጉት ዘዴ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ለማሰራት፣ ስለሚሰሩዋቸው ነገሮች ለማሰብና ከመረጃ አድማጭነት በተሻለ የችግር ፈቺነት ችሎታ እንዲያዳብሩ የሚረዳ የማስተማሪያ ዘዴ ነው (Tudor 1993)፡፡

በተራ ቁጥ.2 ሰዋስውን ለማስተማርስ አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡት ምን ዓይነት ዘዴ ነው? ለምን? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራኑ ሰዋስውን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት ዘዴ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎችን ማገዝና ጥሩ እውቀት ማስጨበጥ ከተፈለገ መምህር ከተማሪ የሆነ ነገር መጠበቅ አለበት፡፡ ተማሪዎች ሁሉ ጊዜ መምህርን የሚጠብቁ ከሆነ ግን መምህር አምላኪ በመሆን መምህሩ የሰጠውን መምህሩ ይመልሰዋል የሚል አመለካከት ስለሚኖራቸው የመምህር ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የመምህር ጥገኛ እንዳይሆኑ፣ ያላቸውን እውቀት እንዲያፈልቁ፣ እርስ በርሳቸው ሀሳብ በመለዋወጥ፣ በመመራመር፣ በመከራከርና ብዙ በማሰብ ሰዋስውን በሚገባ እንዲረዱት ለማድረግ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ዘዴውን እንደሚመርጡት ገልፀዋል፡፡ (ለተጨማሪ መረጃ **አባሪ ‹‹17››ን ይመልከቱ**) ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንድ መምህር ሲናገሩ፣

> *እንግዲህ ሰዋስውን ሳስተምር የምጠቀመው ዘዴ አብዛኛውን ጊዜ የተለመደውንና እስከ ቅርብ ጊዜ ሲተገበር የነበረውን ገለፃ ነበር፡፡ ይህም ለምሳሌ፣ ስለ ቃል ክፍሎች ለማስተማር ስም ማለት እንዲህ ማለት ነው ፣ቅፅል ማለት እንዲህ ማለት ነው እያሉ በመንገር ነበር፡፡ አሁን ግን የስም፣ የግስ፣ የቅፅል ወዘተ. ምንነት የሚነገረው በመምህር ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ተማሪዎቹ እየተወያዩ እንዲገልፁት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ሰዋስውን ሳስተምር አብዛኛውን ጊዜ ተማሪ አሳታፊ በሆነ መልኩ አስተምራለሁኝ፡፡ ይህ ዘዴ የመረጥኩበት ምክንያት ለምሳሌ፣ በሰዋስው ስር ከሚመደቡት የስምን ምንነት በተመለከተ ራሴ ገለፃ ብሰጥ ነገሩ በኔ ያልቃል፡፡ ተማሪዎች መረዳታቸውን እንኳ ማረጋገጥ አልችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ተማሪዎች የስምን ምንነት የሚያውቁት እኔ የነገርኳቸውን ብቻ ነው፡፡ ይህ*

*ደግሞ ስለ ስም ምንነት የሚኖራቸውን ዘላቂ እውቀት ከኔ ባገኙት ብቻ እንዲገደብ ያደርጋል። ይህ እንዳይሆን ግን ተማሪን የሚያሳትፍ ዘዴ (አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ) እመርጠዋለሁ።* **(አባሪ ‹‹19››ን ይመልከቱ)**

መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎችን በቂ የሰዋስው እውቀት ለማስጨበጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ እያደረጉ እንደሚገኙ ነው።

Harmer (1978) እንደገለፁት የሰዋስው ትምህርት የቋንቋውን ስርዓት በመንገር፣ በመተንተንና በማጥናት ብቻ የሚዳብር ሳይሆን ምልልሶችን አዘጋጅቶ ተማሪዎችን በማሳተፍ፣ በይዘቶቹ ተማሪዎች እንደዲወያዩ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ፣እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱ እና የራሳቸው ሚና እንዲጫወቱ በሚያደርግ መልኩ ማስተማርን የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም መምህራኑ ሰዋስውን በማስተማር ሂደት ዘዴውን ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት ለመፈተሽ በተራ ቁ.3 ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምድዎ ምን ያህል ነው? የሚለውን ጥያቄ  ቀርቦላቸው እያንዳንዱ መምህር የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተዋል።

*መምህር-ሀ*

> በዚህ ላይ በጣም በጣም እሰራበታሁ። ምክንያቱም ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ጥሩ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ መጀመሪያ በሚማሩዋቸው ይዘቶች ተሳታፊ መሆን አለባቸው። ስለዚህ ሰዋስውን ሳስተምርም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት ተማሪዎቹ የጥያቄዎቹ ምላሽ ፈልገው እንዲያገኙ አደርጋለሁኝ። ለምሳሌ፣የሚሰጡዋቸው ጥያቄዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትና የተሳቢ አለመስማማት፣የቁጥር አለመስማማት፣ የፆታ አለመስማማት ወዘተ. መለየት ሊሆን ይችላል። በዚህ ወቅት ችግሩን በመለየት ነቅሰው የሚያወጡት እርስ በርስ በመወያየት፣ በመከራከርና መፍትሄ በመፈለግ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ጥሩ የሰዋስው እውቀት ለማስጨበጥ በይዘቶቹ ላይ ራሳቸውን ማሳተፍ አስፈላጊ ስለሆነ ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምዱ ከፍተኛ ነው። **(አባሪ ‹‹17››ን ይመልከቱ)**

መምህር-ለ

ቀደም ብለን እንደተነጋገርነው ሰዋስው ህግ (መመሪያ) ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ተናጋሪና ፀሀፊ እንደሆኑ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጥረት ደግሞ ለተማሪዎች መንገር ሳይሆን በንግግሩ ላይ ተማሪዎችን ተናጋሪ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ እኔም ይህን ዓላማ ለማሳካት እንዲሰራ የሚፈለገውን ስራ አብዛኛውን ጊዜ ለተማሪዎች በመስጠት እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ ከውይይቱ ያገኙትን ውጤት እንዲያንፀባርቁ በማድረግና በማበረታታት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ስለማስተምር ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ እጠቀምበታለሁ፡፡ **(አባሪ ‹‹18››ን ይመልከቱ)**

መምህር-ሐ

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ይህ ዘዴ ተግባራዊ መደረግ አለበት ከተባለበት ወቅት ጀምሮ ዘዴውን የመጠቀም ልምዴ ከፍተኛ ነው ማለት እችላለሁኝ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተቀመጡበት ኔትወርክ መሰረት እንዲሰሩ እያደረግኩኝ አገኛለሁ፡፡ **(አባሪ ‹‹19››ን ይመልከቱ)**

መምህር-መ

ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁ፡፡ አልፎ አልፎ ጊዜው እሚሻማብኝ ከሆነ ደግሞ በቃል ጥያቄና መልስ እንዲሸፈን አደርጋለሁ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን ተማሪዎች እንዲወያዩ ከማድረግ አልፎ እየወጡ እንዲሰሩ በማድረግ ነው ሰዋስውን እማስተምረው፡፡ ስለዚህ በከፍተኛ ደረጃ እጠቀማለሁ፡፡ **(አባሪ ‹‹20››ን ይመልከቱ)**

በአጠቃላይ በምልከታና በቪድዮ ቀረፃ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ሲያስተምሩ ተማሪዎች በቡድን በማሰራት፣የክፍል ስራ በግል በመስጠት፣ተማሪዎች እንዲጠይቁና እንዲመልሱ በማድረግ፣ ተማሪዎች በብዛት የሚሳተፉበትን ዕድል በመፍጠር፣ዘዴዎችን አቀላቅለው በመጠቀም ያስተምራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከፅሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት ከ77 ተማሪዎች 62 (81%) ያህሉ ተማሪዎች ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት

መምህራኑ የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ዘዴ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን አረጋግጠዋል። እንዲሁም ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ሰዋስውን ለማስተማር ሙሉ በሙሉ የሚጠቀሙት ዘዴ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ ገልፀዋል። ከነዚህ መረጃዎችም መምህራኑ ዘዴውን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ ከክፍል ምልከታና ከቪድዮ ቀረፃ በተገኙ መረጃዎች መሰረት መምህራኑ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ከሚባሉት ዘዴዎች በተደጋጋሚ የሚተገብሩዋቸው የቡድን ውይይት፣ጥያቄና መልስ፣የግል (የክፍል) ስራ ናቸው። ይህም በተወሰኑ ዘዴዎች ላይ መገደባቸውን ያመለክታል። እንዲሁም መምህራኑ ተማሪዎች በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ ዙርያ ድክመት ታይቶባቸዋል።

## 4.2 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራን ሚና

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በሚገባ ለመተግበር መምህራን ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ Tudor (1993) እንደገለፁት ይህ ዘዴ ተግባዊ ሲደረግ ተማሪዎችን ማነሳሳት፣ሀላፊነት እንዲወስዱ ማድረግ፣ በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት፣ ተማሪዎች እየተዝናኑ የሚማሩበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ተማሪዎች ሀሳብ በማፍለቅ የሚወያዩበት፣ የሚከራከሩበት፣ የሚጠይቁበትና የሚመልሱበት ዕድል መፍጠር እና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ መንገድ ማሳየት ከመምህራን የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው። በዚህ መሰረትም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት የሚኖራቸው ሚና ምን እንደሆነ ከክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ከቪድዮ ቀረፃ፣ከፅሁፍና ከቃል መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ-4 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራን ሚና በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | የተተኮረባቸው ነጥቦች | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ምርመራ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| 8. | መምህሩ የዕለቱ ትምህርት አስተዋውቀዋል | 14 | - | |
| 9. | መምህሩ የትምህርቱ ዓላማ አስተዋውቀዋል | 2 | 12 | |
| 10. | መምህሩ የተማሪዎችን የቅድመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎች አቅርበዋል | 8 | 6 | |
| 11. | መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የቡድን መሪ ፣ፀሀፊና ሌሎች አባላት በወጉ አደራጅተዋል | - | 14 | |
| 12. | መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን ሲወያዩ እየተዘዋወሩ በመከታተል እገዛ አድርገዋል | 14 | - | |
| 13. | ተማሪዎች ሀሳባቸው ካንፀባረቁ በኋላ መምህሩ ገለፃ በመስጠት የተማሪዎችን ሀሳብ አጠናክረዋል | 14 | - | |
| 14. | መምህሩ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተመፃህፍትና ከሌሎች ምንጮች አፈላልገው በቡድን የሚሰሩዋቸው ጥያቄዎች ሰጥተዋል | - | 14 | |
| 15. | መምህሩ በንቃት ለሚሳተፉ ተማሪዎች ማበረታቻ ቃላት ተጠቅመዋል | 8 | 6 | |
| 16. | መምህሩ ለተጠየቁት ጥያቄዎች በቂ(ትክክለኛ) ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል | 2 | 3 | በ3ቱ ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎችአልጠየቁም፣በ 6ቱ ደግሞ መምህራን ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ አላደረጉም |

ለአስራ አራት ክፍለ ጊዜያት በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ በሁሉም ምልከታዎች መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርእስ በማስተዋወቅ ጀምረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዓይደር ሁለተኛ ደረጃ በተደረጉት ስድስት ምልከታዎች ውስጥ በሁሉም ክፍለ ጊዜያት

የትምህርት ዓላማ በማስተዋወቅ ያልተጀመረ ሲሆን በሐወልቲ ሁለተኛ ደረጃ ግን ከስምንቱ ምልከታዎች በሁለቱ ክፍለ ጊዜያት የዕለቱ ትምህርት ዓላማ በማስተዋወቅ ሲጀመር ተስተውሏል፡፡

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመር በፊት የተማሪዎችን የቅድመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎች (የቅድመ ትምህርት) ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀመር ተማሪዎች የቅድመ እውቀታቸውን በማመንጨት ለተጠየቁት ጥያቄ በቅፅበት መልስ እንዲሰጡ ያስችላል (Bonwell and Eison 1991)፡፡ ከዚም በመነሳት በስምንቱ ምልከታዎች የቅድመ ትምህርት ጥያቄዎች በመጠየቅ የተጀመረ ሲሆን በስድስቱ ምልከታዎች ደግሞ መምህራን በራሳቸው አጭር ገለፃ በመስጠት የጀመሩ መሆናቸውን መመልከት ተችሏል፡፡ በሁሉም ምልከታዎች ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የአንድ ቡድን አባላት የየራሳቸውን ድርሻ እንዲይዙ፤መምህሩ ተማሪዎቹን ፀሐፊ፣ የቡድን መሪ ወዘተ. ብለው ሲከፋፍሉ አልታየም፡፡

ተማሪዎች በቡድንም ሲወያዩ መምህራን ስለሚሰራው ነገር ማብራሪያ ለመስጠት፣ የሚሰራና የሚረብሽ ተማሪ ለመለየት እና ሁሉም ተማሪዎች እየተሳተፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በየቡድኑ እየተዘዋወሩ በመከታተል ተማሪዎችን ሲያግዙ ታይቷል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት በመምህሮቻቸው ተሰጥቷቸው በቡድን ተወያይተውም ይሁን በግላቸው ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ከሰጡ በኂላ መምህሩ የተማሪዎችን ምላሽ በማጠናከር ተጨማሪ ገለፃ ሲሰጡ ተስተውሏል፡፡

በተደረጉት አስራ አራት ምልከታዎች መምህራን በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ይዘቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ እንዲሰሩ ሲደረግ ተስተውሏል፡፡ ነገር ግን መምህራኑ የራሳቸውን ሰዋስዋዊ ይዘቶች በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተመፃህፍት አንብበው እንዲሰሩ ብለው የሰጡት የግልም ሆነ የቡድን ስራ በሁሉም ምልከታዎች አልታየም፡፡ ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ተማሪዎች ሲሳተፉ መምህራኑ በስምንቱ ክፍለ ጊዜያት ጎበዝ፣ጥሩ፣በጣም ጎበዝ እና በጣም ጥሩ በማለት ተማሪዎችን ሲያበረታቱ

ተስተውሏል። በቀሪዎቹ ስድስት ክፍለ ጊዜያት ግን መምህራኑ በንቃት ለሚሳተፉ ተማሪዎች ምንም ማበረታቻ ቃላት ሲጠቀሙ አልታየም።

መምህራን ጥያቄ በሚጠይቁበት ወቅት አጭርና ግልፅ ጥያቄዎች ማዘጋጀት፣ ጥያቄውን ከመጠየቃቸው በፊት ጥያቄውን በሚገባ መግለፅ፣ ለማሰብ በቂ ጊዜ መስጠት፣ በተማሪዎች የሚሰጡ ምላሾችን በአትኩሮት ማዳመጥ እና የተማሪዎችን አቅም ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ መምህራን ፈጣን ምላሽ መስጠት ፣ ተማሪዎችን ማበረታታት፣ ለተማሪዎች መልስ ማስተካከያ መስጠት እና ድክመታቸውን ለመሸፈን የተሳሳተ መልስ ላለመስጠት መጠንቀቅ የመሳሰሉትን ተግባራት በሚገባ መተግበር አለባቸው http://samples.jbpub.com/9780763749453/49451_CH09_FINAL.pdf በዚህም መሰረት በሁለቱም ትምህርት ቤቶች በተደረጉት አስራ አራት ምልከታዎች በአምስቱ ክፍለ ጊዜያት ብቻ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ ታይቷል። ከነዚህ ጥያቄዎች ሁለቱ በሐወልቲ ሁ/ደ/ት/ቤት የተጠየቁ ሲሆን ሶስቱ ጥያቄዎች ደግሞ በዓይደር ሁ/ደ/ት/ቤት ተጠይቀዋል። ከተጠየቁት አምስት ጥያቄዎች ሁለቱ ጥያቄዎች በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በቂ (ትክክለኛ) ምጋቤ ምላሽ ያገኙ ሲሆን የተቀሩት ሶስት ጥያቄዎች ግን መምህራኑ ትክክለኛ ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ አልታየም። ትክክለኛ ምጋቤ ምላሽ ያልተሰጣቸው ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው።

መምህርቷ የሚያስተምሩት አብገር ምዕላዶችን በመጨመር ከነጠላ ወደ ብዙ ቁጥር መቀየር ነበር። በዚህ ወቅት መምህቷ አስተምረው ከጨረሱ በኋላ አንድ ተማሪ “**ደብር** የሚለውን ቃል **ደብሮች** ወይም **አድባራት** ከማለት ይልቅ ለምን **ዱር** በሚለው አንተካውም?” የሚለውን ጥያቄ ጠየቀ። የመምህቷ ምላሽም “**ዱር** የሚለው ቃል ፍቺው (ትርጉሙ) መፈለግ ቢሆን **አድባራት** የሚለውን ቃል ይተካው ነበር። ነገር ግን አሁን እየተማማርን ያለነው የቃላት ትርጉም (ፍቺ) ሳይሆን ቅጥያዎችን በመጨመር ቃላት ማርባት ነው።” የሚል ምላሽ ሰጡ። ይሁን እንጂ መምህርቷ “**ደብር** የሚለው ቃል ትርጉሙ (ፍቹ) **ዱር** ሊሆን ይችላል” በማለት የመለሱት መልስ **የደብር** ፍቺ **ዱር** ሊሆን አይችልም። አሁንም ሌላ ተማሪ እጁን በማውጣት ሁሉንም ቃላት **የአማርኛና የግዕዝ አብገር ምዕላዶች** በመጨመር ማርባት እንችላለን? በማለት ጠየቀ። መምህርቷም

አንድ ቃል ምሳሌ በመውሰድ በሁለቱ መንገድ ማርባት እንደሚቻል አስረድተው "ስለዚህ የአረባቡ ስልት ይለያያል እንጂ በሁለቱም ማርባት እንችላለን፦" በማለት መለሱ። (ለዝርዝር ማብራሪያ **አባሪ ‹‹2››ን ይመልከቱ**) ነገር ግን መምህርቷ የሰጡት ምላሽ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም በአማርኛና በግእዝ መርባት የማይችሉ ቃላት አሉና ነው።

ሶስተኛውና በቂ (ትክክለኛ) ምጋቤ ምላሽ ያላገኘ ጥያቄ መምህሩ **የስምና የግስ ገላጭ** ያስተምሩ ነበር። ክፍለ ጊዜው ሊያልቅ ሲቃረብም ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ጋበዙ። አንድ ተማሪ እጁን በማውጣት "ሰነፍ ተማሪ ዘወትር ይጨነቃል በሚለው ዓረፍተ ነገር **ተማሪ** የሚለው ቃል ቢሰመርበት የምን ገላጭ ይሆናል?" በማለት ጠየቀ። መምህሩም በአንዱ ምድብ **የስም ገላጭ**፣በአንዱ ምድብ ደግሞ **የግስ ገላጭ** በማለት መለሱ። (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹7››ን ይመልከቱ**) ይሁን እንጂ ይህ ምላሽ ትክክለኛ (በቂ) ምጋቤ ምላሽ አይደለም። ምክንያቱም ተማሪ የሚለው ቃል የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። በመሆኑም ተገላጭ እንጂ ገላጭ በመሆን ስለማያገለግል **የስም** ወይም **የግስ ገላጭ** መሆን አይችልም።

በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ መምህራኑ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ የሚጀምሩ ሲሆን የዕለቱን ትምህርት ዓላማ በማስተዋወቅ ዙርያ ግን ድክመት ታይቷል። ከዚህም በተጨማሪ አዲስ ርእሰ ጉዳይ ማስተማር ሲጀምሩ ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ የማድረግ ሁኔታቸው ጥሩ ቢሆንም በአንድ ቡድን የሚደራጁ ተማሪዎች የየራሳቸውን ድርሻ በማከፋፈል ሁሉም የቡድኑ አባላት እንዲሳተፉ በማድረግ ዙሪያ ግን ድክመት ተስተውሏል።

ተማሪዎች በቡድን ሲወያዩ መምህሩ እየዞሩ በመከታተልና እገዛ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የጥያቄዎችን ምላሽ ከሰጡ በኋላ መምህሩ በተማሪዎች ምላሽ ላይ ተጨማሪ ገለፃና ማብራርያ ይሰጣሉ። እንዲሁም መምህራኑ ለጠየቁት ጥያቄ መልስ በመስጠት ንቁ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ተማሪዎች ማበረታቻ ቃላት ይጠቀማሉ ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ መምህራኑ በተማሪዎች ለሚጠየቁ ጥያቄዎች አልፎ አልፎ ትክክለኛ ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት እና የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን

በማዘጋጀት ተማሪዎች ከክፍል ውጭ አንብበው እንዲሰሩ ያለማድረግ ችግሮች እንዳሉ ከክፍል ምልከታው መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን ሚናን አስመልክቶ ከቪድዮ ቀረፃ የተገኘው መረጃ እንመለከታለን፡፡

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-H1

የመምህሩ ስም- መምህር-1

መምህርቷ ወደ ክፍል እንደገቡ አንድ ተማሪ ዳስተራቸውን ተቀብሎ ጥቁር ሰሌዳውን ካፀዳላቸው በኋላ የተለመደውን ሰላምታ አቀርበው የዕለቱን ትምህርት ርእስና ቀን ፃፉ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቻቸውን ፀጥ እንዲሉ በመንገር "ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩት ስለምን እንደነበር ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ምላሽ ሰጡ፡፡ ከዚያም መምህርቷ የዕለቱ ትምህርት ርእስ ዓረፍተ ነገርን በተመለከተ እንደሆነ ገልፀው "አንድ ዓረፍተ ነገር ስህተት የሚባለው የምን የምን ጎድለት ሲታይበት ነው?" የሚል ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ ለሶስት ደቂቃ ያህል በየኔትወርካቸው እንዲወያዩ ነገሩዋቸው፡፡ በውይይቱ ወቅትም መምህርቷ እየዞሩ መከታተላቸውን ቀጠሉ፡፡ የተሰጣቸው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ መምህርቷ የኔትወርኮችን ስም በመጥራት ተማሪዎች የተወያዩበትን ውጤት እንዲናገሩ አደረጉ፡፡ ከተማሪዎች ምላሽ ቡኋላም መምህርቷ በዓረፍተነገር ውስጥ ስህተት ያስከትላሉ ያሉዋቸውን ለእያንዳንዱ ነጥቦች ምሳሌ እንዲሰጡ ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸው በማውጣት ምሳሌ ሰጡ፡፡ የተማሪዎችን ምሳሌ መስጠት ካበቃ በኋላ መምህርቷ "በጣም ጥሩ" ብለው ተማሪዎችን በማበረታታት የተሰጠውን ምላሽ አጠናከሩ፡፡... ከዚያም የዕለቱን ትምህርት ተማሪዎች ማጠቃለያ እንዲሰጡ አደረጉ፡፡ (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹3››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-L1

የመምህሩ ስም- መምህር-2

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ጥቁር ሰሌዳውን በማፅዳት የዕለቱን ትምህርት ርእስና ቀን ፃፉ። በመቀጠል ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለምን እንደተማሩ ተማሪዎችን ጠየቁ። ተማሪዎችም በማስታወስ መለሱ። መምህሩ አሁንም ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለተማሩት ርእሰ ጉዳይ ምሳሌ እንዲሰጡ ተማሪዎቹን አዘዙ። ተማሪዎችም ምሳሌዎችን ሰጡ። ከዚያም መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ዓረፍተ ነገሮች ማስተካከል እንደሆነ በመግለፅ ርዕሱን አስተዋወቁ።

በመቀጠል ሁለት ዓረፍተ ነገር ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የምን ስህተት እንዳለባቸው አስረዱ። ተማሪዎች መረዳታቸው ካረጋገጡ ቡኋላም ሁለት ዓረፍተ ነገር ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ዓረፍተ ነገሮቹ የምን ስህተት እንዳለባቸው በቃል እንዲገልፁ አደረጉ። ተማሪዎቹም በቃል መለሱ። ከዚያም መምህሩ በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ 58 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች በየኔትወርካቸው እየተወያዩ ስህተታቸውን በመለየት አስተካክለው እንዲፅፉ ተማሪዎቹን አዘዙ። ተማሪዎችም በየኔትወርካቸው መወያየት የጀመሩ ሲሆን መምህሩም እየዞሩ ይከታተሉ ነበር። መምህሩ ለጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ጊዜ ሲያበቃም ከእያንዳንዱ ኔትወርክ ተማሪዎች በመምረጥ እየወጡ እዲመልሱ አደረጉ። ተማሪዎችም እየወጡ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ መለሱ።… አስከትለውም የዕለቱን ትምህርት ተማሪዎች እንዲያጠቃልሉ አደረጉ። ተማሪዎች ደግሞ እጃቸውን በማውጣት ማጠቃለያውን የሰጡ ሲሆን መምህሩም “በጣም ጎበዞች” በማለት ተማሪዎችን አበረታቱ። (ለዝርዝር ሀተታ **አባሪ ‹‹5››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ አንድ- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-C1

የመምህሩ ስም- መምህር-3

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ የተለመደውን ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው የዕለቱን ትምህርት “ከግስ አርእስት መመስረት” መሆኑን አስተዋወቁ። አስከትለውም “ከግስ አርአስት እንዴት መመስረት ይቻላል?” የሚለውን ጥያቄ ተማሪዎችን ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ምላሽ ሰጡ። በመቀጠል መምህሩ ሶስት ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከግስ ወደ አርእስት እንዴት እንደተቀየሩ አስረዱ። ከዚያም መምህሩ አምስት ቃላት ተማሪዎቹን በቃል በማስፃፍ

ከግስ ወደ አርእስት እንዲቀይሩ የክፍል ስራ ሰጡ። የክፍል ስራውም በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎች ሲወያዩም መምህሩ እየዞሩ ሲከታተሉ ይታያሉ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላም ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ አዘዙ። ተማሪዎችም የጥያቄዎችን ምላሽ ሰጡ። መምህሩ ተማሪዎችን "ጎበዞች" ብለው በማድነቅ ማጠናከሪያ ሰጡ። ከዚያም **የስም** እና **የግስ ገላጭ** ምንነት በተመለከተ አጭር ማስታወሻ ሰጡ። ለሰጡት ማስታወሻ ገለፃና ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 46 ከ ‹‹ሀ-ረ›› ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች የስምና የግስ ገላጭ በመለየት የክፍል ስራ እንዲሰሩ መምህሩ መመሪያ ሰጡ። ተማሪዎችም ደብተራቸው ላይ በመፃፍ የክፍል ስራውን ሰሩ። የተሰጠውን ደቂቃ ካለቀ በኋላም መምህሩ ተማሪዎች የጥያቄዎችን መልስ በቃል እንዲመልሱ ጋበዙ። ተማሪዎችም እያንዳንዱ ጥያቄ በቃል መለሱ። የተማሪዎች ምላሽ ከተጠናቀቀ በኋላም መምህሩ ስለ ዕለቱ ትምህርት ማጠቃለያ ሰጡ። ቀጥለውም መምህሩ ተማሪዎች በዕለቱ ትምህርት ያልገባቸው እንዲጠይቁ ዕድል ሰጡ። ተማሪዎችም ሁለት ጥያቄዎች ጠየቁ። መምህሩም ለአንደኛው ትክክለኛ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ለሁለተኛው ግን ትክክለኛ ምላሽ አልሰጡም። (**ለተጨማሪ ማብራሪያ አባሪ ‹‹7››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ ሁለት- ዓይደር/ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-K2

የመምህሩ ስም- መምህር-4

መምህርቷ ወደ ክፍል በመግባት ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው የዕለቱን ትምህርት ርእስና ቀን ፃፉ። በመቀጠል ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበው ባለፈው ክፍለ ጊዜ መናገር ተምረው እንደ ነበር በማስታወስ ተማሪዎች በመናገር ስር የተከራከሩበትን ጉዳይ ምን እንደነበር ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ምላሽ ሰጡ። መምህቷም ተማሪዎችን "በጣም ጥሩ ጎብዛቹኋል" በማለት የተማሪዎችን ገለፃ አጠናከሩ። በመቀጠል መምህርቷ የዕለቱን ትምህርት ስዋስዋዊ ስህተት መለየት መሆኑ አስተዋወቁ። ከዚያም "በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚታየው ሰዋስዋዊ ጉድለት በመለየት ዓረፍተ ነገሩን አስተካክላችሁ ፃፉ" የሚለውን ትዕዛዝ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ። በመቀጠል ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ በሶስቱ ዓረፍተ ነገሮች

የሚታየው ስህተት በመለየትና አስተካክለው በመፃፍ አስረዱ። የቀሩትን ደግሞ ተማሪዎች በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎችም መወያየት ጀመሩ። ተማሪዎች ሲወያዩም መምህርቷ በየኔትወርኩ እየዞሩ ይከታተሉ ነበር። መምህርቷ ለሰጡዋቸው ጥያቄዎች የሰጡት ጊዜ ሲያበቃም ተማሪዎች የጥያቄዎችን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ እንዲመልሱ አደረጉ። ተማሪዎችም ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ። በወቅቱም ለተመሳሳይ ተማሪዎች ደጋግሞ እድል የመስጠት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ በመጨረሻም መምህርቷ የተማሪዎችን ምላሽ በማጠናከር ተማሪዎች ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ እድል ሰጡ። ተማሪዎች ደግሞ ጥያቄ እንደሌላቸው ገለፁ። (ለተጨማሪ መረጃ **አባሪ ‹‹8›› ን ይመልከቱ**)

ከቪድዮ ቀረፃ በተገኘው መረጃ መሰረት መምህራን በነበረው የትምህርት ሂደት በርካታ ተግባራት ሲያከናውኑ ተስተውሏል፡፡ መምህራኑ የእለቱን ትምህርት በማስተዋወቅ ተማሪዎች ስለ ርእሰ ጉዳዩ መጀመሪያ እንዲናገሩ አድርገዋል፣ ተማሪዎች ምሳሌዎች እንዲሰጡ ዕድል ሰጥተዋል፣ የክፍል ስራ አስሰርተዋል፣ማስታወሻ አስፅፈዋል፣ ምሳሌዎችን በመውሰድ አስረድተዋል፣የተማሪዎችን ውይይት እየተዘዋሩ ተከታትለዋል፣ ማበረታቻ ቃላት ተጠቅመዋል፣የተማሪዎችን ሀሳብ አጠናክረዋል፣የዕለቱ ትምህርት ከግብ መድረሱን ፈትሸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ በክፍለ ጊዜው መምህራኑ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ሲያደርጉ ታይቷል፡፡ ነገር ግን መምህራኑ ለተመሳሳይ ተማሪዎች ደጋግሞ እድል የመስጠትና ተማሪዎች ለጠየቁዋቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት አልፎ አልፎ ተስተውሏል፡፡ በመቀጠል ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ የተገኘው ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## ሰንጠረዥ-5 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የመምህራን ሚና በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተሰጠ የነጥብ ደረጃ በቁጥርና በመቶኛ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | ያልተመለሱ |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | |
| 7. | መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ዓላማ ያስተዋውቃሉ | 27 | 35 | 27 | 35 | 11 | 14 | 10 | 13 | 2 | 3 | |
| 8. | መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ርእስ ለማስተዋወቅ የቅድመ ትምህርት ጥያቄ በማቅረብ ከዳራዊ እውቀታችን ጋር እንድናያይዝ ያደርጋሉ | 39 | 51 | 27 | 35 | 7 | 9 | 3 | 4 | 1 | 1 | |
| 9. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በክፍልና በቤት ስራ መልክ እንድንሰራ ያደርጋሉ | 41 | 53 | 22 | 28 | 9 | 12 | 3 | 4 | 2 | 3 | |
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች በቡድን እየተወያየን እንድንሰራ ያደርጉናል፣እየተዛዋወሩም ከታተሉናል | 38 | 49.3 | 21 | 27.2 | 7 | 9 | 7 | 9 | 4 | 5 | |
| 11. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን የቡድን ውይይትም ሆነ የቡድን ስራ ሲሰጡ የቡድኑን መሪ፣ፀሐፊና ሌሎች አባላት ያደረጃሉ፤ ሁሉም የቡድኑ አባላት በየተራ የቡድኑ መሪነት ሚና እንዲደርሳቸው ያደርጋሉ | 17 | 22 | 23 | 30 | 17 | 22 | 13 | 17 | 7 | 9 | |
| 12. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በግልም ሆነ በቡድን ሆነን የምንሰራቸውን የተለያዩ ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች በማዘጋጀት ከቤተ መፃህፍትና ከሌሎች ምንጮች አፈላልገን እንድንሰራ ያደርጋሉ | 25 | 32 | 18 | 23 | 16 | 21 | 9 | 12 | 9 | 12 | |
| 13. | ሰዋስውን ስንማር መምህራችን ያልገባን እንድንጠይቅ ያደርጋሉ | 45 | 58.4 | 21 | 27.1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 5 | 6 | |
| 14. | መምህራችን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ዘዴዎች በማቀላቀል ይጠቀማሉ | 30 | 39 | 30 | 39 | 8 | 10.3 | 4 | 5 | 5 | 6.4 | |

በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.7 መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ዓላማ በማስተዋወቅ መጀመራቸውን ለመፈተሽ የቀረበ ሀሳብ 27(35%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣27(35) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 11(14%)ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣10(13%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን የተቀሩት 2(3%) ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተማሪዎቹ መልስ መሰረት 54(70%) ያህሉ ተማሪዎች መምህራቸው የዕለቱ ትምህርት ዓላማ በማስተዋወቅ ይጀምራሉ የሚለውን ሀሳብ እንደሚስማሙበት፣ 12(15%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 11(14%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን ያስቸግራቸዋል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው መምህራን የዕለቱን ትምህርት ሲጀምሩ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ በማስተዋወቅ እንደሚጀምሩ ነው፡፡ ይህም ከክፍል ውስጥ ምልከታ ከተገኘው መረጃ ተመሳሳይ ነው፡፡

Azeb (1984) እንደገለፁት አንድ አዲስ ይዘትን ለማስተማር ተማሪዎች ስለ ርእሰ ጉዳዩ የሚያውቁትን መጀመሪያ እንዲናገሩ በማደረግ ከዳራዊ እውቀታቸው መጀመር የተማሪዎች የእውቀት ደረጃ ምን ላይ እንዳለ ለማወቅ ይረዳል፡፡ በመሆኑም መምህራን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ከዳራዊ እውቀታቸው ጋር እንዲያይዙ ማድረጋቸውን ለመፈተሽ በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.8 በቀረበው ሀሳብ መሰረት 39(51%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣27(35%)የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማሁ፣7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣3(4%) አልስማማም 1(1%)ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተማሪቹ ምላሽ በመነሳት 66(84%) የሚሆኑት ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ጥያቄዎች ይቀርባሉ በሚለው ሀሳብ እንደሚስማሙበት፣4(5%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተውም መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ለማስተማር ተማሪዎች ስለ ርእሰ ጉዳዩ የሚያውቁትን መጀመሪያ እንዲናገሩ ያደርጋሉ፡፡

የግል ስራ ተማሪዎች ለሚሰሩት ነገር በግላቸው ሀላፊነት በመውሰድ የሚሰሩበትና የግል እውቀታቸው ለሌሎች የሚያንፀባርቁበት ነው፡፡ የግል ስራ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በክፍል ስራ መልክ እና በቤታቸው በቤት ስራ መልክ ሊሰጥ ይችላል (Hand

Book of Higher Diploma Program 2011)። በዚህም መሰረት መምህራኑ የሰዋስው ይዘቶችን ተማሪዎች በክፍልና በቤት ስራ መልክ እንዲሰሩ ማድረጋቸውን ለመፈተሽ በቀረበው ሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.9 ላይ ተጠቅሷል። ለዚህ ሀሳብም 41(53%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 22(28%) እስማማለሁ እና 9(12%) ደግሞ ለመወሰን ያስቸግረኛል በማለት መልሰዋል። ከዚህም በተጨማሪ 3(4%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማም በማለት የመለሱ ሲሆን የተቀሩበት 2(3%) ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል። ከተማሪወቹ ምላሽ በመነሳት 63(81%) ያህሉ ተማሪዎች የሰዋስው ይዘቶችን በክፍልና በቤት ስራ መልክ ይሰጣል የሚለውን ሀሳብ እንደሚስማሙበት፣ 5(7%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 9(12%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መረዳት ተችሏል። ስለዚህ የተገኘው መረጃ መምህሩ ተማሪዎችን ሰዋስዋዊ ይዘቶች በክፍልና በቤት ስራ መልክ እንዲሰሩ ማድረጋቸውን ያመላክታል።

Widdwoson (1987) እንደገለፁት በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ትክክለኛ የቋንቋ ሞዴል ማዘጋጀት፣ ከተማሪዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር፣ ተማሪዎችን ማደራጀት፣ ተማሪዎች ያላቸውን ልምድና ለሚያደርጉት ሙከራ ማበረታታት እና እየተዘዋወሩ ተማሪዎችን ማገዝና መከታተል አለባቸው። በዚም መሰረት መምህራን ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን ሲወያዩ እየዞሩ የሚከታተሉ (የሚቆጣጠሩ) መሆናቸውን ለመፈተሽ በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.10 የቀረበው ሀሳብ በውይይት ወቅት መምህሩ እየተዘዋወሩ ተማሪዎችን ማገዝና መከታተልን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን 38(49.3%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 21(27.2%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 7(9%)የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 4(5%) የሚሆኑት ተማሪዎች ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በተማሪዎቹ ምላሽ መሰረትም 59(76.5%) የሚሆኑት ተማሪዎች መምህሩ እየዞሩ በመከታተል እገዛ ያደርጋሉ የሚለውን ሀሳብ እንደሚስማሙበት፣11(14%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መረዳት ተችሏል። ስለዚህ የተገኘው መረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች በቡድን ሲወያዩ እየዞሩ በመከታተል እገዛ ማድረጋቸውን ያመለክታል።

በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.11 መምህሩ ቡድን ሲያደራጁ የቡድኑ አባላት ፀሀፊና መሪ በማለት አደራጅተው ሁሉንም የመሪነት ሚና እንዲደርሳቸው የሚያደርጉ መሆናቸውን በተመለከተ 17(22%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 23(30%) እስማማለሁ፣ 17(22%) ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 13(17%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማም እና የተቀሩት 7(9%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከተማሪቹ መልስ መገንዘብ እንደሚቻለው መምህሩ የአንድ ቡድን አባላት የየራሳቸውን ድርሻ በማከፋፈል ሁሉንም የመሪነት ሚና እንዲደርሳቸው ያደርጋሉ የሚለውን ሀሳብ 40(31%) ያህሉ ተማሪዎች እንደሚስማሙበት፣24(31%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 13(17%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን ያስቸገራቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም መምህራኑ እያንዳንዱ የቡድን አባል የቡድን መሪነት ድርሻ እንዲደርሰው እንደሚያደርጉ ያስረዳል፡፡

በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.12 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስዋስዋዊ ይዘቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተ መፃህፍት ፈልገው በቡድንም ሆነ በግል እንዲሰሩ ማድረጋቸውን በተመለከተ 25(32%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣18(23%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣16(21%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 9(12%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 9(12%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን አዘጋጅተው ተማሪዎች በግላቸውና በቡድን በቤተመፃህፍት አፈላልገው እንዲሰሩ የሚያደርጉ መሆናቸውን 43(55%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደሚስማሙበት፣ 18(24%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 16(21%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ነው፡፡ ከዚህ በላይ በተገኘው ውጤት መሰረት የአማርኛ መምህራኑ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተመፃህፍት አፈላልገው እንዲሰሩ የሚያደርጉ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.13 መምህራን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ የሚያደርጉ መሆናቸውን ለመፈተሽ የቀረበው ሀሳብ 45(58.4%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 21(27.2%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 3(4%)

ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣3(4%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማምና 5(6%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም ብለዋል። ከተማሪዎቹ መልስ መረዳት እንደሚቻለው 66(85.6%) ያህሉ ተማሪዎች መምህራቸው ጥያቄ እንዲጠይቁ የሚያደርጉ መሆናቸውን እንደሚስማሙበት፣8(10%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 3(4%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ነው። ይህም መምህራኑ ሰዋስውን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ዕድል እንደሚሰጡዋቸው ያመለክታል።

በሰንጠረዥ-5 ተራ ቁ.14 መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን በማቀላቀል የሚያስተምሩ መሆናቸውን ለመፈተሽ የቀረበውን ሀሳብ በተመለከተ 30(39%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 30(39%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣8(10.3%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 4(5%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 5(6.4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል። ይህም መምህራቸው ሰዋስውን ሲያስተምሩ ዘዴዎችን አቀላቅለው ይጠቀማሉ የሚለውን ሀሳብ 60(78%) ያህሉ ተማሪዎች እንደሚስማሙበት፣9(11.4) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 8(10.3%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንዳስቸገራቸው ያስረዳል። በተማሪዎች ምላሽ መሰረትም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የተለያዩ ዘዴዎችን በማቀላቀል እንደሚያስተምሩ መረዳት ተችሏል።

በመማር ማስተማር ሂደት የዕለቱ ትምህርት ዓላማ ማስተዋወቅ ተማሪዎች በቂ ዝግጅት በማድረግ እንዲማሩ ያደርጋል። ስለዚህ ተማሪዎች በሰጡት ምላሽ መሰረት አማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ያስተዋውቃሉ። ከዚህም በተጨማሪ መምህራኑ የሰዋስው ይዘቶችን ለማስተማር አዲስ ርእስ ሲጀምሩ የተማሪችን ቅድመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎች በመጠየቅ እንደሚጀምሩ ተማሪዎች ከሰጡት መረጃ መገንዘብ ተችሏል። እንዲሁም መምህራኑ ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸውን ጥያቄዎች በክፍልና በቤት ስራ መልክ ተማሪዎች እንዲሰሩ ያደርጋሉ።

የሰዋስው ይዘቶችን በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ተማሪዎችን በቡድን እንዲሰሩ በማድረግና እየተዘዋወሩ በመከታተል አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ

በአንድ ቡድን የሚደራጁ አባላት የየራሳቸውን ድርሻ በማካፈል ሁሉም የቡድን መሪነት ድርሻ እንዲደርሳቸው በማድረግ፣ ሰዋስዋዊ የሆኑ ይዘቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተመፃህፍትና ከሌሎች ምንጮች አፈላልገው እንዲሰሩ በማድረግ፣ ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ዕድል በመስጠትና ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ሲያስተምሩ ዘዴዎችን አቀላቅለው በመጠቀም ዙሪያ ሁሉም መምህራን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ከተማሪዎች መልስ መረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከቪድዮ ቀረፃ የተገኘው መረጃ መምህራን በሁለት ክፍለ ጊዜያት ካላልሆነ በስተቀር የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ሲያስተዋውቁ አልታየም፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ ተማሪዎች የየራሳቸውን ድርሻ ሲያከፋፍሉና ተማሪዎች ከቤተ መፃህፍት አፈላልገው የሚሰሩዋቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች አዘጋጅተው በመምጣት ሲሰጡ አልታየም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በተወሰነ መልኩ ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከቪድዮ ቀረፃ ከተገኘው መረጃ ጋር የመጣረስ ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

ለመምህራን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የመምህራን ሚና ምንድን ነው? ተብሎ በተራ ቁ. 4 ለተጠየቀው ጥያቄ መምህራኑ መጀመሪያ ማንኛውም መምህር የሚያስተምረውን ነገር ጠንቅቆ ማወቅና በቂ ዝግጅት ማድረግ፣ ተማሪዎች የሚሰሩት ስራ መስጠት ፣ተማሪዎችን እንዲሰሩ ሲያዝዝ ግልፅና የማያሻማ መመሪያ መስጠት፣ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ደግሞ እየዞረ መከታተልና የማይሳተፉትን መቀስቀስ፣ ተማሪዎች እንዲወያዩበት ስለ ተፈለገው ጉዳይ እየተወያዩ መሆኑን በማያወቁት መንገድ መከታተል፣ ሌላ ስራ የሚሰሩ (ወሬ የሚያወሩ ከሆነ ደግሞ ምክር መስጠት)፣ሁሉ ጊዜ የሚሳተፉትን ደጋግሞ ዕድል ከመስጠት ይልቅ ለማይሳተፉት ማሳተፍ፣ ማበረታታት ፣የተሳሳቱትን እርማት መስጠት እና ሀላፊነት በመውሰድ እንዲማሩ ማነሳሳት የሚሉትን ከመምህሩ የሚጠበቁ ተግባራት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹20›› ን ይመልከቱ**)

በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታና ከቪድዮ ቀረፃ የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው መምህራኑ የዕለቱ ትምህርት ርእስ ከማስተዋወቅ ማጠቃለያ እስከ መስጠት ባለው ሂደት የተለያዩ ተግባራት እንደሚያከናውኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ አለማስተዋወቅ፣በአንድ ቡድን ለሚደራጁ አባላት

የየራሳቸውን ድርሻ አለመከፋፈል፣ተማሪዎች በቤታቸው የሚለማመዱዋቸውን ስዋስዋዊ ይዘቶች አዘጋጅቶ አለመስጠት እና በተማሪዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አልፎ አልፎ ትክክለኛ ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት ተስተውለዋል፡፡ ከፅሁፍ መጠይቅና ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ መምህራን በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የተለያዩ ስራዎችን ለተማሪዎች በመስጠት እና ተማሪዎች የሚማሩበትን መንገድ በመክፈት ተማሪዎች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ሲያመቻቹ እንደሚስተዋሉ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ በሁሉም መረጃ መሰብሰብያ መንገዶች የተገኙትን መረጃዎች ስንመለከት መምህራኑ የተወሰኑ ድክመቶች ቢኖሩዋቸውም እንኳ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.3 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎች ሚና

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው መማር የሚያበረታታ ነው፡፡ በሂደቱ ውስጥ መምህራን ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማነሳሳት ተማሪዎች ደግሞ በተሰጣቸው ርእሰ ጉዳይ ላይ መወያየት፣መከራከር፣ ሀሳብ መለዋወጥ፣መጠየቅና መመለስ አለባቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች ከመምህር ከመቀበል የራሳቸውን ሀሳብ እንዲያፈልቁና እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳል (Tudor 1996)፡፡ በዚህ መሰረትም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ያላቸውን ሚና (የሚያከናውኑዋቸውን ተግባራት) ለመለየት በአራቱም መረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች አንድ በአንድ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ከክፍል ምልከታ የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ- 6 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎች ሚና በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | የተተኮረባቸው ነጥቦች | ተከናውኗል | አልተከናወነም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 17. | ተማሪዎች በጥንድ የተሰጣቸውን ጥያቄ ለመመለስ በንቃት ተሳትፈዋል | - | - | የጥንድ ስራ አልተሰጠም |
| 18. | ተማሪዎች በቡድን የተሰጣቸውን ጥያቄ ለመመለስ ተሳትፈዋል | 14 | - | |
| 19. | ተማሪዎች በግል የተሰጣቸውን ጥያቄ ለመመለስ ተሳትፈዋል | 7 | - | 7 ክፍል ጊዜ የግል ስራ አልተሰጠም |
| 20. | ተማሪዎች ከቡድን ውይይት፣ከጥንድና ከቡድን ስራ ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው አንፀባርቀዋል | 14 | - | |
| 21. | ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ ተሳትፈዋል | 5 | 3 | በ6ቱ ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ዕድሉ አልተሰጠም |
| 22. | ተማሪዎች መምህርም ሆነ ተማሪ ሲጠይቅ ሲመልስ በጥሞና ያዳምጣሉ | 10 | 4 | |
| 23. | ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ ቁጥር ሰሌዳ ላይ ፅፈዋል | 6 | 8 | |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በተደረጉት አስራ አራት ምልከታዎች ተማሪዎች በጥንድ እንዲወያዩ አልተደረገም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በጥንድ እንዲሰሩ የተጠየቁትን ጥያቄ መልሰዋል ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን በሁሉም ክፍለ ጊዜያት በቡድን እንዲወያዩ መምህሮቻቸው የሰጡዋቸው ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በንቃት ሲሳተፉ ታይቷል፡፡ Nunan (1988) እንደገለፁት የግል ስራ ተማሪዎች ትምህርቱን የሚማሩት ያለመምህሩ ወይም ያለሌላ ሰው ረዳትነት በግል ጥረታቸው ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች በራሳቸው ጊዜ መማርን እንዲያገኙና ሀላፊነት እንዲወስዱ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በሁለቱም ትምህርት በቶች በተደረጉት

አስራ አራት ምልከታዎች በሰባቱ ክፍለ ጊዜያት የቤትም ሆነ የክፍል ስራ ያልተሰጠ ሲሆን በሰባቱ ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች በግላቸው የክፍል ስራ እንዲሰሩ ተደርጓል። በዚህ ወቅትም ተማሪዎች ለመመለስ በንቃት ሲሳተፉ ተስተውሏል።

በተደረገው ምልከታ ተማሪዎች የጥንድ ስራና የቡድን ስራ ሲሰጡ ባይታይም ከቡድን ውይይት ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው ሲያቀርቡ በሁሉም ምልከታዎች ታይቷል። አንዱ ቡድን የተወያየበትን ሀሳብ በሚያቀርብበት ጊዜ በአስሩ ምልከታዎች ሌሎች በጥሞና ሲያዳምጡ የታየ ሲሆን በአራቱ ክፍለ ጊዜያት ግን ሁሉም ተማሪዎች እኔ፣እኔ የሚለውን ድምፅ በማሰማትና ለአንድ መልስ ዕድል ከተሰጠው ተማሪ ውጭ ያሉት ተማሪዎችም አብረው በመመለስ ፀጥታ ያልሰፈነባቸው ክፍለ ጊዜያት ነበሩ።

ጥያቄ በማንኛውም የትምህርት ደረጃ በክፍል ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎችና መመምህራን መካከል ለሚመሰረት ግንኙነት መሰረት ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው። ይህም የተማሪዎችን የማሰብ፣የተለያዩ መረጃዎችን በቀላሉ የማግኘት፣ የመመርምርና ስሜታቸውን የመግለፅ ችሎታ ለማዳበር ይረዳቸዋል (Hand Book of Higher Diploma Program 2011)። ይሁን እንጂ በተደረጉት አስራ አራት ምልከታዎች ተማሪዎች በአምስቱ ክፍለ ጊዜያት ብቻ ጥያቄ ሲጠይቁ የተስተዋሉ ሲሆን በሶስቱ ክፍለ ጊዜያት ሲጠይቁ አልታዩም። በተቀሩት ስድስት ክፍለ ጊዜያት ግን መምህራኑ ራሳቸው ተማሪዎች ያልገባቸው እንዲጠይቁ እድል አልሰጡም። ተማሪዎች ጥያቄ በመምህርም ሆነ በተማሪ ሲጠየቅ በጥሞና በማዳመጥ በቡድን ውይይት ወይም በግል እንዲሰሩ የተሰጣቸውን ጥያቄ በስድስቱ ክፍለ ጊዜያት ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተው ሲፅፉ ታይቷል።

ከተደረገው የክፍል ውስጥ ተከታታይ ምልከታ መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎች በቡድንም ሆነ በግል የተሰጣቸውን ጥያቄ በመመለስና ከቡድን ውይይት ያገኙትን ሀሳብ ለተማሪዎች በሚገባ በማንፀባረቅ ንቁ ተሳትፎ እንደሚያሳዩ ነው። ከዚህም በተጨማሪ አልፎ አልፎ ጥያቄ በመጠየቅ፣ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥቶ በመፃፍ የሚሳተፉ ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ የሚሰጡትን ምላሽ በጅምላ ሲመልሱ ታይቷል። ይሁን እንጂ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የጥንድ ስራ ሲሰጥ አልታየም። በዚህ መሰረት በምልከታ በተገኘው መረጃ በክፍል ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የሚተገብሩዋቸውና

ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው የመማር ማስተማር ዘዴዎች የቡድን ውይይት፣ጥያቄና መልስ እና የክፍል ስራ መሆናቸው መገንዘብ ተችሏል። በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎች ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ከቪድዮ ቀረፃ የተገኘው መረጃም ቀጥሎ የቀረበውን ይመስላል።

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ- G2

የመምህሩ ስም- መምህር-1

መምህርቷ ወደ ክፍል ሲገቡ አንድ ተማሪ ዳስተሩን ተቀብሎ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዳላቸው። በመቀጠል መምህርቷ የተለመደውን ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቤት ስራ መስራታቸውን እየዞሩ አረጋገጡ። ከዚያም ተማሪዎች የሰሩትን የቤት ስራ እየወጡ እንዲያነቡ አደረጉ። ተማሪዎችም የፃፉትን የቤት ስራ እየወጡ አነበቡ። በመቀጠል መምህርቷ የዕለቱን ትምህርት ርእስ ከስም ወደ ቅፅል መቀየር መሆኑ አስተዋወቁ። ከዚያም "ስም ምንድን ነው? ቅፅልስ?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ምላሽ ሰጡ። ከዚያም መምህርቷ ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ምሳሌዎች በመውሰድ ስም ወደ ቅፅል እንዴት እንደሚቀየር አስረዱ። መምህርቷ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምሳሌ መረዳታቸው ካረጋገጡ በኋላም በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 69 ከ ‹‹ሀ-በ›› ስር ያሉትን ቃላት ከስም ወደ ቅፅል በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አሳሰቡ። ተማሪዎችም እየፃፉ እና እየተወያዩ ነበር። መምህርቷ ለሰጡት ጥያቄ የሰጡት ደቂቃ ሲያበቃም ጥቁር ሰሌዳውን ለአራት ከፍለው ከአራት ኔትወርኮች አራት ተማሪዎችን በማስወጣት መልሳቸውን ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲፅፉ አዘዙ። ተማሪዎችም እየወጡ በመፃፍ መልሳቸውን ፃፉ። … መምህርቷ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል ቢሰጡም ተማሪዎች ግን ሲጠይቁ አልታዩም። (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹9›› ን ይመልከቱ**) መምህርቷ በ ምድብ ‹‹H›› በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ሲያስተምሩም ተማሪዎች ሚናቸውን የተወጡ መሆናቸውን ከቪድዮ ቀረፃ በተገኘው መረጃ መገንዘብ ተችላል። (ለዝርዝር ማብራሪያ **አባሪ ‹‹10››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-E2

የመምህሩ ስም- መምህር-2

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ለተማሪዎች ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱ፡፡ በመቀጠል ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩት ስለምን እንደነበር ተማሪዎቹን ጠየቁ፡፡ ተምሪዎችም ስለ ምን እንደተማሩ በማስታወስ መለሱ፡፡ መምህሩም ተማሪዎች ምሳሌ እንዲሰጡ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት የተለያዩ ምሳሌዎች ሰጡ፡፡ ከዚያም መምህሩ አምስት ቃላት በመፃፍ ተማሪዎች የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም የክፍል ስራውን በግላቸው ሰሩ፡፡ የተሰጣቸው ጊዜ ካለቀ በኋላም ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ አሳሰቡ፡፡ ተማሪዎችም በቃል መለሱ፡፡ መምህሩ "አንድ ቃል ከሌላ ቃል እንዴት ማዛመድ ይቻላል?" በማለት ለተማሪዎች ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ምላሽ ሰጡ፡፡ ከዚያም መምህሩ በወቅቱ የሚሰሩት ቃላት በማጣመር መሆኑን ገልፀው ተማሪዎች "በመማሪያ መፅሀፋችሁ ገፅ 69 ከ ‹‹1-10›› ያሉትን ቃላት በየኔትወርካቹ እየተወያያችሁ አዛምዱ" በማለት አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም ተወያዩ፡፡ ደቂቃው ካለቀ በኋላም ተማሪዎችም ለተጠየቁት ጥያቄዎች ከየኔትወርካቸው አንዳንድ ተማሪ በመነሳት ምላሽ ሰጡ፡፡ (ለተጨማሪ ሀተታ **አባሪ ‹‹11››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-L2

የመምህሩ ስም- መምህር-2

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱ፡፡ በመቀጠል "ባለፈው ክፍለ ግዜ ስለምን ተምራችሁ ነበር?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም ስለ ቃለ ጉባኤ መማራቸውን ገለፁ፡፡ መምህሩ "ቃለ ጉባኤ ምንድን ነው?" የሚል ጥያቄ ለተማሪዎች አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት "የቃለ ጉባኤ ምንነት አብራሩ፡፡ መምህሩ "ሌላ የተማራችሁት ነገር ነበር እስኪ አስታውሱ" በማለት ተማሪዎችን እንዲያስታወሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ስለ "ጠለፋ"

መማራቸውን ገለፁ፡፡ መምህሩ አሁንም “ጠለፋ ምንድን ነው?” የሚል ጥያቄ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም ከየኔትወርኩ እጃቸውን በማውጣት የጠለፋ ምንነት ገለፁ፡፡ ከዚያም መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ከስም ቅፅሎችን መመስረት የሚለውን መሆኑ በማስተዋወቅ አራት ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፅፈው ከስም ወደ ቅፅል እንዴት እንደሚቀየሩ አስረዱ፡፡ ተማሪዎች መረዳታቸው ካረጋገጡ በኋላም በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 69 ከ ‹‹ሀ-መ›› ስር ያሉት ቃላት በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም ሰሩ፡፡ መምህሩ ለሰጡት ጥያቄ የሰጡት ደቂቃ ሲያበቃም ከያንዳንዱ ኔትወርክ የተመረጡ ተማሪዎች እየወጡ ጥቁር ሰሌዳ ላይ መልሳቸውን እንዲፅፉ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም እየወጡ መልሳቸውን ፃፉ፡፡ መምህሩ ተማሪዎች ቀደም ብለው ከሰሩዋቸው ውጪ ሌላ ቅጥያ በመጨመር ቅፅሎችን መስርተው ምሳሌ እንዲሰጡዋቸው ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም የተለያዩ ምሳሌዎች ሰጡ፡፡ ቀጥለውም መምህሩ “የዕለቱን ትምህርት አጠቃልሎ የሚነግረኝ ማን ነው?” የሚል ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡ (ለተጨማሪ መረጃ **አባሪ ‹‹12››ን ይመልከቱ**)

ቀረፃ ሁለት- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-C2

የመምህሩ ስም- መምህር-3

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ የተለመደውን ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱ፡፡ በመቀጠል መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚታዩት ጉደለቶችን በመለየት ዓረፍተ ነገሮችን ማስተካከል መሆኑን በመግለፅ ምሳሌዎችን ወስደው አስረዱ፡፡ ከዛ የቀሩትን ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ጥያቄዎቹ በቃል መለሱ፡፡ ቀጥለውም “ምሳሌውን መሰረት በማድረግ **ነጠላ** ቁጥሮችን ወደ **ብዙ** ቁጥሮች ቀይሩ” የሚለውን ትዕዛዝ ስር ካሉት ሁለት ቃላት ምሳሌ በመውሰድ እንዴት እንደሚረቡ አስረዱ፡፡ በመቀጠል መምህሩ በምሳሌው መሰረት በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ ተማሪዎችን አዘዙ፡፡ ውይይቱ ከተጠናቀቀ በኋላም መምህሩ ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ እንዲመልሱ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን እያወጡ ቢመልሱም እንኳ እኔ፣እኔ የሚል ድምፅ

ክፍሉን በጣም ረብሾታል። ከዚያም መምህሩ የተማሪዎችን ምላሽ አጠናከሩ።… ቀጥለውም ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ጋበዙ። ተማሪዎችም ያልገባቸውን ጠየቁ። (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ‹‹13 ››ን ይመልከቱ**) መምህሩ በምድብ ‹‹A›› በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ሲያስተምሩም ተማሪዎች ሚናቸውን መወጣታቸው የበቪድዮ ምዝግቡ አመልክቷል። (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹14››ን ይመልከቱ**)

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት መምህራቸው ባዘዙዋቸው መሰረት በቡድን በመወያየት፣የውይይቱ ውጤት ለክፍል ጓደኞቻቸው በማንፀባረቅ፣ የተጠየቁትን በመመለስ፣የክፍል ስራ በመስራት፣ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተው በመፃፍና የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለያ በመስጠት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው። ይህም በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን ድርሻ የሚጫወቱ መሆናቸውን ያስረዳል። ነገር ግን ለተጠየቀው ጥያቄ በህብረት የመመለስ ችግር አልፎ አልፎ ተስተውሎባቸዋል። በማስከተል ደግሞ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ምላሽ እንመለከታለን።

## ሰንጠረዥ- 7 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎች ሚና በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተሰጠ የነጥብ ደረጃ በቁጥርና በመቶኛ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | ያልተመለሱ |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | |
| 15. | ሰዋስውን ስንማር አንድን የሰዋስው ይዘት መምህሩ ከማስተማራቸው በፊት የምናውቀውን እንናገራለን | 28 | 36 | 30 | 39 | 10 | 13 | 6 | 8 | 3 | 4 | |
| 16. | የክፍላችን ተማሪዎች በግል፣ሆነ በቡድን እንድንሰራቸው የሚሰጡን የሰዋስው ይዘቶ ሀላፊነት በመውሰድ እንሰራለን | 20 | 26 | 28 | 36 | 19 | 25 | 10 | 13 | - | - | |
| 17. | መምህራችን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ጥያቄችን በመጠየቅ ንቁ ተሳትፎ እናደርጋለን | 31 | 40.2 | 40 | 52 | 5 | 6.4 | 1 | 1 | - | - | |
| 18. | በመምህርም ሆነ በተማሪ ለተጠየቀው ጥያቄ በመለስ ንቁ ተሳትፎ እናደርጋለን | 44 | 57 | 20 | 26 | 8 | 10.3 | 1 | 1.2 | 4 | 5 | |
| 19. | የተሰጠንን ስራለማጠናቀቅ ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀማለን | 25 | 32 | 34 | 44 | 9 | 12 | 3 | 4 | 6 | 8 | |
| 20. | በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከናውኑ ተግባራት በጥንድ በጥንድ ሲሰጠን በአግባቡ እንሰራለን | 14 | 18 | 28 | 36.3 | 21 | 27.2 | 4 | 5 | 10 | 13 | |

በሰንጠረዥ-8 ተራ ቁ.15 የቀረበው ሀሳብ መምህሩ የቅድመ ትምህርት ጥያቄዎችን ሲጠይቁ ተማሪዎች በንቃት መልስ የመስጠታቸውን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህም 28(36%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 30(39%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 10(13%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣6(8%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 3(4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የተማሪዎቹ ምላሽ በመመልከት 58(75%) የሚሆኑት ተማሪዎች የቅድመ እውቀት ጥያቄዎች ሲጠየቁ ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩ መሆናቸውን እንደሚስማሙበት፣9(12%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 10(13%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም መምህሩ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን

ሲያስተምሩ ተማሪዎች የሚያውቁትን መጀመሪያ እንዲናገሩ ዕድሉን ሲሰጡዋቸው ተማሪዎች የሚያውቁትን በመናገር ንቁ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ያስረዳል፡፡

Getachew (2001) እንደገለፁት በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ማቀድና በክፍል ውስጥ (ሀላፊነት በመውሰድ መማር፣ ማስታወሻ መያዝ) ፣ የተማሩትን ማጥናት፣ በራሳቸው ችሎታ መሰረት እርስ በርስ መተጋገዝ እና እርስ በርስ ከሚያደርጉት ግንኙነት ተጠቃሚ መሆን መቻል አለባቸው፡፡ በዚህ መሰረትም በሰንጠረዥ-8 ተራ ቁ.16 ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ ሀላፊነት በመውሰድ የሚሰሩ መሆናቸውን ለመፈተሽ ለቀረበው ሀሳብ 20(26%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 28(36%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማሁ፣19(25%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 10(13%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አልስማማም ያሉ ሲሆኑ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ አልተሰጠም፡፡ ከተማሪዎቹ ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው 48(62%) ያህሉ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ በአግባቡ የሚሰሩ መሆናቸውን እንደሚስማሙበት፣ 10(13%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 19(25%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ነው፡፡ ከዚህም ተማሪዎች እንዲሰሩት የተሰጣቸውን ስራ ሀላፊነት በመውሰድ የሚሰሩ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሰንጠረዥ-8 ተራ ቁ.17 ሰዋስውን በመማር ማስተማር ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ በንቃት የሚሳተፉ መሆናቸውን በተመለከተ 31(40.2%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 40(52%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 5(6.4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣1(1%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን ፈፅሞ አልስማማም የሚል መልስ የለም፡፡ ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ተማሪዎች ሰዋስውን ሲማሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ እንደሚታዩ 71(92.2%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደሚስማሙበት፣1(1%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ እንደማይስማማበትና የተቀሩት 5(6.4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እናዳስቸገራቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም በሰዋስው መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ያልገባቸውን በመጠየቅ ንቁ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ያመለክታል፡፡

በአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የተማሪዎች ዋነኛ ሚና በተሰጣቸው ርእሰ ጉዳይ በመወያየት፣በመከራከር፣ጥያቄ በመመጠቅ፣በመመለስ እና አስተያየት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆኖ መማር ነው (Widdwoson 1987)። ከዚህም በመነሳት በሰንጠረዥ-8 ተራ ቁ.18 ተማሪዎች የሰዋስው ይዘቶችን ሲማሩ ለተጠየቁት ጥያቄ በመመለስ ንቁ ተሳትፎ ማድረጋቸውን በተመለከተ 44(57%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 20(26%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 8(10%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣1(1%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማምና 4(5%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በዚህ መሰረትም 64(83%) ያህሉ ተማሪዎች መልስ በመስጠት ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩ መሆናቸውን እንደሚስማሙበት ፣5(6.2%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 8(10.3%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚቸገሩ ነው። ከተገኘው መረጃ በሰዋስው መማር ማስተማር ሂደት በመምህርም ሆነ በተማሪ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ተማሪዎች ለመመለስ ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

በሰንጠረዥ-8 ተራ ቁ.19 የተሰጣቸውን ስራ ለመስራት ጊዚያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ሀሳብ 25(32%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 34(44%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣9(12%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 3(4%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 6(8%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል። ከተማሪዎቹ መልስ በመመልከት የተሰጣቸውን ስራ ለማጠናቀቅ ጊዜያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙ መሆናቸውን 59(76%) የሚሆኑት ተማሪዎች የሚስማሙ መሆናቸውን፣9(12%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ የማይስማሙ መሆናቸውንና 9(12%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መገንዘብ ተችሏል። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለውም ተማሪዎች የተለያዩ ስራዎች ማለትም በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ስራዎች ሲሰጣቸው የተሰጣቸውን ስራ ለማጠናቀቅ የሚሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ እንደሚጠቀሙ ነው።

በስንጠረዥ-8 ተራ ቁ.20 ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የጥንድ ስራ በአግባቡ የሚሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ 14(18%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 28(36.3%)

ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 21(27.2%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 4(5%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማምና 10(13%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የተገኘውን መረጃ እንደሚያመላክተው ተማሪዎች የጥንድ ስራን በአግባቡ የሚሰሩ መሆናቸውን 42(54.3%) ያህሉ ተማሪዎች እንደሚስማሙበት፣ 14(18%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና 21(27.2%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው ነው። ከዚህም ተማሪዎች የተሰጣቸውን የጥንድ ስራ በአግባቡ የሚሰሩ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ስለ እርስ ጉዳዩ ቅድመ እውቀት እንዲናገሩ እድሉን ሲሰጡዋቸው፤መልስ በመስጠት፣ የተሰጣቸው ስራ ሀላፊነት ወስዶ በመስራት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅና የተጠየቁትን ጥያቄዎች በመመለስ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ እንዲሰሩበት የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ የሚጠቀሙና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በጥንድ እንዲወያዩ ሲደረግ በአግባቡ የሚሰሩ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል። ነገር ግን በምልከታና በቪድዮ ቀረፃ የተገኘው መረጃ ተማሪዎች በጥንድ እንዲወያዩ ስላልተደረገ የጥንድ ስራ በአግባቡ እንደሚሰሩ ማወቅ አልተቻለም። ከዚህም በተጨማሪ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ተማሪዎች ምላሽ ሲሰጡ በጋራ የመመለስ ሁኔታ፣ጥያቄዎች በመጠየቅ ንቁ ተሳትፎ አለማሳየት ችግሮች ተስተውሎባቸዋል። ስለዚህ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በምልከታና በቪድዮ ቀረፃ ከተገኘው መረጃ አብዛኛው ተመሳሳይ ቢሆንም በተወሰነ መልኩ ግን የመጣረስ ሁኔታ ተስተውሏል።

በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የተማሪዎች ሚና ለመለየት ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር የተማሪዎች ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ? ተብሎ በተራ ቁ.4 ለተጠየቀው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽም ይህንኑ የተማሪዎች ሀሳብ የሚያጠናክር ሲሆን የተማሪዎች ሚና በተሰጣቸው ርእስ ጉዳይ ነፃ ሆነው በመወያየት፣ በመከራከር የተሰጣቸውን ስራ በመስራት፣ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው በማንፀባረቅ ፣ያልገባቸውን በመጠየቅና የተጠየቁትን በመመለስ ንቁ ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል። (ለተጨማሪ ዝርዝር አባሪ‹‹19››ን ይመልከቱ)

ከዚህ ጋር በተያያዘ መምህራንና ተማሪዎች ሚናቸውን በሚገባ የሚወጡ መሆናቸውን ለመፈተሽ በተራ ቁ.5 የመምህሩም ሆነ የተማሪዎች ሚና ይህ ከሆነ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የራሳቸውን ሚና በአግባቡ ይወጣሉ ይላሉ? ምናልባት በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ቢገልፁልኝ፡፡ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ መምህራኑ በተቻላቸው መጠን ሚናቸውን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ምክንያቱም መምህራን ሚናቸውን በሚገባ የማይወጡ ከሆነ ተማሪዎቻቸው ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ከዚህም መተጨማሪ በተማሪዎች ዙርያም ድርሻቸውን በአግባቡ ካልተወጡ ዝርዝር ውጤታማ ሊሆኑ ስለማይችሉ መምህር እውቀትን ለማስጨበጥና ተማሪዎች ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት ውጤታማ ለመሆን ሁለቱም እጅና ጓንት ሆነው መጓዝ እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጎበዝ ተማሪዎች ሚናቸውን በሚገባ የሚወጡ ቢሆኑም እንኳ አንድ አንድ ተማሪዎች ደግሞ በቡድን ሲወያዩ የመረበሽ ባህሪ ሲያሳዩ፣ ሲሰለቹ እና ስራ ሲፈቱ እንደሚስተዋሉም ጨምረው ገልፀዋል፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንድ መምህር ሲገልፁ፣

> *እ… በመምህራን ዘንድ የራስ ድርሻ ያለመወጣት ችግር ብዙም አይታይም፡፡ በተማሪዎች ዘንድም አንዳንድ ጎበዝ ተማሪዎች ራሳቸውንና የኔትወርካቸውን አባላት በማሳተፍ፤ የከበዳቸውን ይዘት ደግሞ ለመምህራቸው በመጠየቅ ለመስራት ሲጣጣሩ ይታያሉ፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች የመሰልቸት ባህሪ ያሳያሉ፡፡ በተለይ ይዘቱ የሚከብዳቸው ከሆነ ያልገባቸውን ለመምህሩ ወይም ለጓደኞቻቸው ከመጠየቅ ይልቅ መስራቱን ትተው ይተኛሉ፣ ሌላ ወሬ ያወራሉ፣ይቀላለዳሉ ወዘተ.፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ሀላፊነትን የመወጣት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃርም ተማሪዎች ድርሻቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህ መንስኤው ግን ተማሪዎቹ የዘዴው ጠቀሜታ የሚያውቁት አይመስለኝም፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ራሷ እንዳትደክም እኛን ታስቸግራለች የሚሉ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ አሁን አሁን ግን በሁሉም ትምህርት ቤትና በሁሉም መምህራን ሲተገበር ስለሚያዩት ጠቀሜታውን እየገባቸው መጥቷል፡፡ ይህም ስለ ዘዴው በቂ እውቀት ካለመኖር የተነሳ ስለሆነ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሚመለከተው አካል መፍትሄ ቢፈልግ የተሻለ ይመስለኛል፡፡* (አባሪ‹‹18››ን ይመልከቱ)

ከላይ ከተሰጠው ምላሽ ማስተዋል የሚቻለው በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ሚናቸውን ለመወጣት ችግር እንደሌለባቸው እና በተማሪዎች ዘንድ ግን መምህራኑ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚተገብሩት ከስራ ለመሸሽ ሲሉ አድርጎ መመልከት ፣መረበሽ ወዘተ. የመሳሰሉትን ችግሮች እንደሚታይባቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ ምልከታ፣በቪድዮ ቀረፃ፣በፅሁፍና በቃል መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች የተማሪዎች ድርሻ የሰፋ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ምክንያቱም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ ተማሪዎች ዋና ተዋንያኖች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በሐወልቲና ዓይደር ሁ/ደ/ትቤት የሚገኙ ተማሪዎች በቡድን ውይይት ሀሳብ በማፍለቅና የውይይቱ ውጤት ለክፍሉ በማቅረብ፣ በአጠቃላይ የተለያዩ ተግባራት በመስራት በመሳሰሉት ተሳትፎ እንደሚያደርጉ መረዳት የተቻለ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ተማሪዎች በመምህርም ሆነ በተማሪ ጥያቄ ሲጠየቅ በህብረት የሚመልሱ መሆናቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራንምና ተማሪዎች ሚናቸውን በሚገባ የመወጣት ሁኔታቸውን ለመፈተሽ ለመምህራን በቀረበው የቃል ጥያቄ ከተገኘው ምላሽ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት እንደሚሰለቹ፣እንደሚረብሹ እና መምህራኑ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የሚተገብሩት ከስራ ለመሸሽ ሲሉ አድርጎ መመልከት አዝማሚያ እንዳላቸው መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረትም ተማሪዎች ሚናቸውን በሚገባ ይወጣሉ ብሎ መደምደም የሚያስደፍር አልሆነም፡፡

## 4.4 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች

ትምህርት ሚኒስቴር (1999) ባወጣው መመሪያ መሰረት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት፣ ደረጃቸውን የጠበቁ ቁሳቁሶች (ወንበር፣ጠረጴዛ፣ጥቁር ሰሌዳ)፣ ከአርባ ያልበለጠ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች፣ ከተማሪዎች ቁጥር ጋር የተመጣጠነ የወንበር ቁጥር መኖር እና የወንበሮቹ አቀማመጥ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ መሆን (ለመንቀሳቀስ በቂ ክፍተት መኖር) አለበት፡፡ በዚህ መሰረት በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ዘዴውን በመተግበር ሂደት የወንበሮችና የተማሪዎች ብዛት የተመጣጠነ መሆኑ፣ የወንበሮቹ አቀማመጥ ዘዴውን ለመተግበር

አመቺ መሆናቸው፣የመማሪያ ክፍሎች አቀማመጥ ከሚረብሹ ድምፆች የራቁ መሆናቸውን እና ወንበሮቹ በቀላሉ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን በክፍል ምልከታው የተተኮረባቸው ነጥቦች ነበሩ፡፡ በነጥቦቹ መሰረትም በናሙናነት በተመረጡ ሰባት ምድቦች የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት እና የተማሪዎች መቀመጫ ወንበሮች ብዛት የተመጣጠነ ነው፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎቹ ብዛት በአንድ ምድብ ከ 48-55 ነው፡፡ በአንድ ዴስክ የሚቀመጡ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ ሶስት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ዴስኮች ብዛት 20 እና ከ20 በላይ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች የዴስክ ችግር አልታየም፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ከ አርባ በላይ ስለሆነ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ሲደረግ ትምህርት ሚኒስቴር ለቋንቋ ትምህርት በሚፈቅደው መሰረት አይደለም፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች ብዛት ይታያል፡፡ በዚህ ምክንያትም መምህራን የሚረብሹና የሚማሩ ተማሪዎችን ለመለየት ሲቸገሩ ተስተውሏል፡፡

በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ በመማሪያ ክፍል ተማሪዎች የሚቀመጡባቸው ወንበሮች አቀማመጥ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ መሆን መቻል አለባቸው፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች አቀማመጥ በኔትወርክ ነው፡፡ በአንድ ኔትወርክ ውስጥ ከ 6-9 ያህሉ ተማሪዎች የተካተቱ ሲሆን 6 አባላት ላሉት ኔትወርክ ሁለትና ሶስት ዴስኮች፣9 አባላት ላሉት ኔትወርክ ሶስትና አራት ዴስኮች ተመድበዋል፡፡ የዴስኮቹ አቀማመጥን በተመለከተ የአንድ ኔትወርክ አባላት የሚቀጡባቸው ዴስኮች ፊት ለፊት ተገጣጥመው ተቀምጠዋል፡፡ የሌላው ኔትወርክም አለፍ ብሎ በተመሳሳይ ተቀምጠዋል፡፡ በየኔትወርኩ መካከል ያለውን ክፍተት በመጠኑ መንቀሳቀስ የሚያስችል ስለሆነ ዘዴውን ለመተግበር ብዙም ሲያስቸግር አልታየም፡፡

የመማሪያ ክፍሎቹ ከሚረብሹ ድምፆች የራቁ መሆናቸውን በተመለከተ የሁለቱም ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች ከመኪናና ከሌሎች የሚረብሹ ድምፆች የራቁ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች የከሰዓት ፈረቃ ሲሆን በመስኮት ከፍተኛ ፀሀይ የመግባት ሁኔታ ታይቷል፡፡ በዚህ ወቅትም ተማሪዎች ከመቀመጫ ወንበራቸው ተነስተው ፀሀይ ወደ ሌለበት አካባቢ ሲሄዱ ተስተውሏል፡፡ ይህም የኔትወርኩ አባላት ለመበታተን መንስኤ ሆኗል፡፡

Silberman (1996) እንደገለፁት የተማሪዎች አቀማመጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች ወንበር በቀላሉ የማይንቀሳቀስ ከሆነ ለአተገባበር እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሚቀመጡባቸው ወንበሮች ክብደት ያላቸው ዴስኮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ የነበራቸውን ቡድን በአዲስ መልክ ለማደራጀትና መቀመጫ ወንበራቸውን ይዘው እንዲቀያየሩ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን ተስተውሏል፡፡ ይህም ተማሪዎች አንድ ጊዜ ከተመደቡት ቡድን ውጪ ሌላ ቡድን እንዲመሰርቱ ለማድረግ የራሱ የሆነ ጫና አሳድሯል፡፡

በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ከወንበሮቹ ብዛት የተመጣጠነ፣ የመማሪያ ክፍሎች ከሚረብሹ ድምፆች የራቁና የዴስኮቹ አቀማመጥ ጥሩ ሆኖ በመገኘቱ ዘዴውን በመተግበር ሂደት የታዩ አወንታዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ዘዴውን ለመተግበር መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት አለመሆኑ፣የተማሪዎች መቀመጫ ዴስኮች ከቦታ ቦታ የማይንቀሳቀሱ በመሆናቸው፤የተማሪዎችን ቡድን በአዲስ መልክ ለማዋቀርና ሌሎች ዘዴዎችን ለመተግበር አስቸጋሪ ሆነው መገኘት ዘዴውን በመተግበር ረገድ የታዩ አሉታዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል በአሳታፊ የማስተማሪያ ትግበራ ሂደት የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎችን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረቡ ዝግ ጥያቄዎች የተገኙት ምላሾች እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ-8 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎችን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተሰጠ የነጥብ ደረጃ በቁጥርና በመቶኛ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | ያልተመለሰ |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | |
| 21. | የመማሪያ ክፍላችን በቡድን የሚሰሩ የሰዋስው ጥያቄዎች ለመስራት የሚያመች ነው | 33 | 43 | 27 | 35 | 10 | 13 | 4 | 5 | 3 | 4 | |
| 22. | የመምህራንና የተማሪዎች ፍላጎት ማነስ አሳታፊ የማስተማሪያዘዴ ለመተግበር ተፅእኖ ያሳድራል | 17 | 22 | 23 | 30 | 14 | 18 | 14 | 18 | 9 | 12 | |
| 23. | የቡድንውይይቱ ሚከናወነው በጎበዝ ተማሪዎች ነው | 22 | 28.2 | 22 | 28.5 | 7 | 9 | 13 | 17 | 13 | 17 | |
| 24. | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር የጊዜ እጥረት ይታያል | 20 | 26 | 28 | 36 | 11 | 14 | 9 | 12 | 9 | 12 | |

የመማሪያ ክፍል ሁኔታ ማለትም የቁሳቁሶች አቀማመጥ፣የክፍሉ አደረጃጀት፣ የመማሪያ ክፍሉ መስፋትና መጥበብ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ወሳኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ ጥሩ የመማሪያ ክፍል በሌለበት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር አስቸጋሪ ነው (Sqazzin and Graan 1998)፡፡ በዚህ መሰረትም በሰንጠረዥ-9 ተራ ቁ.21 የቀረበውን ሀሳብ በተመለከተ 33(43%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣27(35%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣10(13%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣4(5%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 3(4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ በሰጡት መረጃ መሰረትም የመማሪያ ክፍሉ በቡድን ለመስራት አመቺ ነው የሚለውን ሀሳብ 60(78%) የሚሆኑት ተማሪዎች የሚስማሙበት መሆናቸው 7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች የማይስማሙበት መሆናቸውንና የተቀሩት 10(13%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም የመማሪያ

ክፍሉ በቡድን ለመስራት አመቺ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያጠናክራል፡፡

Plass (1998) እንደገለፁት የተማሪዎችና የመምህራን ፍላጎት ማነስ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ ይህን ጉዳይ ለመፈተሽ በሰንጠረዥ-9 ተራ ቁ.22 የቀረበውን ሀሳብ 17(22%) ያህሉ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 23(30%) እስማማለሁ፣14(18%) ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 14(18%) አልስማማምና 9(12%) ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተማሪዎቹ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው 40(52%) ያህሉ ተማሪዎች ተፅእኖ የሚያሳድር መሆኑን እንደሚስማሙበት፣23(30%) ያህሉ ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 14(18%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንዳስቸገራቸው ነው፡፡ ከተማሪዎቹ መልስ በተገኘው መረጃ መሰረት መምህራንና ተማሪዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

በሰንጠረዥ-9 ተራ ቁ.23 የቀረበላቸውን ሀሳብ በተመለከተ 22(28.5%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 22(28.5%) የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣13(17%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልስማማምና 13(17%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት የቡድን ስራ የሚሰራው በጎበዝ ተማሪዎች ነው የሚለውን ሀሳብ 44(57%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደሚስማሙበት ፣ 26(34%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 7(9%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም የቡድን ውይይቱ የሚሰራው በተወሰኑ ተማሪዎች መሆኑን ያመለክታል፡፡

ኤልያስ (1997) Cruickshank እና ሌሎች (1991)ን ጠቅሰው እንደገለፁት በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ለማስተማር ያዘጋጁትን ይዘት በሚገባ ለማስተላለፍ፣ ለማጠናቀቅና ተማሪዎች ለማሳተፍ በቂ ጊዜ መኖር አለበት፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ በቀረበው ሰንጠረዥ ተራ ቁ.24 ለቀረበው ሀሳብ 20(26%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም

እስማማለሁ፣28(36%) ያህሉ ተማሪዎች እስማማለሁ፣11(14%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል፣9(12%) ያህሉ ተማሪዎች አልስማማምና 9(12%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተግበር የጊዜ እጥረት የሚታይ መሆኑን 48(62%) ያህሉ ተማሪዎች እንደሚስማሙበት፣ 18(24%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ እንደማይስማሙበትና የተቀሩት 11(14%) ያህሉ ተማሪዎች ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በማስተማር የጊዜ እጥረት የሚታይ መሆኑን ያመለክታል፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎችን ለመለየት ከመምራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ተራ ቁ.6 በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አሉ የሚሉዋቸውን አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ቢገልፁልኝ፡፡ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ መምህራኑ የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ አወንታዊ ገፅታዎች ብዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ መምህራን እያንዳንዱ ተማሪ ምን እንዳወቀ ለማወቅ ይረዳቸዋል፣ ተማሪዎች (ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ ከመምህር ጥገኝነት ነፃ ወጥተው እንዲማሩ፣ በስራ እንዲጠመዱ፣ ፈጣሪዎች እንዲሆኑ፣በራስ የመተማመን አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ እና የተለያዩ መፃህፍት በመፈተሽና በማንበብ ጥሩ እውቀት እንዲጨብጡ ያደርጋል)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚማሩትን ጉዳይ ሀሳብ እንዲለዋወጡበት፣ እንዲሰሩት፣ እንዲገልፁት እና እንዲፅፉት ስለሚረዳ መምህራን ያቀዱትን ዓላማ ከግብ መድረሱንና አለመድረሱን ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡

አሉታዊ ገፅታዎቹ ደግሞ ይህ ዘዴ ተግባራዊ ሲደረግ በቁጥር ትንሽ ተማሪዎች ይፈልጋል፤በዚህ ትምህርት ቤት ግን የተማሪዎች ብዛት ራሱ አንድ ችግር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች (በየኔትወርካቸው አለመቀመጥ፣መማሪያ መፅሀፍ ይዘው አለመምጣት፣ በኔትወርክ ተወያዩ፣ ተከራከሩ፣ሲባሉ ከተሰጣቸው ርእስ ጉዳይ ወጥተው (መማር ትተው) ሌላ ወሬ እንዲያወሩ ዕድል ይፈጥራል)፣ በክፍል ውስጥ ያሉት ጎበዝ፣ መካከለኛና ደካማ ተማሪዎች ሁሉም እኩል ተሳታፊዎች መሆናቸው ማረጋገጥ አያስችልም፡፡ እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ዴስኮች ከባድ መጠን ያላቸው መሆን፣የመማሪያ ክፍሉ አቀማመጥ በተለይ በስተደቡብ ያሉት የመማሪያ ክፍሎች

የከሰዓት ፈረቃ ሲሆን በመስኮት ከፍተኛ ፀሀይ የሚገባባቸው መሆን ናቸው። በአጠቃላይ ግን ይህ ዘዴ ተማሪዎች ቋንቋን በመተግበር ተሳታፊ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ከአሉታዊ ገፅታው አወንታዊ ገፅታው ያመዝናል። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ተቋቁመን እየተገበርን እንገኛለን በማለት ገልፀዋል። (ለዝርዝር ማብራሪያ **አባሪ‹‹17››ን ይመልከቱ**)

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እየተገበሩት ቢሆንም እንኳ በአተገባበሩ ሂደት የሚገጥሙዋቸው ችግሮች ግን በርካታ መሆናቸው መገንዘብ ተችሏል። ይሁን እንጂ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እነዚህ ችግሮች ቢኖሩበትም ከአሉታዊ ገፅታው አወንታዊ ገፅታው እንደሚበልጥ በማመን ተገባራዊ እያደረጉት እንደሚገኙ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ ያስረዳል። ከዚህም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እንደማንኛውም ዓይነት የማስተማሪያ ዘዴ የተወሰኑ ድክመቶች ቢኖሩትም ጠንካራ ጎኖችቹ ስለሚበልጡ ተግባራዊ ማድረጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል።

Seifu (2011) Girma (2005)ን ጠቅሰው እንደገለፁት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ መደረግ አለበት ተብሎ በሚታሰብበት ወቅት የሚዘጋጁ ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ሆነው መቅረብ አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን ዘዴውን በመተግበር ሂደት የራሱ የሆነ ተፅእኖ ያሳድራል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ ተራ ቁ.7 የሚያስተምሩበት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ናቸው ይላሉ? መልስዎ አዎ (አይደለም) ከሆነ ምክንያትዎን ቢያብራሩልኝ። ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራኑ ካላቸው ጊዜ አንፃር፣ ከተማሪዎች ብዛት፣ ዘዴውን ለመተግበር የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ካለመሟላት ውጪ በመማሪያ መፅሀፉ ያሉትን ሰዋስዋዊ ይዘቶ ዘዴውን ለመተግበር ምንም ችግር እንደሌለባቸው እና አመቺ እንደሆኑ ገልፀዋል። (ለተጨማሪ ዝርዝር **አባሪ ‹‹20››ን ይመልከቱ**)

መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር የሚያስከትሉት ችግር አለመኖሩና አመቺ መሆናቸው ነው።

መምህራን የተለያዩ ይዘቶችን በሚያስተምሩበት ጊዜ እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው የሚመሩበት የመምህር መምሪያ ያስፈልጋቸዋል። ይህም የመማር ማስተማር ሂደቱ የተቃና እንዲሆንና መምህራኑ ለተመሳሳይ ጥያቄ የተለያየ ምላሽ እንዳይመልሱ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። በሐወልቲና ዓያደር ሁ/ደ/ት/ቤት የሚገኙ መምህራንስ የመምህር መምሪያ ይኖራቸው ይሆን? ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ተራ ቁ.8 ሰዋስዋዊ የሆኑ ይዘቶችን እንዴት ማስተማር እንዳለባችሁ የመምህር መምሪያ ላይ የተገለፀ ነገር አለ? ካለ ቢገልፁልኝ። ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ  መምህራኑ የመምህር መምሪያ እንደሌላቸው ገልፀዋል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንድ መምህር ሲገልፁ፣

> *…እህ አይደለም ሰዋስው ብቻ ለማስተማር የሚያገለግል የመምህር መምሪያ በአጠቃላይ አማርኛን ለማስተማር የሚያገለግል መምሪያም የለንም። የተሞክሮ ልውውጥ በማድረግ ብቻ እናስተምራለን።* **(አባሪ ‹‹20››ን ይመልከቱ)**

ከላይ ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ የሚያስተምሩዋቸውን ይዘቶች እንዴት ማስተማር እናዳለባቸው የሚመራ የመምህር መምሪያ አለመኖሩ ነው።

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን ዘዴውን በተመለከተ ስልጠና መውሰድ አለባቸው። ይህ ያስፈለገበት ምክንያት Tudor (1996) እንደገለፁት መምህራኑ በመምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ሲያደርጉ ቆይተው በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለማስተማር አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ስለሚችል ነው። በዚህ መሰረትም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን በዜዴው ለማስተማር ስልጠና ያገኙበትን ሁኔታ መኖሩ ለመፈተሽ ከመምህራን ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ በተራ ቁ.9 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የወሰዱት ስልጠና አለ? ካለ ቢገልፁልኝ። ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራኑ ዘዴውን የሚተገብሩት በትምህርት ጉዞ ካገኙት እውቀት እና እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው እርስ በርስ በመነጋገር እንጂ በትምህርት ቤቱ የዘዴውን አተገባበር በተመለከተ የተሰጣቸው ስልጠና አለመኖሩን ገልፀዋል።

በአጠቃላይ በአራቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተገኘው መረጃ መሰረት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ሲደረግ የታዩ አወንታዊ ገፅታዎች መምህራን ተማሪዎችን በቡድን እንዲቀመጡ አድርገው የሚሰራውን ስራ እየተወያዩ እንዲሰሩ መደረጉ፣ ተማሪዎች ከውይይት ያገኙትን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ መደረጉ፣ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ዕድል መስጠቱ፣ ተማሪዎች በቡድን ሲወያዩ መምህራን እየዞሩ መከታተላቸውና እገዛ ማድረጋቸው፣ ተማሪዎችም ለውይይት የተሰጣቸውን ርእሰ ጉዳይ  እየተወያዩ መታየታቸው፣ የተማሪዎቹ ብዛትና የወንበሮቹ ብዛት መመጣጠናቸው፣ የወንበሮቹ አቀማመጥ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ሆነው መገኘታቸው፣ የመማሪያ ክፍሎች አቀማመጥ ከሚረብሹ ድምፆች ነፃ መሆናቸው፣ ስዋስዋዊ ይዘቶቹ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ሆነው መገኘታቸው፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ በብዛት ክፍለ ጊዜውን በተሳትፎ የሚሸፈነው በተማሪዎች መሆኑን ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ በመማሪያ ክፍሉ የሚገኙ የተማሪዎች መቀመጫ ወንበሮች ከቦታ ቦታ የማይንቀሳቀሱ ሆነው መገኘታቸው፣የመማሪያ ክፍሎች አቀማመጥ ከፍተኛ ፀሀይ የሚገባባቸው መሆኑ፣የቡድን ውይይት ሲሰጡ በተወሰኑ ተማሪዎች እንዲሰራ ዕድል መስጠቱ፣ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የመሰላቸት ባህሪ ማሳየታቸው፣ የተማሪዎችን ቁጥር መብዛቱ፣ የክፍለ ጊዜ እጥረት መታየቱ እና ተማሪዎች ሲወያዩ ውይይቱን ወደ ረብሻ እንዲቀይሩት መንገድ መክፈቱ ዘዴው ተግባራዊ ሲደረግ የተስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራን (አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ከሚባሉት የተወሰኑ ዘዴዎች ላይ መወሰናቸው፣ የሚያስተምሩት ርእስ ዓላማ አለማስተዋወቃቸው፣ተማሪዎች ከቤተ መፃህፍት የሚሰሩዋቸው ስዋስዋዊ ይዘቶችን አለማዘጋጀታቸው አለመስጠታቸው፣ ተማሪዎች እየተወያዩ የሚሰሩትን የክፍል ስራ ሲሰጡ የመወያያና የመፃፍያ ጊዜ አለመለየታቸው)፣ መምህራን በዘዴው ዙሪያ የወሰዱት ስልጠና አለመኖሩና ተማሪዎች ደግሞ ዘዴውን በተመለከተ ግንዛቤ አለመኖራቸው ዘዴውን ሲተገበር የታዩ አሉታዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡

በመጨረሻ መምህራኑ ስለ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ያላቸውን አስተያየት እንዲገልፁ በቃለ መጠይቁ ተራ ቁ.10 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዘዴ ተማሪዎች የሚማሩት ነገር እየተገበሩት

እንዲያልፉ፣ ተዘጋጅተው እንዲመጡ፣ ጥሩ ተናጋሪና ፀሀፊ እንዲሆኑ፣ሀላፊነት እንዲወስዱ፣ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና በተለይ ሴቶች ሀፍረትን እንዲያስወግዱ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እኛ የምንፈልገው ተማሪዎች ተምረው ነገ በራስ በመተማመን የሚናገሩ፣ የሚፅፉ፣ የሚያነቡና የሚያስረዱ እንዲሆኑ ነው፡፡ ይህም ስኬታማ የሚሆነው በክፍል ውስጥ ተሳታፊ በመሆን መሰረት ይዘው ሲወጡ ነው፡፡ ስለዚህ ነገ አገርን የሚመሩ፣ ችግር የሚፈቱ ተማሪዎች ለማፍራት የግድ በክፍል ውስጥ መለማመድ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ሰዋስውም ይሁን ሌሎች ይዘቶች ማስተማር ውጤታማ እንዲሆን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መኖርና መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ሂደቱ ስኬታማ የሚሆነው የተማሪዎቹ ቁጥር አነስ ብሎ፣በቂ መሳሪያዎች ተሟልተውና በቂ ክፍለ ጊዜ ሲኖር ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ (ለዝርዝር ሀተታ **አባሪ ‹‹19›› ን ይመልከቱ**)

በአጠቃላይ መምህራን ከሰጡት አስተያየት መረዳት እንደሚቻለው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ከመምህር ጥገኛነት ነፃ በመሆን ስለሚማሩት ጉዳይ በመጠየቅ፣ በመመለስ፣ በመወያየት፣ በመከራከር፣ በመመራመርና ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩበት ነው፡፡ ይህም ቋንቋን በማዳመጥ ከመማር አልፎ ቋንቋን ለመከወን ተወዳዳሪ የለውም፡፡ ስለዚህ ማስተማር ስኬታማ በሆነ መንገድ ለማካሄድ እና ተማሪዎች ጥሩ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ለወደፊቱም መቀጠል ያለበት ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ስኬታማ ለማድረግ ዘዴውን ለመተገግበር የሚያስፈልጉ ነገሮች መሟላት አለባቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሐወልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን እንዴት እንደሚተገብሩት መፈተሽ ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹም በሐውልቲና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን ሲያስተምሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት መፈተሽ፣ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የመምህራንና የተማሪዎች ሚና መለየት እና በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ሂደት የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች መለየት የሚሉት ናቸው፡፡ ለዚህም በ2004 ዓ.ም በማስተማር ላይ የሚገኙ አራት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ሰባት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች በጥናቱ ታቅፈዋል፡፡ በናሙናነት ከተወሰዱት መምህራንና ተማሪዎች ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በክፍል ውስጥ ምልከታ፣በቪድዮ ቀረፃ፣ በፅሁፍ መጠይቅ፣ በቃለ መጠይቅ እና እንዳስፈላጊነቱም በፎቶግራፍ በመታገዝ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት ከተገኘው ውጤት በመነሳት ከዚህ በታች የቀረቡትን ማጠቃለያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- ❖ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት መረጃዎቹ ጠቁመዋል፡፡ ይህም መምህራኑ የቡድን ውይይት፣ የጥያቄና መልስ እና የክፍል ስራ የሚሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች ብቻ በተደጋጋሚ ይተገብራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከነዚህ ውጪ ለምሳሌ፣የቤት ስራ፣የጥንድ ስራ የመሳሰሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች አይተገብሩም፡፡

- ❖ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅመው ሲያስተምሩ የሚያስተምሩትን ርእስ በማስተዋወቅ፣ ቅድመ ትምህርት ጥያቄዎችን

በማቅረብ፣የቡድን ውይይት በመስጠት፣የቡድን ውይይቱን አሰራር በሚገባ በመግለፅ፣በውይይቱ ወቅት እየዞሩ በመከታተል፣የተማሪዎች ምላሽ በማጠናከር፣ ተማሪዎች የሚሳተፉበት መንገድ በማመቻቸት፣ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት፣ ተማሪዎችን በማበረታታትና ማጠቃለያ በመስጠት ሚናቸው ተጫውተዋል፡፡ ነገር ግን የዕለቱ ትምህርት ዓላማ አለማስተዋወቅ፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል በቡድን ውይይቱ ላይ ያለውን ድርሻ አለመግለፅ፣ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ ሲያዝዙ ስራው የሚፈጀው ጊዜ ቀድሞ አለማሳወቅ፣ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ የሚሰሩዋቸው ሰዋስዋዊ ያዘቶች አዘጋጅቶ አለመስጠት፣የማይሳተፉ ተማሪዎች እንዲሞክሩ አለማድረግ እና አልፎ አልፎ ደግሞ ትክክለኛ መልስ አለመስጠት ችግሮች ተስተውሎባቸዋል፡፡

- ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በቡድን በመወያየት፣ከውይይት ያገኙትን ውጤት ለጓደኞቻቸው በማንፀባረቅ፣የተሰጣቸውን ስራ ሀላፊነት ወስደው በመስራት፣ጥያቄ በመመለስ፣በአጠቃላይ ያለ ፍርሃት በንቃት በመሳተፍ ሚናቸው ተጫውተዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ያልገባቸውን አለመጠየቅ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች በቡድን ውይይት አለመሳተፍ፣ አንዳንድ ጊዜ የመሰላቸት ባህሪ ማሳየት እና ውይይቱን ትተው ወደ ሌላ ወሬ በመግባት እንደሚረብሹም ተስተውሏል፡፡

- በአንድ ቡድን ውስጥ የተደራጁ ተማሪዎች ብዛት ከ 6-9 ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በአንድ ቡድን የሚደራጁት ውጤታቸውን እና ከትምህርት ቤት ውጪ በቅርበት የሚገናኙበት ሁኔታ መሰረት ተደርጎ ነው፡፡ በአንድ ቡድን ውስጥ የተደራጁ ተማሪዎች አንድ ጊዜ ከተመደቡ አመቱን ሙሉ አብረው በአንድነት ይዘልቃሉ፡፡

- በመማር ማስተማር ሂደቱ ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ጊዜ በቂ አለመሆኑ ከመምህራንና ከተማሪዎች በተገኘው መራጃ መረዳት ተችሏል፡፡

- መምህራን ቀደም ሲል አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር እውቀትና ክሂል ያገኙት በትምህርት ሲሆን አሁን ደግሞ በጋራ በሚያደርጉት መተጋገዝና በግል

ጥረታቸው አተገባበሩን ለማጎልበት እንደሚሞክሩ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውጪ መምህራን የዘዴውን አተገባበር በተመለከተ እውቀትን ለመጨበጥ የወሰዱት ስልጠና የለም፡፡

- በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ወንበሮች መካከል ያለው ክፍተት በቂ በመሆኑ ዘዴውን ተግባራዊ ሲደረግ የጎላ ችግር ሲያስከትል አልታየም፡፡ ይሁን እንጂ በመማሪያ ክፍሉ የሚገኙት ወንበሮች ለማንቀሳቀስ የሚከብዱና ቡድኖችን እንደ አዲስ ለመመደብ የሚያስቸግሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ዘዴውን ተግባራዊ ለማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር ከሚፈቅደው በላይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መምህራን ዘዴውን ተጠቅመው ለማስተማር አመቺ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ነገር ግን መምህራኑ ሰዋስዋዊ ይዘቶችንም ሆነ ሌሎች ይዘቶች ለማስተማር መንገድ የሚመራቸው የመምህር መምሪያ የላቸውም፡፡ መምህራኑ የሚያስተምሩት ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ቋንቋ መምህራን ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግና እንዴት እንደሚያስተምሩ እርስ በርሳቸው ሰብስባ አድርገው በመወሰን እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

- ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ሆነው መገኘታቸው ፣የወንበርና የተማሪዎች ቁጥር መመጣጠኑ፣ በወንበሮቹ መካከል ያለው ክፍተት በቂ መሆኑ፣ የመማሪያ ክፍሎች ከሚረብሹ ድምፆች ነፃ መሆናቸው፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን፣ በቡድን ሆነው የሚቀመጡባቸው አቀማመጦች የቡድን አባላት መቀራረብንና እርስ በርስ መተያየትን የሚፈጥሩ መሆናቸው በክፍል ውስጥ አደረጃጀት አወንታዊ ሁኔታ የሚንፀባረቅባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በቡድን በሚሰሩበት ወቅት ሁሉም ድርሻቸውን መወጣታቸው ማረጋገጥ አለማስቻሉ፣ ሰፊ ጊዜና ጥቂት የተማሪ ቁጥር መፈለጉ እና በውይይት ወቅት ተማሪዎች የሚረብሹበት ዕድል መፍጠሩ፣ አሉታዊ ገፅታዎቹ መሆናቸው መረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

በሐወልቲና ዓይደር ሁ/ደ/ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር የሚታዩባቸውን ችግሮች በማስተካከል፣ለወደፊቱ በተሻለ ሁኔታ ዘዴውን ተግባራዊ ያደርጉት ዘንድ፣ አጥኚዋ የሚከተሉትን መፍትሄ ሀሳቦች አቅርባለች፡፡

- ✓ መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ስር ከሚካተቱት የቡድን ውይይት፣ ጥያቄና መልስ እና የክፍል ስራ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከመጠቀም ውጪ የቤት ስራ፣የቡድን ስራ፣ የጥንድ ስራ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች እያቀላቀሉ ቢጠቀሙ፣

- ✓ በመማር ማስተማር ሂደት የዕለቱ ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች ማስተዋወቅ በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ተማሪዎች ምን ማወቅ እንደሚጠበቅባቸው እንዲያውቁ ይረዳል፡፡ ስለዚህ መምህራኑ የዕለቱ ትምህርት ዓላማ የማስተዋወቅ ልምድ እንዲኖራቸው ጥረት ቢያደርጉ፣

- ✓ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የሁሉም ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን በቡድን በሚሰሩ ተግባራት ሁሉም የቡድን አባላት ተሳትፎ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስልቶችን አዘጋጅተው ቢጠቀሙ፣

- ✓ ተማሪዎች የሚሰሩት ተግባር በሚሰጥበት ጊዜ የተሰጣቸውን ጊዜ አስቀድሞ ማሳወቅ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ማንኛውም ዓይነት ተግባር ተማሪዎች እንዲሰሩ ሲያዝዙ ለስራው የተሰጣቸውን የጊዜ መጠን ቀድመው ቢያሳውቁ፣

- ✓ ሰዋስውን በመማር ማስተማር ሂደት መምህራኑ ተደጋጋሚ ዕድል የሚሰጡት በተደጋጋሚ ለሚሳተፉ ተማሪዎች ነው፡፡ ስለዚህ መምህራኑ እጃቸውን በማውጣት የማይሳተፉ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ቢያነሳሱ፣

- ✓ የሰዋስው እውቀት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ በማድረግ ብቻ ላይዳብር ይችላል፡፡ ስለዚህ መምህራኑ የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በቤታቸው እንዲለማመዱ ቢያደርጉ፣

- ✓ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚደራጁ ተማሪዎች በቅርበት ከሚገናኙበት አንፃር መመደቡ በሌላ አካባቢ ከሚገኙ ተማሪዎች አዲስ እውቀት እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ ጊዜ የተመሰረቱትን ቡድኖች ዓመቱን ሙሉ እንዲዘልቁ መደረጉ ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እውቀታቸውን እንዳይቀያየሩ ከማድረጉም ውጪ በቡድን አበላቱ መሰላቸት ሊከሰት ይችላል፡፡ ስለዚህ የሚደራጁ ቡድኖች በወር፣ በሁለት ወር ወዘተ. የሚቀያየሩበትና እውቀታቸውን የሚለዋወጡበት መንገድ ለመፍጠር ተማሪዎች ቢቀላቀሉና በየወቅቱ አዳዲስ ቡድን ቢመሰረት፣

- ✓ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር እንቅፋት ከሆኑት አንዱ የጊዜ እጥረት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ችግር ለመቅረፍ የሚመለከተው አካል የበኩሉን አስተዋፅኦ ቢያደርግ፣

- ✓ በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ሂደት የተወሰኑ ተማሪዎች የመሰልቸት ባህሪ እንደሚያሳዩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ዘዴውን በተመለከተ ግንዛቤ ስለሌላቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራኑ ዘዴውን የሚተገብሩት ከትምህርትና ከልምድ ባገኙት እውቀት ነው፡፡ ስለዚህ ዘዴውን በተመለከተ ለተማሪዎቹ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ለመምህራኑ ደግሞ ያላቸውን እውቀት ማሳደጊያ ስልጠና ለመስጠት የሚመለከተው አካል መፍትሄ ቢፈልግለት፣

- ✓ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ዴስኮች (ወንበሮች) ከባድ ከመሆናቸው የተነሳ ተማሪዎች ወደ ተለያየ ቦታ በመንቀሳቀስ ቡድኖች እንደ አዲስ ማደራጀት አልተቻለም፡፡ ስለዚህ ወንበሮቹ በቀላሉ የሚንቀሳቀሱና ባለ መደገፊያ ወንበሮች የሚሆኑበት መንገድ ቢመቻች፣

- ✓ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በአንድ ክፍል ከ50 በላይ ነው። ከብዛታቸው የተነሳ እያንዳንዱን ተማሪ በተገቢው መንገድ ለመገምገም ያስቸግራል። ስለዚህ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ወደ 40 ዝቅ እንዲል የሚመለከተው አካል ጥረት ቢያደርግ፣

- ✓ በመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የመምህር መምሪያ ነው። የመምህር መምሪያ መምህራን የማያውቁትን ወይም የሚጠራጠሩትን ነገር ለማረጋገጥ ይረዳል። ስለዚህ የመምህር መምሪያ በማሰራጨት ዙሪያ የሚመለከተው አካል መፍትሄ ቢያበጅለት፣

## ዋቢ ጽሁፎች


ሙሉጌታ ይታየው:: (1996):: "የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮተቤ መመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት መርሃ ግብር እንደታየው::"አማርኛን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)::

ትምህርት ሚኒስቴር:: (1986):: *አዲሱ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ*:: አዲስ አበባ ፣ኢ.ት.መ.ማ.ድ::

------------------------::(1990):: "ትምህርት መርሀ -ትምህርት::" አዲስ አበባ፣ በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት በቋንቋ ትምህርት ብዱን የተሰናዳ:: (ያልታተመ)::

---------------------------::(1999):: "የኢትዮጵያ መምህራን ልማት መመሪያ::" አዲስ አበባ::

ባየ ይማም:: (1987):: *የአማርኛ ሰዋስው::* አዲስ አበባ፣ የት.መ.ማ.ማ. ድርጅት::

ጌታሁን አማረ:: (1990):: *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ::* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

ኤልያስ አድማሱ:: (1997):: "በኦሮምያ መምህራን ኮሌጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ::" አማርኛን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)::

ደረጀ ነጋሽ:: (1999):: "የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረማርቆ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር::" አማርኛን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)::

ዑመር ዳውድ:: (2002):: "የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን የንኡስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር::" አማርኛን

በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት። (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ ።(2001)። *የምርምር መሰራታዊ መርሆችና አተገባበር*። ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

Azeb Desta.(1984). "Elements of General Methods of Teaching. Knowledge and Competencies for Teachers." Department of Curriculum and Instruction, Faculty of Education. Addis Ababa University. (Unpublished Module).

Bedilu Teka. (2011). "Teachers' Participation of Active Learning and Their Classroom Practices in English Language Classes of Mettu Secondary and Preparatory School." Addis Ababa University. Unpublished Masters Thesis.

Bonwell,C and Eison.(1991). *Active Learning.* Creating Excitement in the Classroom. Rhen: Grips.

Borich,G.(1984). *Effective Teaching Method.* New York: Merrill.

Brumfit,C.(1984). *Communicative Methodology in Language Teaching.* Cambridge: CUP.

Carter,R.(1990).*Knowladge abaout Language and the Curriclum.* Hadder Stoughter: London Sydney Auckland.

Cohen,E.(1994). *Restructuring the Classroom: Conditions for productive Small groups.* Retrieved From: http://www. Julieboyd. Com.au/ILF/pages/members/act/bkovervus/tandlearn pdfs/design-group work:pdf/.

Doff, A.(1988). *Teach English.* Cambridge : Cambridge University Press.

Getachew Adugna. (2001). "Three Modules of in the Teaching of Secondary School Amharic Subject Area Methodology (A Distance Education material for Special in- service Trainees)."Department of Curriculum and Instruction, Facility of Education.Addis Ababa University. (Unpublished Moudle).

Hand Book of Higher Diploma Program for Teacher Educators (2011). Ministry of Education. Addis Ababa: Ethiopia.

Harmer,J.(1978). *Teaching and Learning Grammer.* Hong Kong: Longman Group.

--------------(1991).*the Practice of English Language Teaching.* Longman: London and New York.

Hock,L.E, (2009). *Classroom Grouping for Effective Learning.* Retrieved From http://www.ascd.org/ASCD/pdt/Journals/ed- lead/el-196104- hock.pdf.

ICDR.(1999). *Teachers' Educational Handbook.* Addis Ababa: Institute of Curriculum Development and Research.

Kelly,L.G.(1976). *25 Centuries of Language Teaching.* Massachusetts: Newbury House Publishers.

Littlewood, W.(1981). *Communicative Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Lyons,J.(1968). *Introduction to Theoretical Linguistics.* Cambridge: Cambridge University Press.

MOE (1994). "The Teacher Education System Overhaul (TESO) Program Policy Document. Addis Ababa: Ministry of Education. (Unpublished).

Muttusa,N.G. and Wills, G.M (1995). *Modern Practice in Education and Science.* Gaborone: Bots Wana.

Nunan,D.(1988).*The Learner-Centered Curriculum.* Cambridge: Cambridge University Press.

Petty,G.(2004).*Teaching Today.* Nelson Thormes: a Wolters Kluwer Business.

Plass,H. (1998). "The Learner-Centered Classroom" In Amare Asgedom etal.(ED).Quality of Education In Ethiopia : Version of 21st Centaury. Addis Ababa: IER.

Rechards,J. and Rodgers,T.(1986).*Approaches and Methodes In Language Teaching : A Description and Analysis.* Cambridge: Cambridge University Press.

-------------------. (2001). *Approaches and Methods in Language Teaching.* Cambridge: CUP.

Seifu Berihu.(2011) "Implementation of Active Learning Method in Spoken English Classes With University Students in Focus." Unpublished Masters thesis. Addis Ababa University.

Silberman,M. (1996). *Active Learning: 101 Strategies to Teach Any subject.* Boston: Allyn and Bacon.

Sqazzin,T. and Graan, M.V, (1998). *Education Reform and Innovations in Namibia.* Okahandja: Namibia.

Temesgen Engida (2002.) "Teaching Primary School Subjects using Learner Centered Methodology." *In The Ethiopia Journal of Educational researchers Association,* Vol, 1 (1), 31-45).

Tudor,I.(1993). "Teachers' Role in the Learner- Centered Classroom." *ELT Journal,* Vol. 8(3),22-32

------------(1996). *Learner Centeredness as a Language Education.* Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P.(1988). *Grammer Practice Activities: A Practical Guide for Teacher.* Cambridge: Cambridge University press.

Widdwoson, H.G (1987). "Roles of Teacher and Learner." *ELT Journal,* Vol. 41(2), 83-87).

## ድረ ገፅ

*Active Learning and Teaching Methods Rationale.* Retrieved From: http://www.nicurriculum.org.uk/docs/key_stage_3/ALTM-KS3.pdf.

*Active teaching strategies and learning activities.* Retrieved From: http://samples.jbpub.com/9780763749453/49451_CH09_FINAL.pdf.

*Approaches Teaching Grammer.* Retrieved From፡ http://www.teachingenglish.org.uk/polls/approaches-teaching-grammar

*pedagogical grammar* . Retrieved From፡ http://en.wikipedia.org/wiki/Pedagogical_grammar

*Pedagogical grammar.* Retrieved From፡ http://www.wisegeek.com/what-is-a-pedagogical-grammar.htm

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

Active Participant -ንቁ ታሳታፊ

Participatory Teaching Method -አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ

Passive Reciptant - ፍዝ ተቀባዮች

Teacher Centered Method -መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ

# አባሪዎች

**አባሪ-1፡- የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ (Check List)**

ይህ የምልከታ መከታተያ ቅፅ **በክፍል አንድ** አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን ነጥቦችና እና **በክፍል ሁለት** ደግሞ የክፍል ውስጥ አደረጃጀትን (የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታ ፣ የተማሪዎች ቁጥር ከወንበሮች ጋር መመጣጠን፣ የተማሪዎች አቀማመጥ) የሚመለከቱ ነጥቦች አካቷል። ምልከታ አድራጊው ሰው በመረጠው ተራ ቁጥር ትይዩ ይህን (×) ምልክት በማድረግ ምልከታውን አከናውኗል።

## አጠቃላይ መረጃ

የትምህርት ቤቱ ስም ____________

ምድብ __________

የትምህርት ርዕስ ____________

የምልከታ ዙር ____________ ቀን ____________

ትምህርቱ የተጀመረበት ሰዓት ____________

ትምህርቱ ያለቀበት ሰዓት ____________

የተማሪዎች ብዛት ወንድ ____________ ሴት __________

**ክፍል-አንድ፡-** የሰዋስው ይዘቶችን በማስተማር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በተመለከተ

| ተ.ቁ | የተተኮረባቸው ነጥቦች | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1. | በሰዋስው መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ ተደርጓል | | |
| 2. | የክፍል ስራ ተሰጥቷል | | |
| 3. | በሰዋስው መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በጥንድ እንዲወያዩ ተደርጓል | | |
| 4. | በትምህርቱ ጣልቃ ጥያቄ የመጠየቅና የመመለስ ዘዴ ተተግብሯል | | |
| 5. | መምህሩ ዘዴዎችን በማቀላቀል ተጠቅመዋል | | |
| 6. | በክፍለ ጊዜው በብዛት ሲሳተፉ የሚታዩት ተማሪዎች ናቸው | | |
| 7. | በክፍለ ጊዜው በብዛት ሲሳተፉ የሚታዩት መምህራን ናቸው | | |
| 8. | መምህሩ የዕለቱ ትምህርት አስተዋውቀዋል | | |
| 9. | መምህሩ የትምህርቱ ዓላማ አስተዋውቀዋል | | |
| 10. | መምህሩ የተማሪዎችን የቅድመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎች አቅርበዋል | | |
| 11. | መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የቡድን መሪ ፣ፀሀፊና ሌሎች አባላት በወጉ አደራጅተዋል | | |
| 12. | መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን ሲወያዩ እየተዘዋወሩ በመከታተል እገዛ አድርገዋል | | |
| 13. | ተማሪዎች ሀሳባቸው ካንፀባረቁ በኋላ መምህሩ ገለፃ በመስጠት የተማሪዎችን ሀሳብ አጠናክረዋል | | |
| 14. | መምህሩ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተመፃህፍትና ከሌሎች ምንጮች አፈላልገው በቡድን የሚሰሩዋቸው ጥያቄዎች ሰጥተዋል | | |
| 15. | መምህሩ በንቃት ለሚሳተፉ ተማሪዎች ማበረታቻ ቃላት ተጠቅመዋል | | |
| 16. | መምህሩ ለተጠየቁት ጥያቄዎች በቂ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል | | |
| 17. | ተማሪዎች በጥንድ የተሰጣቸውን ጥያቄ ለመመለስ በንቃ ተሳትፈዋል | | |
| 18. | ተማሪዎች በቡድን የተሰጣቸውን ጥያቄ ለመመለስ ተሳትፈዋል | | |
| 19. | ተማሪዎች በግል የተሰጣቸውን ጥያቄ ለመመለስ ተሳትፈዋል | | |
| 20. | ተማሪዎች ከቡድን ውይይት፣ከጥንድና ከቡድን ስራ ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው አንፀባርቀዋል | | |
| 21. | ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ ተሳትፈዋል | | |
| 22. | ተማሪዎች መምህርም ሆነ ተማሪ ሲጠይቅና ሲመልስ በጥሞና ያዳምጣሉ | | |
| 23. | ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፅፈዋል | | |

**ክፍል ሁለት፡-** የክፍል ውስጥ አደረጃጀትን በተመለከተ

| ተ.ቁ | የተተኮረባቸው ነጥቦች | ነው | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | የወንበሮችና የተማሪዎች ብዛት የተመጣጠነ ነው | | |
| 2. | ወንበሮቹ በቀላሉ የሚንቀሳቀሱ ናቸው | | |
| 3. | የወንበሮቹ አቀማመጥ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ነው | | |
| 4. | የመማሪያ ክፍሉ ከሚረብሹ ድምፆች የራቀ ነው | | |

**አባሪ-2፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-1 ምድብ** ‹‹G1››

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድበ- G

ክፍለ ጊዜ -2ኛ

ሰዓት 7፡10-7፡50

ቀን- 11/04/2004

የመምህሩ ስም መምህር-1

የተማሪዎች ብዛት - 50

መምህርቷ ወደ ክፍል እንደገቡ የተለመደውን ሰላምታ አቀረቡ፡፡ በመቀጠል ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ለሁለት በመክፈል በስተግራ በኩል፡- ‡

አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውንና ቀን ፃፉ፡፡ ከዚያም መምህርቷ ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ ምን እንደተማሩ ተማሪዎቻቸውን ጠየቁ: ተማሪዎችም "የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች" በማለት መለሱ፡፡ መምህርቷም ተማሪዎች ምሳሌ እንዲሰጡዋቸው የአንድ ኔትዎርክ ስም ጠሩ፡፡ የኔትወርኩ አንድ አባል ከወንበሩ በመነሳት "ለምሳሌ፡- **መጠነ** የሚለውን ቃል ብንወሰድ ተመሳሳይ ፍቹ **ለካ** ሲሆን ተቃራኒ ፍቹ ደግሞ **ገመተ** ነው፡፡" በማለት መለሰ፡፡ በመቀጠል መምህርቷ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ ቁጥርን በተመለከተ መሆኑን በማስተዋወቅ ተማሪዎች በዚህ ዙሪያ የሚያወቁትን እንዲናገሩ እድል ሰጡ፡፡ በማስከተልም "የአማርኛ ቁጥሮች በስንት ይከፈላሉ?፣ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር ለመቀየር የምንጠቀምበት ስልትስ ምንድን ነው?" የሚሉትን ሁለት ጥያቄዎች በመጠየቅ ለአምስት ደቂቃ ያህል በየኔትወርካቸው እንዲወያዩ አደረጉ፡፡ በወቅቱም መምህርቷ ተማሪዎች እየተወያዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥና ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ በየኔትወርኩ በመዞር ይከታተሉ ነበር፡፡ ከተወሰነ ደቂቃ ቡኋላም

---

‡ 1. አማርኛ፡- መምህራኑ የትምህርቱ ዓይነት ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው

2. (የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት፣ ያ- ደራሲ እና ተማሪው)፡- የምንባቡ ርዕሶች

3. ክፍል አራት- ሰዋስው፡- መምህራኑ በአራተኛው ክፍል የሚያስተምሩት ሰዋስው እንደሆነ ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ነው፡፡

የተሰጣቸውን ደቂቃ እንዳለቀ ነግረው ኔትወርክ ስድስትን በመጥራት የኔትወርኩ አባላት ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ጋበዙ። አንድ የኔትወርኩ አባልም ከወንበሩ በመነሳት ቆም ብሎ "የአማርኛ ቁጥሮች በስንት ይከፈላሉ? ለሚለው በሁለት ነው። እነሱም፡- **ነጠላ** እና **ብዙ** ቁጥር ናቸው። ነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር ለመቀየር የምንጠቀምበት ስልት ደግሞ አብገር ቅጥያዎችን በመጨመር ነው።" በማለት መለሰ። መምህርቷ አሁንም ኔትዎርክ አምስትን በመጥራት ለተሰጠው ማብራርያ ምሳሌ እንዲሰጡ ጠየቁ። አንድ ሴት ተማሪ ከወንበሯ በድግ ብላ በመቆም "ለምሳሌ፡- **ቤት** በሚለው ቃል **-ኦች** የሚለውን አብገር ምዕላድ ከኋላ ሲጨመርበት **ቤቶች**፣ **አበበ** በሚለው ቃል **እነ-** የሚለውን አብገር ምዕላድ ከፊት ሲጨመርበት **እነ-አበበ** ይሆናል።" በማለት መለሰች። አሁንም የሌላ ኔትዎርክ አባል ከወንበሩ በመነሳት "**ቃል** በሚለው **-ኣት** የሚለውን አብገር ምዕላድ ከኋላ በመጨመር **ቃላት**፣ **በሬ** በሚለው **-ዎች** የሚለውን አብገር ምዕላድ ከኋላ በመጨመር **በሬዎች** ይሆናል።" በማለት መለሰ። በመቀጠል መምህርቷ ተማሪዎቹን "በጣም ጎበዞች" በማለት አበረታትተው አራት ቃላት ጥቁር ሴሌዳ ላይ ፃፉ። ለእያንዳንዱ ቃልም የአማርኛ እና የግእዝ አብገር ምዕላዶችን በመጨመር በአማርኛ እና በግዕዝ እንዴት እንደሚበዙ አስረዱ።

ከዚያም መምህሩ አንድ ነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር ለመቀየር የሚጠቅሙ ስልቶች ምን ምን መሆናቸውን ተማሪዎች ማጠቃለያ እንዲሰጡ ጠየቁ። ተማሪዎችም "ጥገኛ ምዕላዶችን በመጨመር ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር መቀየር ይቻላል።" በማለት ማጠቃለያ ሰጡ። መምህርቷም **እነ**፣ **ኦች**፣ **ዎች** ወዘተ. የአማርኛ ቅጥያቂዎች ሲሆኑ **-ኣት** ደግሞ የግዕዝ ቅጥያ መሆኑን በመግለፅ የተማሪዎችን ማጠቃለያ አጠናከሩ። በመቀጠል መምህርቷ በመማሪያ መፅሀፋ ገፅ 59-60 በ ‹‹ሀ›› ስር የሚገኙትን ቃላት ቀደም ብሎ በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት እየተወያዩ የክፍል ስራ እንዲሰሩ ተማሪዎቹን አዘዙ። ተማሪዎችም የተወሰኑ እየፃፉ በመወያየት፣ የተወሰኑት ደግሞ ውይይቱን ትተው ደብተራቸው ላይ በመፃፍ የክፍል ስራውን መስራት ጀመሩ። መምህርቷም መፃፉን ትተው መጀመሪያ እንዲወያዩ በመንገር እየዞሩ ሲከታተሉ ተስተውሏል።

መምህርቷ የተሰጣቸው ጊዜ እያለቀ ስለሆነ ማጠናቀቅ እንዳለባቸው ተማሪዎችን በመንገር እንዲሰሩዋቸው የሰጡዋቸውን ቃላት ጥቁር ሴሌዳ ላይ ፃፉ። ከዚያም

ተማሪዎች **የቃላቱን አማርኛና ግዕዝ እርባታ** ጥቁር ሴሌዳ ላይ እየወጡ እንዲፅፉ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም እየወጡ መልሶችን ፃፉ፡፡ አስከትለውም መምህርቷ የቀሩትን ጥያቄዎች በቃል እንዲሰሩ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ለእያንዳንዱ ቃል በአማርኛ እና በግእዝ እርባታ በማብዛት መምህራቸው የጠየቋቸውን ጥያቄዎች በቃል መለሱ፡፡ ከዚያም መምህርቷ "በአጠቃላይ የዕለቱን ትምህርት አንድን ነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር ለመቀየር የምንጠቀምባቸው ስልቶች ምን ምን መሆናቸውን እና አማርኛና ግዕዝ እርባታ ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ አይተናል፡፡" በማለት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡

በመጨረሻም መምህርቷ ተማሪዎች በዕለቱ ትምህርት ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ ዕድል ሰጡ፡፡ አንድ ተማሪ እጁን በማውጣት "**ደብር** የሚለው ቃል **ደብሮች** ወይም **አድባራት** ከምንል ይልቅ ለምን **ዱር** በሚለው አንገልፀውም?" የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡ መምህርቷም "እዚህ ላይ ምናልባት ትርጉም (ፍቺ) እየተማማርን ቢሆን **ዱር** የሚለው ፍቹ **አድባር** ማለት እንችል ይሆናል፤አሁን እየተማማርን ያለነው ግን ፍቺ ሳይሆን አብገር ምዕላድን (ቅጥያን) በመጨመር ቃላትን ማብዛት ነው፡፡ በመሆኑም **ደብር** ሲበዛ በአማርኛ እርባታ **ደብሮች**፣ በግእዝ እርባታ ደግሞ **አድባራት** ይሆናል፡፡" በማለት መለሱ፡፡ አሁንም ሌላ ተማሪ እጁን በማውጣት "ሁሉንም ቃላት የአማርኛና የግዕዝ አብገር ምዕላዶች በመጨመር ማርባት እንችላለን?" በማለት ጠየቀ፡፡ መምህርቷም አንድ ቃል ምሳሌ በመውሰድ በሁለቱ መንገድ ማብዛት እንደሚቻል አስረዱ፡፡ "ስለዚህ የአረባቡ ስልት ይለያያል እንጂ በሁለቱም ማርባት እንችላለን፡፡" በማለት መለሱ፡፡ ሌላ ጥያቄ እንደሌለ ካረጋገጡ በኋላም "የዛሬ ትምህርታችን እዚህ ላይ ያበቃል፡፡" በማለት አጠናቅቀው ወጡ፡፡

**አባሪ-3፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-2 ምድብ ‹‹H1››**

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-H

ክፍለ ጊዜ- 4ኛ

ሰዓት 9፡45-10፡25

ቀን 12/04/2004

የመምህሩ ስም መምህር-1

የተማሪዎች ብዛት -57

መምህርቷ ወደ ክፍል ገቡ። በመቀጠል ዳስተራቸውን አንድ ተማሪ ተቀብሎ ጥቁር ሰሌዳውን ካፀዳላቸው በኋላ የተለመደውን ሰላምታ አቀረቡ። ከዚያም ጥቁር ሰሌዳውን ለሁለት በመክፈል በስተግራ በኩል አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋሰው[3]

የሚለውንና ቀን ከፃፉ በኋላ ተማሪዎቻቸውን ፀጥ እንዲሉ በመንገር "ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማራችሁት ስለምን ነበር?" ብለው ጠየቁ። አንድ ተማሪ እጁን በማውጣት "የቤተ መፃህፍት አጠቃቀም" በማለት መለሰ። በመቀጠል መምህርቷ ቤተመፃህፍት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፣ ወደ ቤተመፃህፍት ሲሄዱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ የተለያዩ መፃህፍት አንብበው ያገኙትን መረጃ ፅፈው እንዲመጡ እንደነገሩዋቸው በማስታወስ መስራታቸውን እየዞሩ አረጋገጡ። ከዚያም የፃፉት ነገር ደብተራቸው ላይ መስፈሩ ለጠቅላላ እውቀት እንደሚጠቅማቸው በመግለፅ የዕለቱ ትምህርት ርእስ ዓረፍተ ነገርን በተመለከተ እንደሆነ ገለፁ።

መምርቷ "አንድ ዓረፍተ ነገር ስህተት የሚባለው የምን የምን ጎድለት ሲታይበት ነው?" የሚል ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ ለሶስት ደቂቃ ያህል በየኔትወርካቸው እንዲወያዩ ነገሩዋቸው። ተማሪዎቹም ወደያውኑ ውይይቱን የጀመሩ ሲሆን መምህርቷ ደግሞ እየዞሩ መከታተላቸውን ቀጠሉ። የተሰጣቸው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ መምህርቷ ኔትወርክ ሰባት እንዲመልሱ ዕድሉን ሰጡ። አንድ የኔትወርኩ አባል ከወንበሩ ብድግ ብሎ በመቆም "አንድ ዓረፍተ ነገር ስህተት አለው የሚባለው ለምሳሌ፡- የቁጥር አለመስማማት ሲኖር ነው።" በማለት መለሰ። አሁንም መምህርቷ የእያንዳንዱን ኔትወርክ ስም በመጥራት ዕድሉን እንዲደርስ አደረጉ። ዕድሉ የተሰጣቸው ኔትወርኮች አባላትም "የፆታ አለመስማማት፣ የመደብ አለመስማማት፣ የቅደም ተከተል አለመስማማት፣የጊዜ አለመስማማት፣ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀፅ አለመስማማት እና የስርዓተ ነጥብ አለመስማማት በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲያጋጥም ዓረፍተ ነገሩ ስህተት አለው ይባላል።" በማለት መለሱ።

መምህርቷ በዓረፍተነገር ውስጥ ስህተት ያስከትላሉ ያሉዋቸውን ለእያንዳንዱ ነጥቦች ምሳሌ እንዲሰጡ ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ አንድ ተማሪ እጁን በማውጣት "ለምሳሌ፡- ስዑድ ምሳውን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ፡፡ በሚለው ዓረፍተነገር የባለቤትና የማሳሪያ አንቀፅ አለመስማማት ይታያል፡፡" በማለት ከመለሰ በኂላ ሌላ ተማሪ ደግሞ "መብራህቱ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡ ብንል የፆታ አለመስማማት ይታያል፡፡" በማለት መለሰ፡፡ ሌሎችም በተመሳሳይ ተሳትፏቸውን ቀጠለ፡፡ የተማሪዎች ምሳሌ መስጠት ካበቃ በኂላ መምህርቷ ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ በእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር የሚታየውን ስህተት የምን ስህተት እንደሆነ አስረዱ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአንድ ዓረፍተ ነገር የሚገባ ስርዓተ ነጥብ በተገቢ ቦታው ካልተቀመጠ ስህተት እንደሚፈጥር በመግለፅ ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን ጥያቄዎች እየተወያዩ የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡

በውይይቱ ወቅትም መምህርቷ በየኔትወርኩ እየዞሩ ሲከታተሉ የታዩ ሲሆን ውይይቱ ካበቃ በኂላም ተማሪዎች ከየኔትወርኩ እየወጡ የጥያቄዎችን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲፅፉ መመሪያ ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም ከየኔትወርኩ እየወጡ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ መልስ ሰጡ፡፡ መምህርቷም ጥቁር ሰሌዳ ላይ ከተፃፉ መልሶች ስህተት መልስ የተሰጠበት ካለ ተማሪዎች ለይተው እንዲነግሩዋቸው አደረጉ፡፡ ተማሪዎች በስህተት የተመለሰ ጥያቄ ከለዩ በኂላ ተመልሰው ሌሎች ተማሪዎች እንዲያስተካክሉት አዘዙ፡፡ ተማሪዎቹም እየወጡ አስተካከሉ፡፡ መምህርቷም ተማሪዎችን በማድነቅ የተሰጡትን ምላሽ አጠናከሩ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ማስተካከያ የተደረገበትን መልስ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ጊዜ ሰጡ፡፡

ተማሪዎች ማስተካከያውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው መጨረሳቸውን ካረጋገጡ በኂላም "ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር ለመቀየር የምንጠቀምበት ስልት ምንድን ነው?" በማለት ወደ ቀጣዩ ርእስ አመሩ፡፡ አንድ ሴት ተማሪ እጇን በማውጣት "ለምሳሌ:-**ዎች** የሚለውን ምዕላድ በቃል መጨረሻ በመጨመር **ነጠላ** ቁጥር ወደ **ብዙ** ቁጥር መቀየር ይቻላል፡፡" በማለት መለሰች፡፡ ወድያውም የትምህርት ቤቱ ደወል ተደመጠ፡፡ መምህርቷም ክፍለ ጊዜው ማለቁ ስለገባቸው "በዛሬው ትምህርታችን ምን እንደተማማርን ማጠቃለያ የሚሰጠኝ ማን ነው?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም "አንድን ዓረፍተ ነገር

ስህተት የሚያስብሉት ምን ምን መሆናቸውን ለይተናል" በማለት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡ መምህርቷም "ጎበዞች" ብለው ተማሪዎችን በማበረታታት ጨርሰው ከክፍል ወጡ፡፡

**አባሪ-4፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-2 ምድብ ‹‹E1››**

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-E

ክፍለ ጊዜ- 1ኛ

ሰዓት 6፡30-7፡10

ቀን 13/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-2

የተማሪዎች ብዛት - 49

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ለሁለት ከፈሉ፡፡ በስተግራ በኩልም ቀንና አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን ፃፉ፡፡ በመቀጠል መምህሩ "ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ያላቸውን ሰዋስዋዊ ስህተት በመለየት አስተካክላችሁ ፃፉ" የሚለውን ትዕዛዝ ተማሪዎች በቃል እንዲፅፉ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ፃፉ፡፡ ከዚያም መምህሩ አራት ዓረፍተ ነገሮች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች እንዲፅፉ አዘዙ፡፡ በወቅቱም መምህሩ ተማሪዎች ፅፈው እስኪጨርሱ የተወሰነ ጊዜ ጠበቁ፡፡ ፅፈው ከጨረሱ በኋላም ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩት ለማሳየት መምህሩ አንደኛውን ተራ ቁጥር ወስደው አስረዱ፡፡ በመቀጠል የቀሩትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ መመሪያ ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም ውይይቱን የጀመሩ ሲሆን መምህሩም እየዞሩ መከታተል ጀመሩ፡፡ የተሰጠው ደቂቃ ካለቀ በኋላም ተማሪዎች ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ጋበዙ፡፡ ተማሪዎችም ከየኔትወርኩ እጃቸውን በማውጣት ለጥያቄዎቹ ምላሽ ሰጡ፡፡ የተማሪዎች ምላሽ እንዳበቃም መምህሩ "በአጠቃላይ በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ

የፆታ፣ የቁጥር፣ የጊዜ፣ የቅደም ተከተል፣ የመደብ እና የባለቤትና የግስ አለመስማማት ሊያጋጥም ይችላል፡፡" በማለት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡

መምህሩ ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም መስራት ጀመሩ፡፡ የተፈቀደላቸውን ደቂቃ ካበቃ በኋላም መምህሩ ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በቃል ምላሽ እንዲሰጡ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ጥያቄዎቹን በቃል መለሱ፡፡ በመቀጠል ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር እንዴት እንደሚቀየር በመማሪያ መፅሀፋቸው ያሉትን ምሳሌዎች እንዲመለከቱ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም ምሳሌዎችን ተመለከቱ፡፡ መምህሩ ተማሪዎች ምሳሌዎችን መረዳቸውን ካረጋገጡ በኋላም በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-ነ›› ያሉትን ቃላት በየኔትወርካቸው እየተወያዩ **ከነጠላ ወደብዙ ቁጥር** እንዲቀይሩ መመሪያ ሰጡ፡፡ ከውይይቱ በኋላም ከየኔትወርኩ አንድ ተማሪ ወጥቶ እንደሚሰራ በማስረዳት ከየኔትወርኩ ወጥተው የሚሰሩ ተማሪዎች አንተ አንቺ በማለት ለዩ፡፡ በመቀጠል የሚወያዩበት ጉዳይ ደብተራቸው ላይ መፃፍ እንደሌለባቸው በመግለፅ ውይይቱ ቀጠለ፡፡ መምህሩም እየዞሩ ይከታተሉ ነበር፡፡ የተሰጣቸውን ደቂቃ ከተጠናቀቀ በኋላም ከየኔትወርኩ የተመረጡ ተማሪዎች እየወጡ መልሳቸውን ጥቁር ሰሌዳ በመፃፍ ለፃፉት መልስ ገለፃ ሰጡ፡፡ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ሰርተው ሲጨርሱም መምህሩ ማጠናከሪያ ሰጥተው ሰዓታቸውን ተመለከቱ፡፡ ክፍለ ጊዜው መገባደዱን ሲያስተውሉም የቀሩትን ማለትም ከ ‹‹ሸ-ነ-›› ያሉትን ጥያቄዎች የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ አዘዙ፡፡ በመቀጠል መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ተማሪዎች ማጠቃለያ እንዲሰጡ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት "የዛሬው ትምህርታችን የአንድ ዓረፍተ ነገር የሰዋስው ስህተት ለይቶ ማስተካከልና ነጠላ ቁጥር ወደብዙ ቁጥር መቀየር የሚሉት ናቸው፡፡" በማለት መለሱ፡፡ መምህሩም ተማሪዎችን አድንቀው የተሰጣቸውን የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ በአፅንኦት በመንገር ተሰናብተው ወጡ፡፡

**አባሪ-5፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-2 ምድብ ‹‹L1››**

ቀረፃ አንድ- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-L

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰዓት 7፡50-8፡30

ቀን 16/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-2

የተማሪዎች ብዛት - 55

በቅድሚያ መምህሩ ጥቁር ሰሌዳውን በማፅዳት ለሁለት ከፈሉ፡፡ በስተግራ በኩልም ቀንና

አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን በመፃፍ ለተማሪዎች ሰላምታ አቀረቡ፡፡ በመቀጠል ባለፈው ክፍለ ጊዜ ሰለምን ርእስ እንደተማሩ ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም "የቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች፡፡" በማለት መለሱ፡፡ መምህሩም ተማሪዎች ምሳሌ እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት "ለምሳሌ፣ **አደገ** የሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቹ **በለፀገ** የሚል ሲሆን ተቃራኒ ፍቹ ደግሞ **ኂላቀረ** ነው፡፡" በማለት መለሱ፡፡ በመቀጠልም መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ዓረፍተ ነገሮችን ማስተካከል እንደሆነ በመግለፅ ርዕሱን አስተዋወቁ፡፡

መምህሩ "የፈፀምኩት ስህተት በርካታ ናቸው፡፡" የሚለውን ዓረፍተ ነገር ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ዓረፍተ ነገሩ የምን ስህተት እንዳለበት ገለፁ፡፡ ከዚያም አስተካክለው በመፃፍ ተማሪዎቹን አስረዱ፡፡ ተማሪዎች ምሳሌውን መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኂላም መምህሩ

1. በትምህርት ቤታችን ያለችውን ዛፍ ቅርንጫፎቹ ብዙ ናቸው፡፡
2. የገዛችው ጫማ ነው ትርሀስ፡፡

የሚሉትን ዓረፍተ ነገሮች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገሮቹ የምን ስህተት እንዳለባቸው እንዲለዩና ስህተቱን ከለዩ በኋላ ደግሞ ዓረፍተ ነገሮቹን በቃል እንዲያስተካክሉ መመሪያ ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም በቃል መለሱ፡፡ በመቀጠል መምህሩ በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 58 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች በየኔትወርካቸው እየተወያዩ ስህተታቸውን በመለየት አስተካክለው እንዲፅፉ ተማሪዎቹን አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም በየኔትወርካቸው መወያየት የጀመሩ ሲሆን መምህሩም እየዞሩ ይከታታሉ ነበር፡፡ መምህሩ ለጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ጊዜ ሲያበቃም ከእያንዳንዱ ኔትወርክ ተማሪዎች በመምረጥ እየወጡ እዲመልሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም እየወጡ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ መለሱ፡፡ መምህሩ ተማሪዎች ለሰጡት ምላሽ ማስተካከያ በመስጠት ወደ ሚቀጥለው ርእስ አመሩ፡፡ ከዚያም

1. ቃል - ቃሎች- ቃላት
2. ልብስ - ልብሶች - አልባሳት
3. ቤት - ቤቶች - አብያት
4. ወፍ - ወፎች - አእዋፍ

የሚሉትን ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ወደ ብዙ ቁጥር እንዴት እንደተቀየሩ አስረዱ፡፡ ቃላቱ **በአማርኛ** እና **በግእዝ** እንደበዙም ገለፁ፡፡ መምህሩ የሰጡትን ገለፃ ተማሪዎች መረዳታቸውን ጠይቀው አረጋገጡ፡፡ ተማሪዎች ግልፅ መሆኑን ከገለፁ በኋላም መምህሩ በምሳሌው መሰረት በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59-60 ያሉት ጥያቄዎች የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ ተማሪዎቹን አዘዙ፡፡ አስከትለውም "እስኪ ዛሬም ምን አወቃችሁ?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎች ደግሞ እጃቸውን በማውጣት "በአንድ ዓረፍተ ነገር ያለውን ስህተት መለየት፣ ዓረፍተ ነገሩን አስተካክሎ መፃፍ እና ነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር መቀየር የሚሉትን ተምረናል፡፡" በማለት መለሱ፡፡ መምህሩም ተማሪዎችን "በጣም ጎበዞች" ብለው በማድነቅ ተማሪዎችን አበረታቱ፡፡ ከዚያም የዕለቱ ትምህርት ተማሪዎች የገለፁት መሆኑን በማብራራት የዕለቱን ትምህርት አጠናቅቀው ከክፍል ወጡ፡፡

**አባሪ-6፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-3 ምድብ ‹‹A1››**

ቀረፃ አንድ- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-A

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰዓት 3፡20- 4፡00

ቀን 13/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-3

የተማሪዎች ብዛት -51

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ለተማሪዎች ሰላምታ በማቅርብ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ለሁለት ከፈሉ፡፡ በስተግራ በኩል አማርኛ[1]

ያ- ደራሲ[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውንና ቀን ፃፉ፡፡ በመቀጠል መምህሩ በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ገፅ 46 የሚገኘው "ከግስ አርእስት መመሰረት" የሚለውን ትዕዛዝ በማንበብ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ቀጥለውም "ከግስ አርእስት እንዴት ይመሰረታል? ማለትም አዳዲስ ቃላት እንዴት መመሰረት ይቻላል?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት "ከግስ አርእስት የሚመሰረተው በግስ መጀመሪያ **መ-** ን እና በግስ መጨረሻ **-ት** ን በመጨመር ነው፡፡" በማለት ተማሪዎች መልስ ሰጡ፡፡ አስከትለውም መምህሩ ተማሪዎችን ምሳሌ እንዲሰጡ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት "ለምሳሌ፡- **መታ-መምታት፣ከራ-መኩራት** ወዘተ." በማለት መለሱ፡፡ በመቀጠል መምህሩ በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ገፅ 45 በ ሀ፣ለ፣ሐ እና መ ስር የሚገኙትን ቃላት ተማሪዎች ከግስ ወደ አርእስት እንዲቀይሩ የክፍል ስራ ሰጡ፡፡ ተማሪዎች በግላቸው የክፍል ስራውን ሲሰሩም መምህሩ እየዞሩ ይከታተሉ ነበር፡፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላም ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን እያወጡ ጥያቄዎችን በቃል መለሱ፡፡

መምህሩ በሚቀጥለው (በገፅ 46) የሚገኙትን ጥያቄዎች ለማሰራት መጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ በቃል እንዲፅፉ መመሪያ ሰጡ፡፡

*ቅፅል የስም ገላጭ ሲሆን በጣም የሚለውን ቃል ከፊቱ (በስተግራ) በኩል አስቀድሞ ሲገባበት ተቀባይነት ያለው ቃል እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ማለት በጣም----------ስም በሚለው ሀረግ በባዶ ቦታው ሲገባ ተቀባይነት ያለው ቃል ማለት ነው፡፡*

መምህሩ ይህንን ማስታወሻ በቃል ካስፃፉ በኂላም **የስም ገላጭ ስምን የሚገልፅ፣የግስ ገላጭ ደግሞ ግስን የሚገልፅ ቃል** መሆኑን አብራሩ፡፡ በመቀጠል

1. ተንኮለኛ ምንጊዜም ይጋለጣል፡፡
2. አጥፊ ሰው ይቅርታ ይጠይቃል፡፡

የሚሉት ዓረፍተ ነገሮች በቃል በማንበብ በመጀመሪያው ተራ ቁጥር የተሰመረበት ቃል የግስ ገላጭ በሁለተኛው ደግሞ የስም ገላጭ መሆኑን አስረዱ፡፡

መምህሩ በተማሪዎቹ መማሪያ መፅሀፍ ገፅ 46 ከ ‹‹ሀ-ረ›› ያሉትን የተሰመረባቸው ቃላት የስም እና የግስ ገላጭ በማለት እንዲለዩ የክፍል ስራ ሰጡ፡፡ ተማሪዎቹም መስራት ጀመሩ፡፡ መምህሩም እየዞሩ ይከታተሉ ነበር፡፡ በወቅቱም ተማሪዎች ያልገባቸውን እየጠየቁ መምህሩም እያስረዱዋቸው ነበር፡፡ መምህሩ የተሰጠው ደቂቃ ማለቁን ለተማሪዎች በማስታወስ ለሚሰጡት መልስ ከነምክንያቱ እንዲገልፁ አዘዙ፡፡ በወቅቱም ተማሪዎች እኔ፣እኔ በማለት እና ለተጠየቀው ጥያቄ በጅምላ በመመለስ የሚመለሰውን መልስ አለመደማመጥ ይስተዋል ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ተማሪዎች እጃቸውን በማውጣት የተጠየቁትን ጥያቄዎች ከነምክንያታቸው መለሱ፡፡ መምህሩ መልስ ለሚሰጡ ተማሪዎች ጎበዝ በማለት ያበረታቱ ነበር፡፡ ተማሪዎች ለሰጡት ማብራሪያም መምህሩ ማስተካኪያ ሰጡ፡፡

መምህሩ እየተወያዩ ሶስት ሶስት ዓረፍተ ነገሮች በመመስረት **የስምና የግስ ገለጭ** እንዲለዩ ተማሪዎቹን አዘዙ። ተማሪዎችም ለ5 ደቂቃ ያህል በመወያየት ሶስት ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ከነ የስምና የግስ ገላጫቸው ለይተው መልስ ሰጡ። በመቀጠል መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ከማጠቃለላቸው በፊት ተማሪዎች እንዲጠይቁ ዕድል ሰጡ። አንድ ተማሪ እጁን በማውጣት "**ማለ** የሚለው ቃል ወደ አርእስት ሲቀየር **መማል** ይሆናል። ስለዚህ እዚህ ላይ **-ት** አይታይም፤እና ወደ አርእስት አልተቀየረም ማለት ነው?" የሚል ጥያቄ አቀረበ። መምህሩም ከግስ አርእስት የሚመሰረተው በቃሉ መጨረሻ **-ት** ን መኖር ግዴታ እንዳልሆነ አብራርተው አስረዱ። ሌላ ተማሪ እጁን በማውጣት "**ቃኘ** የሚለው ወደ አርእስት እንዴት ይቀየራል? ትርጉሙስ ምንድን ነው?" በማለት ጠየቀ። መምህሩም "ወደ አርእስት ሲቀየር **መቃኘት** ይሆናል ትርጉሙ ደግሞ **ዳሰሰ፣ጎበኘ፣አየ** ማለት ነው።" በማለት መለሱ። አሁንም ሌላ ተማሪ እጁን በማውጣት "ሰነፍ ተማሪ ዘወትር ይጨነቃል። በሚለው ዓረፍተ ነገር **ተማሪ** የሚለውን ቃል ቢሰመርበት የምን ገላጭ ይሆን ነበር?" በማለት ጠየቀ። መምህሩም ተማሪዎች እንዲሞክሩ ዕድሉን ሰጡ። ተማሪዎች የመሰላቸውን መልስ ከሰጡ በኂላ መምህሩም **የግስ ገላጭ** የሚለውን ምላሽ ሰጡ። በመጨረሻም በክፍል አምስት ስር ያሉት ሁለት ስነ ፅሁፋዊ ግጥሞች አንድነትና ልዩነት የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ በማዘዝ ጨርሰው ወጡ።

**አባሪ-7፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-3 ምድብ ‹‹C1››**

ቀረፃ አንድ- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-C

ክፍለ ጊዜ- 6ኛ

ሰዓት 10፡25-11፡15

ቀን 19/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-3

የተማሪዎች ብዛት - 51

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ለሁለት በመክፈል በስተግራ በኩል አማርኛ[1]

ያ- ደራሲ[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውንና ቀን በመፃፍ የተለመደውን ሰላምታ አቀረቡ። በመቀጠል የዕለቱን ትምህርት "ከግስ አርእስት መመሰረት" መሆኑን አስተዋወቁ። አስከትለውም "ከግስ አርእስት እንዴት መመሰረት ይቻላል?" የሚለውን ጥያቄ ተማሪዎችን ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት "አንድ ግስ ላይ ከፊት **መ-** በመጨመር እና ከመጨረሻ ደግሞ እንደ አስፈላጊነቱ **-ት** ን በመጨመር ከግስ አርእስት መመሰረት ይቻላል።" በማለት መለሱ። በመቀጠል መምህሩ **ሰራ- መስራት፣ ፈለገ- መፈለግ ፣ከተተ- መክተት** የሚሉት ምሳሌዎችን በመውሰድ ከግስ ወደ አርእስት እንዴት እንደተቀየሩ አስረዱ። ከዚያም መምህሩ አምስት ቃላት ተማሪዎቹን በቃል በማስፃፍ ከግስ ወደ አርእስት እንዲቀይሩ የክፍል ስራ ሰጡ። የክፍል ስራውም በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎችም የተወሰኑ እየተወያዩ በመፃፍ፣የተወሰኑ ደግሞ ውይይቱን ትተው በመፃፍ የክፍል ስራውን መስራት ጀመሩ። መምህሩም እየዞሩ ሲከታተሉ ይታያሉ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላም ተማሪዎች የክፍል ስራውን እጃቸውን እያወጡ እንዲመልሱ ጋበዙ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት በቃል መለሱ። መልስ በሚሰጥበት ወቅትም እኔ፣እኔ የሚለውንና ለአንድ ጥያቄ በጋራ መመለስ ይስተዋል ነበር።

መምህሩ ተማሪዎች የራሳቸውን ግሶች አዘጋጅተው ወደ አርእስት ለመቀየር በግላቸው እንዲያዘጋጁ አዘዙ። ከተወሰነ ደቂቃ በኋላም ተማሪዎች ከግስ ወደ አርእስት የቀየሩዋቸው ቃላት እጃቸውን እያወጡ በቃል መለሱ። በመቀጠል መምህሩ ተማሪዎች የተማሩትን ጉዳይ መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኋላ "**የስም** እና **የግስ ገላጭ** ምን ማለት ነው?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ። ተማሪዎችም "የስም ገላጭ ከስም በፊት የሚመጣ (ባለቤትን የሚገልፅ)፣የግስ ገላጭ ከግስ በፊት የሚመጣ (ማሰሪያ አንቀፅን የሚገልፅ) ነው።" በማለት መለሱ። መምህሩም ተማሪዎች በሰጡት ሀሳብ ላይ ማጠቃለያ በመስጠት ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ በቃል እንዲፅፉ አሳሰቡ።

*ቅፅል የስም ገላጭ ሲሆን በጣም የሚለውን ከቅፅሉ በስተግራ ሲገባበት ተቀባይነት ያለው ቃል ከሆነ ነው። ይህም ማለት በጣም------- ስም በሚለው ሀረግ ውስጥ በባዶ ቦታው ላይ ሲገባ ተቀባይነት ያለው ቃል ማለት ነው።*

የሚለውን ማስታወሻ ከሰጡ በኋላ በጣም ደግ (ሰው)፣

በጣም ወፍራም (በሬ) የሚሉትን ሁለት ሐረጎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ በቅንፍ ውስጥ ካሉት ስሞች በፊት ያሉት **ደግ** እና **ወፍራም** የስም ገላጭ ናቸው። በማለት ማስታወሻውን አጠናከሩ። በመቀጠል

1. ተንኮለኛ ምንግዜም ይጋለጣል።
2. አጥፊ ሰው ይቅርታ ይጠይቃል።

የሚሉት ሁለት ምሳሌዎች በመውሰድ በመጀመሪያ ጥያቄ የግስ ገላጭ እና በሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ የስም ገላጭ መሆኑን አስረዱ። ከዚያም ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 46 ከ ‹‹ሀ-ረ›› ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች የስምና የግስ ገላጭ በመለየት የክፍል ስራ እንዲሰሩ መምህሩ መመሪያ ሰጡ። ተማሪዎችም ደብተራቸው ላይ በመፃፍ የክፍል ስራውን መስራት የጀመሩ ሲሆን መምህሩም እየዞሩ ተማሪዎችን ሲከታተሉ ታይቷል። የተሰጠውን ደቂቃ ካለቀ በኋላም መምህሩ ተማሪዎች የጥያቄዎችን መልስ በቃል እንዲመልሱ ጋበዙ። ተማሪዎችም እያንዳንዱ ጥያቄ በቃል መለሱ። በመቀጠል ተማሪዎች የራሳቸውን ዓረፍተ ነገር በመመስረትና አንድ ቃል በማስመር የስም እና የግስ ገላጭ እንዲለዩ አዘዙ። ተማሪዎችም ለተወሰነ ደቂቃ በማሰብ አዘጋጁ። ደቂቃውን ካለቀ በኋላም መምህሩ ተማሪዎችን እየመረጡ በማስነሳት እንዲመልሱ አደረጉ። ተማሪዎችም ከተቀመጡበት በመነሳት መልስ ሰጡ። የተማሪዎች ምላሽ ከተጠናቀቀ በኋላም መምህሩ ስለ ዕለቱ ትምህርት ማጠቃለያ ሰጡ።

ቀጥለውም መምህሩ ተማሪዎች በዕለቱ ትምህርት ያልገባቸው እንዲጠይቁ ዕድል ሰጡ። አንድ ሴት ተማሪ እጇን በማውጣት “ለምሳሌ፡- አበበ መጣ። በሚለው ዓረፍተ ነገር የስም እና የግስ ገላጭ እንዴት መለየት እንችላለን?” በማለት ጠየቀች። መምህሩም “አሁን የተናገርሽው ዓረፍተ ነገሩን ብቻ ነው። ይሁን እንጂ የስም (የግስ) ገላጭ መሆኑን ለማወቅ የተሰመረበት ቃል ያስፈልጋል። አንቺ ግን አላሰመርሽም። ስለዚህ

ከሁለቱ አንዱን ለመለየት ዋናው የተሰመረበት ቃል ላይ ማተኮር ስለሆነ በመሰረትሽው ዓረፍተ ነገር መለየት አይቻልም።" በማለት መለሱ። ከዚያም መምህሩ "ሰነፍ ተማሪ ዘወትር ይጨነቃል። በሚለው ዓረፍተ ነገር ተማሪ የሚለው ቃል ቢሰመርበት የምን ገላጭ ይሆናል።" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ። ተማሪዎችም የመሰላቸውን መለሱ። በመጨረሻም መምህሩ "የግስ ገላጭ" ይሆናል የሚል ምላሽ ሰጡ። ወድያውኑም ክፍለ ጊዜው በማለቁ ስለተደወለ ተማሪዎች ሌላ ጥያቄ ካላቸው በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ መጠየቅ እንደሚችሉ አሳሰቡ። ከዚያም በክፍል አምስት ስር ባሉት ሁለት ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ፅፈው እንዲመጡ የቤት ስራ በመስጠት ተሰናብተው ወጡ።

**አባሪ-8፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-4 ምድብ ‹‹K1››**

ቀረፃ አንድ- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-K

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰዓት 7፡50-8፡30

ቀን 15/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-4

የተማሪዎች ብዛት - 48

መምህርቷ ወደ ክፍል እንደገቡ ተማሪዎች ዳስተሩን ተቀብለው ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱላቸው። በመቀጠል መምህርቷ የተፀዳውን ጥቁር ሰሌዳ ለሁለት በመክፈል በስተግራ በኩል ቀንና አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን ፃፉ። ቀጥለውም ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ ምን እንደተማሩ ተማሪዎቹን ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት የወሊድ መቆጣጠሪያ መንገዶችን በተመለከተ መማራቸውን ገለፁ። መምህርቷም ስለ ባለፈው ትምህርታቸው አጭር ገለፃ በመስጠት የዕለቱ ትምህርት ሰዋስው መሆኑን አስተዋወቁ። በመቀጠል "ምሳሌውን

መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ነጠላ ቁጥሮች ወደብዙ ቁጥር ቀይሩ።" የሚለውን ትእዛዝ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ። ከዚያም ቃላት ከነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር እንዴት መቀየር እንደሚቻል ምሳሌዎችን በመውሰድ አስረዱ። ቀጥለውም ምሳሌው ግልፅ መሆን አለመሆኑን ለተማሪዎች ጥያቄ አቀረቡ። ተማሪዎችም ግልፅ መሆኑን ከገለፁ በኋላ መምህቷ በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-ከ›› ያሉትን ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች እየወጡ እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎችም በግላቸው እየወጡ ሰሩ።

በወቅቱም መምህርቷ የሚሰጡት ዕድል ወንድና ሴት በማቀላቀል ነበር። ነገር ግን ዕድል የመስጠት ሁኔታው ለተወሰኑ ተማሪዎች ደጋግሞ መስጠት ይታይ ነበር። ተማሪዎች እየወጡ ጥቁር ሰሌዳ ላይ የጥያቄዎችን መልስ ከፃፉ በኋላ መምህርቷ ተማሪዎችን በማድነቅ ከአምስቱ የቃል ክፍሎች ሊረቡ የሚችሉት **ስምና ቅፅል** ሲሆኑ **ስሞች** ሲረቡም **በአማርኛና በግዕዝ** ሊረቡ እንደሚችሉ በመግለፅ የተማሪዎችን መልስ አጠቃለሉ። በመቀጠል በሳድስ የሚጨርሱ ቃላት ሲበዙ ሁል ጊዜ **-ኦች** የሚወስዱ ሲሆን ከዛ ውጭ ያሉት ግን **-ዎች** እንደሚወስዱ ገለፁ። መምህርቷ ግልፅ መሆን አለመሆኑን ተማሪዎችን ጠይቀው ካረጋገጡ በኋላ ወደ እሚቀጥለው ርእስ ቀጠሉ።

መምህርቷ በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ 59 ላይ "የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት በፍቺ የቀረቡ ሌሎች ቃላትና ሀረጋት ተኩ።" የሚለውን ትዕዛዝ በማንበብ በስሩ ከሚገኙ ሁለት ምሳሌዎች በመውሰድ አስረዱ። ከዚያም ተማሪዎች መረዳታቸውን ጠየቁና ተማሪዎች መረዳታቸውን ሲገልፁ የቀሩትን በየኔትወርካቸው በመወያየት እንዲሰሩ አዘዙ። በወቅቱም መምህርቷ በየኔትወርኩ እየዞሩ ለተወሰነ ጊዜ በማከታተል ከቆዩ በኋላ ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች ጋር በመቀመጥ ጥያቄዎችን በማንበብ ያወያዩ ነበር። የተሰጠው ደቂቃ ካለቀ በኋላም ከየኔትወርኩ ተማሪዎች እየተነሱ በቃል እንዲመልሱ አደረጉ። ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ መምህሩም ማስተካከያ ይሰጡ ነበር። በመቀጠል ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ **ተማሪው** የሚለውን ምንባብ በማንበብ የአንብቦ መረዳት ጥየቄዎች በቃል ለመመለስ ተዘጋጅተው እንዲመጡ የቤት ስራ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት አጠናቅቀው ወጡ።

አባሪ-9፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-1 ምድብ ‹‹ G2››

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ- G

ክፍለ ጊዜ -2ኛ

ሰዓት 7፡10-7፡50

ቀን- 22/04/2004

የመምህሩ ስም መምህር-1


የተማሪዎች ብዛት - 50

መምህርቷ ወደ ክፍል ሲገቡ አንድ ተማሪ ዳስተሩን ተቀብሎ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱላቸው፡፡ በመቀጠል መምህርቷ የተለመደውን ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ጥቁር ሰሌዳውን ለሁለት በመክፈል በግራ በኩል ቀንና አማርኛ[1]

ተማሪው[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን ፃፉ፡፡ ቀጥለውም የደብዳቤ አፃፃፍን በተመለከተ የቤት ስራ እንደሰጡ ተማሪዎችን በመጠየቅ ደብተራቸውን እየዞሩ ፈትሸው መስራታቸውን አረጋገጡ፡፡ ከዚያም ከሰሩት ተማሪዎች መካከል አንድ ሴት ተማሪ በማስወጣት የሰራችውን አንድታነብ ጋበዙ፡፡ ተማሪዋም ወደ መድረክ በመውጣት የፃፈችውን ደብዳቤ አነበበች፡፡ ተማሪዋ አንብባ ከጨረሰች በኋላም መምህርቷ የዕለቱ ትምህርት ከስም ወደ ግስ መቀየር መሆኑን በመግለፅ “ዓላማ፡- ከስም ወደ ቅፅል መቀየር”




የሚለውን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ከዚያም “ስም ምንድን ነው? ቅፅልስ?” በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ አንድ ሴት ተማሪ እጇን በማውጣት “ስም ማለት በአንድ ዓረፍተ

ነገር እንደ ባለቤት ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡" በማለት መለሰች፡፡ መምህርቷም "ስም ማለት በአረፍተ ነገር ውስጥ እንደ **ባለቤት፣ ተሳቢ** እና **ዘርፍ** ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡" በማለት የተማሪዋን ሀሳብ አጠናከሩ፡፡ ቀጥለውም መምህርቷ

1. መፅሀፍ ተቀደደ፡፡
2. አበበ መፅሀፍ ገዛ፡፡
3. መፅሀፌን ወሰደው፡፡

የሚሉትን ዓረፍተ ነገሮች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ **መፅሀፍ** የሚለውን ቃል በሶስቱም ዓረፍተ ነገሮች እንደ ምን ሆኖ እንደገባ ገልፅው የስም ምንነትን አጠቃለሉ፡፡ አስከትለውም "ቅፅልስ ምንድን ነው?" የሚል ጥያቄ ለተማሪዎች አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም "ቅፅል ስምን የሚገልፅ ነው፡፡" በማለት መለሱ፡፡ ቀጥለውም መምህሩ ሁለት ወንድ እና ሁለት ሴት ተማሪዎች ወደ መድረክ በማስወጣት ተማሪዎች በቁመት (ረዥም፣ አጭር)፣ በዓይነት (ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም)፣ በክብደት (ወፍራም፣ቀጭን) እያሉ እንዲለዩዋቸው ካደረጉ በኋላ ተማሪዎቹን ለመለየት የተጠቀሙዋቸው ቃላት በሙሉ ቅፅሎች መሆናቸውን አስረዱ፡፡ በመቀጠል መምህርቷ ሶስት ምሳሌዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከስም ወደ ቅፅል እንዴት እንደሚቀየሩ አስረዱ፡፡

መምህርቷ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምሳሌ መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 69 ከ ‹‹ሀ-በ›› ስር ያሉትን ቃላት ከስም ወደ ቅፅል በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አሳሰቡ፡፡ ተማሪዎችም እየፃፉ እና እየተወያዩ ነበር፡፡ መምህርቷም እየዞሩ ይከታተሉ ነበር፡፡ መምህርቷ ለሰጡት ጥያቄ የሰጡት ደቂቃ ሲያበቃም ጥቁር ሰሌዳውን ለአራት ከፍለው አራት ተማሪዎችን ከየኔትወርኩ በማስወጣት የሰሩትን ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲፅፉ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም እየወጡ በመፃፍ መልሳቸውን አስቀመጡ፡፡ መምህርቷም ተማሪዎች ለሰሩት መልስ ማስተካከያ በመስጠት "የዛሬው ትምህርት ዓላማ ከስም ወደ ቅፅል መቀየር የሚል ነው፡፡" በማለት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡ መምህርቷ ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል ቢሰጡም ተማሪዎች ግን ሲጠይቁ አልታዩም፡፡ መምህርቷም "ጥያቄ ከሌለ የዛሬ ትምህርታችን እዚህ ላይ ያበቃል፣የሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ቅፅሎች በዓረፍተ ነገር እያስገባን እንሰራለን፡፡" በማለት ጨርሰው ወጡ፡፡

አባሪ-10፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-1 ምድብ ‹‹H2››

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-H

ክፍለ ጊዜ- 5ኛ

ሰዓት 9፡45-10፡25

ቀን 23/04/2004

የመምህሩ ስም መምህር-1

የተማሪዎች ብዛት -57

መምህርቷ ወደ ክፍል በመግባት የተለመደውን ሰላምታ አቀረቡ፡፡ ቀጥለውም ጥቁር ሰሌዳውን በማፅዳት ለሁለት ክፍለው በስተግራ በኩል

አማርኛ[1]

ተማሪው[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውንና ቀን ፃፉ፡፡ በመቀጠል "ዓላማ፡- ስምን ወደ ቅፅል መቀየር" የሚለውን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ከዚያም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የቤት ስራ እንደሰጡ በማስታወስ ተማሪዎች መሰራታቸውን እየዞሩ በመፈተሽ አረጋገጡ፡፡ አስከትለውም ደብዳቤ የስራ እና የግል ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል በመግለፅ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ተማሪዎች እንዲናገሩ ዕድል ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም "የስራ ደብዳቤ ማህተም የሚያስፈልገው ሲሆን የግል ግን አያስፈልገውም፣ የስራ ደብዳቤ ፊርማ፣ ቁጥር የሚያስፈልገው ሲሆን የግል ግን አያስፈልገውም እና የስራ ደብዳቤ አንድ ሰው ለአንድ ድርጅት የሚፅፈው ሲሆን የግል ደግሞ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚፃፃፉት ነው ወዘተ." በማለት መለሱ፡፡ መምህርቷም ማጠናከሪያ ሰጡ፡፡

መምህርቷ ከዓላማው ስር "ዘመናዊ የቃል ክፍሎች" የሚለውን በመፃፍ "በዘመናዊው ስዋሰው የቃል ክፍሎች ምን ምን ናቸው?" በማለት ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም "ስም፣ቅፅል፣ ግስ፣መስተዋድድ እና ተውሳካ ግስ" በማለት ዘረዘሩ፡፡ መምህርቷ "የዕለቱ ትምህርታችን ስምን ወደ ቅፅል መቀየር ነው፡፡" በማለት አስተዋወቁ፡፡ ቀጥለውም መምህርቷ የስም

ግልጋሎትን እንዲገልፁ ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎቹም "እንደ **ባለቤት**፣ **ተሳቢ** እና **ዘርፍ** ሆኖ ያገለግላል፡፡" በማለት መለሱ፡፡ መምህርቷም የተማሪዎችን ሀሳብ በማጠናከር፡፡

ሀ. እርሳስ ጠፋ፡፡

ለ. አበበ እርሳስ ገዛ፡፡

ሐ. እርሳሴን ፋሲል ወሰዱብኝ፡፡

የሚሉትን ሶስት ምሳሌዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ እርሳስ የሚለውን ቃል በሶስቱም እንደ ምን ሆኖ እንደሚያገለግል አስረዱ፡፡ በመቀጠል አራት ተማሪዎች መድረክ ላይ በማስወጣት ተማሪዎች ዓይነታቸውን (ቀይ፣ጥቁር፣ጠይም)፣ቁመታቸው (አጭር፣ረዥም)፣ ክብደታቸውን (ቀጭን፣ ወፍራም) በማለት እንዲለዩ አደረጉ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ለመለየት የተጠቀሙዋቸው ቃላት በሙሉም ቅፅል መሆናቸውን አስረዱ፡፡ ቅፅሎቹ ስሞቹን እንደሚገልፁ አብራርተው ሶስት ምሳሌዎችን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ስምን ወደ ቅፅል እንዴት መቀየር እንደሚቻል አስረዱ፡፡

መምህርቷ ተማሪዎች መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኋላም በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ገፅ 69 ከ ‹‹ሀ-በ›› ያሉትን በየኔትወርካቸው እየተወያዩ የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ በወቅቱም የተወሰኑት መወያየቱን ትተው ሲፅፉ፣ የተወሰኑት ደግሞ መፃፉን ትተው ሲወያዩ እና የተወሰኑት ደግሞ እየፃፉም እየተወያዩም ነበር፡፡ መምህርቷም እየዞሩ መከታተላቸውን ቀጠሉ፡፡

መምህርቷ ውይይቱ ካለቀ በኋላ ተማሪዎች የሰሩትን የክፍል ስራ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ደብተራቸውን እየዞሩ በማየት ፈተሹ፡፡ በመቀጠል ከየኔትወርኩ ሁለት ሴት እና ሁለት ወንድ በድምሩ አራት ተማሪዎችን በማስወጣት የጥያቄዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲፅፉ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ቀጥለውም መምህርቷ ተማሪዎች የፃፉትን መልስ በማንባብ እርማት እና ማብራሪያ ሰጡ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል ሰጡ፡፡ አንድ ሴት ተማሪም እጇን በማውጣት "**ወዛም** እና **አመዳም** የሚሉት ቃላት ሁለቱም ቅፅሎች

ናቸው፡፡ ነገር ግን ቅድም ሲያስረዱን አንዱ ለአንዱ ተቃራኒ ፍቺ ነው፡፡ ብለውን ነበር እና እንዴት ነው እነዚህ ቃላት ተቃራኒ የሚሆኑት?" በማለት ጠየቀች፡፡

መምህርቷም አንድ ተማሪ አንዱ የደረቀ አንዱ ደግሞ ለምለም ያለ ቅጠል እንዲያመጣላቸው ቀስ ብለው ነገሩት፡፡ ተማሪውም ሄደ፡፡ እስከዛም ተማሪዎች እንዲያስረዷት ለተማሪዎች ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም መልሳቸውን በመመለስ ተማሪዋን ለማስረዳት ሞከሩ፡፡ የተላከው ተማሪም ሁለት **ለምላማ** እና **ደረቅ** ቅጠሎች ይዞ መጣ፡፡ መምህርቷም ሁለቱን ዓይነት ቅጠሎች በማሳየት ለምለም ያለው ቅጠል ወዛም የደረቀው ደግሞ አመዳም መሆኑን በማስረዳት ጥያቄዋን መለሱላት፡፡ አሁንም "ሌላ ጥያቄ ካለ ሲሉ ጠየቁ፡፡" ተማሪዎችም "የለም" አሉ፡፡ መምህርቷም "ጥያቄ ከሌላችሁ የዕለቱ ትምህርት ይህን ይመስላል፡፡" በማለት የሰጡትን አሳይመንት (የቤት ስራ) ሰብስበው ከክፍል ወጡ፡፡

**አባሪ-11፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-2 ምድብ** ‹‹ E2››

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-E

ክፍለ ጊዜ- 1ኛ

ሰዓት 6፡30-7፡00

ቀን 24/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-2

የተማሪዎች ብዛት - 49

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ጥቁር ሰሌዳውን በማፅዳት ለሁለት ከፍለው በስተግራ በኩል ቀንና

አማርኛ[1]

ተማሪው[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን በመፃፍ ሰላምታ አቀረቡ፡፡ በመቀጠል "ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማማርነው ስለምን ነበር?" በማለት ተማሪዎቹን ጠየቁ፡፡ ተምሪዎችም "**ነጠላ** ቁጥር ወደ **ብዙ** ቁጥር

መቀየር እና ስምን ወደ ቅፅል መቀየር" የሚል ምላሽ ሰጡ፡፡ መምህሩም ተማሪዎች ምሳሌ እንዲሰጡ አዘዙ፡፡ ተማሪዎች አሁንም እጃቸውን በማውጣት "**ቤት** የሚለውን ቃል አማርኛ እርባታ **ቤቶች** ሲሆን ግእዝ እርባታ ደግሞ **አብያት** ይሆናል፡፡" እንዲሁም "**ሀሜት** የሚለውን ስም ወደ ቅፅል ሲቀየር **ሀሜታም** ይሆናል ወዘተ."በማለት ምሳሌዎችን ሰጡ፡፡

መምህሩ "ዛሬ የምንማማረው ለ30 ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም አስሩን ደቂቃ ትራፊኮች የመንገድ ጉዳይ ገለፃ ለመስጠት ይጠቀሙበታል፡፡ ስለዚህ ካለው ጊዜ አንፃር ፈጠን ብላችሁ ቀጥለው የቀረቡትን የክፍል ስራ ስሩ፡፡" በማለት መመሪያ ሰጡ፡፡ ከዚያም አምስት ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ተማሪዎችም የክፍል ስራውን በግላቸው መስራት ጀመሩ፡፡ መምህሩም እየዞሩ መከታተላቸውን ቀጠሉ፡፡ የተሰጣቸው ጊዜ ካላቀ በኋላም ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ አሳሰቡ፡፡ ተማሪዎችም በቃል መለሱ፡፡ መምህሩም "ስለዚህ በሚገባ ገብቷችኋል ማለት ነው፡፡" በማለት ወደ እሚቀጥለው ርእስ አለፉ፡፡

መምህሩ "ቃላት እንዴት ማዛመድ ይቻላል?" በማለት ለተማሪዎች ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም "በተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ፣በምሳሌያዊ አነጋገር ፣ በፈሊጣዊ አነጋገር እና በጥምር ቃል ማዛመድ ይቻላል፡፡" በማለት መለሱ፡፡ በመቀጠል መምህሩ "ያላችሁት ሁሉ ትክክል ነው" ብለው ተማሪዎቹን በማድነቅ "ጅምር ዓረፍተ ነገሮች (ሀረጎች)ን በሚሟላትም ማዛመድ ይቻላል፡፡" በማለት የተማሪዎችን ሀሳብ አጠናከሩ፡፡ ከዚያም አሁን የሚሰሩት ቃላት በማጣመር መሆኑን ገለፁ፡፡ ቀጥለውም "በመማሪያ መፅሀፋችሁ ገፅ 69 ከ ‹‹1-10›› ያሉትን ቃላት በየኔትወርካቹ እየተወያያችሁ አዛምዱ፡፡" በማለት አዘዙ፡፡

መምህሩ ለውይይቱ የተሰጣችሁ ደቂቃ 5 ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ በማለት ካሳሰቡ በኋላ እንዴት መሰራት እንዳለባቸው እየዞሩ ማስረዳት ጀመሩ፡፡ ደቂቃው ካለቀ በኋላም ከየኔትወርኩ አንድ ተማሪ እንዲመልስ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ለተጠየቁት ጥያቄዎች ከየኔትወርካቸው አንዳንድ ተማሪ በመነሳት ምላሽ ሰጡ፡፡ አስከትለውም መምህሩ "ወፍ ዘራሽ ምን ማለት ነው?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን

በማውጣት “ወፍ የዘራችው ማለት ነው፡፡” የሚል ምላሽ ሰጡ፡፡ መምህሩም በጣም በመሳቅ “በሉ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ጠይቃችሁ መልስ ይዛችሁ ኑ” በማለት “ስለተደወለ ለዛሬ እዚህ ይበቃል፡፡” ብለው ተሰናብተው ከክፍል ወጡ፡፡

**አባሪ-12፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-2 ምድብ ‹‹ L2 ››**

ቀረፃ ሁለት- ሐወልቲ /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-L

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰዓት 7፡50-8፡30

ቀን 26/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-2

የተማሪዎች ብዛት - 55

መምህሩ ወደ ክፍል ገብተው ሰላምታ በማቅረብ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱ፡፡ በመቀጠል ጥቁር ሰሌዳውን ለሁለት በመክፈል በስተግራ በኩል

አማርኛ[1]

ተማሪው[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውንና ቀን ፃፉ፡፡ በመቀጠል “ባለፈው ክፍለ ግዜ ስለምን ተምራችሁ ነበር?” በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም ስለ ቃለ ጉባኤ መማራቸውን ገለፁ፡፡ መምህሩ “ቃለ ጉባኤ ምንድን ነው?” የሚል ጥያቄ ለተማሪዎች አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት “ቃለ ጉባኤ ማለት የአንድ ሰብሰባ ሂደት የሚያሳይ የፅሁፍ መረጃ ነው፡፡” በማለት መለሱ፡፡ መምህሩ “ሌላ የተማራችሁት ነገር ነበር እስኪ አስታውሱ” በማለት ተማሪዎችን እንዲያስታወሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት “ስለ ጠለፋ” በማለት መለሱ፡፡ መምህሩ አሁንም “ጠለፋ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም ከየኔትወርኩ እጃቸውን በማውጣት “ጠለፋ ማለት በሴቶች ላይ የሚደረግ አላስፈላጊ ግንኙነት ነው፣ አብዛኛውን ጊዜ በገጠር አካባቢ የሚያጋጥም ሆኖ ወንዶች ሴቶችን ያለፍላጎት አምፀው ሲወስዱዋቸው ነው ወዘተ.” በማለት መለሱ፡፡

መምህሩ ተማሪዎችን በማድነቅ “የዛሬ ትምህርታችን ደግሞ ክፍል አራት ሰዋስው በሚለው ስር ከስም ቅፅሎችን መመስረት ነው፡፡” በማለት ርእሱን አስተዋወቁ፡፡ ከዚያም አራት ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከስም ወደ ቅፅል እንዴት እንደሚቀየሩ አስረዱ፡፡ ተማሪዎች መረዳታቸው ካረጋገጡ በኂላም በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 69 ከ ‹‹ሀ-መ›› ስር ያሉት ቃላት በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ በውይይቱ ወቅት መምህሩ እየዞሩ በመከታተል ለተማሪዎች እገዛ ያደረጉ ነበር፡፡ እንዲሁም መምህሩ በውይይቱ ወቅት እያንዳንዱን ጥያቄ የሚሰሩ ተማሪዎች ከየኔትወርኩ በመምረጥ ወጥተው እንደሚሰሩ አስረዱ፡፡ ለሰጡት ጥያቄ የሰጡት ደቂቃ ሲያበቃ ከያንዳንዱ ኔትወርክ የተመረጡ ተማሪዎች እየወጡ ጥቁር ሰሌዳ ላይ መልሳቸውን እንዲፅፉ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም እየወጡ መልሳቸውን ፃፉ፡፡ በመቀጠል መምህሩ “በአጠቃላይ ቀደም ብላችሁ እንደሰራችሁት ስሞች ላይ የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር ከስም ቅፅል መመስረት ይቻላል፡፡” በማለት ማጠቃለያ ሰጡ፡፡

መምህሩ ተማሪዎች ቀደም ብለው ከሰሩዋቸው ውጪ ሌላ ቅጥያ በመጨመር ቅፅሎችን መስርተው ምሳሌ እንዲሰጡዋቸው ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም የተለያዩ ምሳሌዎች ሰጡ፡፡ ቀጥለውም መምህሩ “የዕለቱን ትምህርት አጠቃልሎ የሚነግረኝ ማን ነው?” የሚል ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት “ስሞች ላይ የተለያዩ ቅጥያዎች በመጨመር አዲስ ቅፅል መመስረት እንደሚቻል ተምረናል፡፡” በማለት መለሱ፡፡ መምህሩም ተማሪዎችን በማድነቅ በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 69 ከ ‹‹1-10›› አዛምድ ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ በመስጠት ክፍለ ጊዜውን አጠናቅቀው ወጡ፡፡

**አባሪ-13 ፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-2 ምድብ** ‹‹ C2››

ቀረፃ ሁለት- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ- C

ክፍለ ጊዜ- 6ኛ

ሰዓት 10፡25-11፡15

ቀን 26/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-3

የተማሪዎች ብዛት -51

በቅድሚያ መምህሩ ወደ ክፍል በመግባት ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ለሁለት በመክፈል በስተግራ በኩል

አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውንና ቀን ፃፉ፡፡ በመቀጠል መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ሰዋስው መሆኑን በመግለፅ "የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚታዩትን ጉደለቶች በመለየት ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡" የሚለውን ትዕዛዝ አነበቡ፡፡ ከዚያም ዓረፍተ ነገሩ ያለበትን ጉድለት በማስረዳት እንዴት እንደሚስተካከልም አስረዱ፡፡ ከዛ የቀሩትን ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ጥያቄዎቹን በቃል መለሱ፡፡ ቀጥለውም "ምሳሌውን መሰረት በማድረግ **ነጠላ** ቁጥሮችን ወደ **ብዙ** ቁጥሮች ቀይሩ፡፡" የሚለውን ትዕዛዝ ስር ካሉት **ልብስ** እና **ሐረግ** የሚሉትን ቃላት ከመፅሀፋቸው በማንበብ ቃላት የተለያዩ ቅጥያቂዎችን በመጨመር **በአማርኛ** እና **በግእዝ** መርባት እንደሚችሉ አስረዱ፡፡

በመቀጠል መምህሩ በምሳሌው መሰረት በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 59 ከ ‹‹ሀ-መ›› ያሉትን በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ ተማሪዎችን አዘዙ፡፡ መምህሩም እየዞሩ መከታተል ጀመሩ፡፡ የተሰጣቸውን ጊዜ ካለቀ በኋላም "የተሰመረባቸውን ቃሎችና ሀረጎች በፍቺ የሚቀርቡ ቃሎችና ሀረጎት ተኩ፡፡" የሚለውን ትዕዛዝ ስር

ሀ. <u>ሀይማኖትን</u> በተመለከተ

ለ. <u>የጋብቻ</u> ሁኔታን በተመለከተ

የሚሉትን ሁለት ምሳሌዎች በመውሰድ የመጀመሪያውን ቃል **እምነትን** የሁለተኛው ደግሞ **ትዳርን** የሚሉት ተመሳሳይ ፍቾች መስጠት እንደሚቻል አስረዱ፡፡ በመቀጠል የቀሩትን ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም በቃል መለሱ፡፡ መምህሩ የተማሪዎችን ምላሽ ማስተካከያ በመስጠት ተማሪዎች የራሳቸውን ዓረፍተ ነገር በማዘጋጀት አስምረው የተሰመረውን ቃል ፍቺ እንዲፈልጉ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም የተለያዩ መልሶች ሰጡ፡፡

በመጨረሻም መምህሩ በአጠቃላይ የዕለቱ ትምህርት ሶስት መልመጃዎችን እንደሰሩ እና የመጀመሪያው የሰዋስው ጉድለቶችን መለየት፣ቃላት በአማርኛና በግዕዝ እርባታ ከነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ መቀየር እና የተሰመረባቸውን ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መፈለግ የሚሉትን መሆናቸውን አብራሩ፡፡ ቀጥለውም ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ጋበዙ፡፡ አንድ ተማሪ እጁን በማውጣት “መነኩሴ ማለት ፍቹ ምንድን ነው?” በማለት ጠየቀ፡፡ መምህሩም ተማሪዎች እንዲሞከሩ ዕድሉን ሰጡ፡፡ አንድ ሴት ተማሪ እጇን “በማውጣት መነኩሴ ማለት ገዳም ውስጥ የሚኖር ነው፡፡” በማለት መለሰች፡፡ ከዛ መምህሩም ተማሪዋን ጎበዝ በማለት “መነኩሴ በገዳም የሚኖር ብቻ ሳይሆን እናቶችና አባቶች ዕድሜያቸው ገፋ ሲል ከዚህ በኋላ የዓላማዊ ህይወት በቃን ብለው በቤታቸው (በገዳም) ወደ መንፈሳዊ ህይወት የሚገቡበት፣የቤተክርስትያን አገልጋይ መሆን አለብኝ ብለው የወሰኑ ሰዎች ናቸው፡፡” በማለት መለሱ፡፡ ከዚያም ክፍለ ጊዜው በማለቁ ስለተደወለ “ሌላ ጥያቄ ካላችሁ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡” በማለት ጨርሰው ወጡ፡፡

**አባሪ-14፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-3 ምድብ ‹‹ A2››**

ቀረፃ ሁለት- ዓይደር /ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-A

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰዓት 3፡20-4፡00

ቀን 22/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-3

የተማሪዎች ብዛት - 55

በቅድሚያ መምህሩ ወደ መማሪያ ክፍሉ እንደገቡ ጥቁር ሰሌዳውን በማፅዳት ለሁለት ከፈሉ፡፡ በመቀጠል ሰላምታ በማቅረብ በተከፈለው ጥቁር ሰሌዳ በስተግራ በኩል ቀንና

አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን ፃፉ። ቀጥለውም የዕለቱን ትምህርት ሰዋስው መሆኑን አስተዋወቁ። አስከትለውም "በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚታዩትን ጎድለቶች ከለያችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገሩን አስተካክላችሁ ፃፉ።" የሚለውን ትዕዛዝ ከመፅሀፋቸው በማንበብ አንድ ዓረፍተ ነገር በቃላቸው ለተማሪዎች አነበቡላቸው። ካነበቡ በኋለም በዚህ ዓረፍተ ነገር የምን ስህተት እንዳለ ተማሪዎች ለይተው እንዲናገሩ ዕድሉን ሰጡ። ተማሪዎችም የሚታየውን ስህተት በመለየት መለሱ። መምህሩም የተማሪዎችን ሀሳብ በማጠናከር እና ትክክል መሆናቸውን በመግለፅ ዓረፍተ ነገሩ ሲስተካከል ምን ዓይነት ቅርፅ እንደሚኖረው አስተካክለው አነበቡላቸው። የቀሩትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ አደረጉ። ተማሪዎችም በቃል መለሱ። መምህሩም የተማሪዎችን መልስ እርማት በመስጠት ወደ እሚቀጥለው ርእስ አለፉ።

ቀጥለውም "ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ነጠላ ቁጥሮችን ወደ ብዙ ቁጥር ቀይሩ" በሚለው ትዕዛዝ ስር ከተካተቱት **ቃል- ቃሎች- ቃላት፣ልብስ- ልብሶች- አልባሳት** የሚሉትን ቃላት ከመፅሀፋቸው በማንበብ ቃላት **በአማርኛ እና በግእዝ** መርባት እንደሚችሉ አስረዱ። ምሳሌዎቹን ተማሪዎች መረዳታቸውን ካረገገጡ በኋላም በመማሪያ መፅሀፋቸው ገፅ 45 ከ ‹‹ሀ-በ›› ያሉትን በየኔትወርካቸው እየተወያዩ የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎችም የተወሰኑትን በመፃፍ፣ የተወሰኑትን በመወያየት እና የተወሰኑትን ደግሞ እየፃፉና እየተወያዩ ተስተውሏል። መምህሩም ተማሪዎችን በመዞር መከታተል ጀመሩ። ውይይቱ ከተጠናቀቀ በኋላም መምህሩ ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ እንዲመልሱ ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን እያወጡ ቢመልሱም እንኳ እኔ፣እኔ የሚል ድምፅ ክፍሉን በጣም ረብሾታል።

መምህሩ "የተሰመረባቸውን ቃሎችና ሀረጎች በፍቺ በሚቀርቡ ሌሎች ቃሎች እና ሀረጎች ተኩ።" የሚለውን ትዕዛዝ ከመፅሀፋቸው በማንበብ ከትዕዛዙ ስር ያሉትን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች አንብበው ተመሳሳይ ፍቻቸውን በማስረዳት የቀሩትን ተማሪዎች በየኔትወርካቸው በመወያየት እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎቹ መስራት፣ መምሩም እየዞሩ መከታተል ጀመሩ። የተሰጣቸውን ደቂቃ ካለቀ በኋላም ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ እንዲመልሱ አዘዙ። ተማሪዎችም እጃቸውን እያወጡ መለሱ። ቀጥለውም መምህሩ የተማሪዎችን መልስ በማጠናከር ቀደም ብለው የሰሩዋቸውን መሰረት በማድረግ

የራሳቸው ዓረፍተ ነገሮች አዘጋጅተው በማስመር ላስመሩላቸው ቃላት ደግሞ ፍቻቸውን እንዲፈልጉ አዘዙ። ተማሪዎችም በግላቸው በመስራት መልሶቻቸውን በቃል መለሱ። መምህሩም ተማሪዎችን በማድነቅ ተማሪዎች ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ ዕድሉን ሰጡ። ተማሪዎችም ጥያቄ አለመኖራቸው ሲገልፁ መምህሩ "የዕለቱን ትምህርት እዚህ ላይ ያበቃል።" በማለት ክፍለ ጊዜውን አጠናቅቀው ወጡ።

**አባሪ-15 ፡- የቪድዮ ቀረፃ ዘገባ ከመምህር-4 ምድብ ‹‹ K2››**

ቀረፃ ሁለት- ዓይደር/ሁ/ደ/ት/ ቤት

ምድብ-K

ክፍለ ጊዜ- 3ኛ

ሰዓት 7፡50-8፡30

ቀን 24/04/2004

የመምህሩ ስም- መምህር-4

የተማሪዎች ብዛት - 48

በቅድሚያ መምህርቷ ወደ ክፍል በመግባት ጥቁር ሰሌዳውን አፅድተው ለሁለት ከፈሉ።

በግራ በኩልም ቀንና አማርኛ[1]

የህዝብ ብዛትና የአገር እድገት[2]

ክፍል አራት- ሰዋስው[3]

የሚለውን ፃፉ። በመቀጠል መምህርቷ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበው ባለፈው ክፍለ ጊዜ መናገር ተምረው እንደ ነበር በማስታወስ ተማሪዎች በመናገር ስር የተከራከሩበትን ጉዳይ ምን እንደነበር ጠየቁ። ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት

1. የወሊድ መቆጣጠሪያ ለወጣቶች ይባሰኑ መር እንዲያወጡ ያደርጋል። ይህ አባባል ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?
2. ያገቡ ካላገቡ ጋር ሲነፃፃሩ ያላገቡ በቁጥር ይበዛሉ። ይህ መሆኑ ችግር አለው ትላላችሁ? ሀሳባችሁን ግለፁ።

የሚል ነበር በማለት መለሱ፡፡ መምህርቷም "በጣም ጥሩ" ብለው ተማሪዎችን በማድነቅ ሌላስ "ምን ተምራችሁ ነበር?" በማለት ሌላ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ተማሪዎችም "**ነጠላ** ቁጥሮችን ወደ **ብዙ** ቁጥሮች መቀየር፡፡" በማለት መለሱ፡፡ መምህርቷ አሁንም "እስኪ የቃል ክፍሎች ምን ምን ናቸው ብለን ነበር? ከነዚህ የቃል ክፍሎችስ ሊረቡ የሚችሉት ምን ምን ናቸው?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸውን በማውጣት ስም፣ ቅፅል፣ ግስ፣ መስተዋደድ እና ተውሳከ ግስ መሆናቸውን ገለፁ፡፡ ከነዚህም ሊረቡ የሚችሉ ስምና ቅፅል መሆናቸው ገለፁ፡፡ አሁንም መምህርቷ "የአማርኛ ስሞችና ቅፅሎች **-ኦች** እና **-ዎች** ይወስዳሉ፡፡ ለምን አንድ ዓይነት ምዕላዶች አይወሰዱም?" በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ተማሪዎችም እጃቸው በማውጣት "ስሞች-**ኦች** የሚወሰዱት አብዛኛውን ጊዜ በሳድስ ሲጨርሱ ነው፡፡ ከዛ ውጭ የሚጨርሱ ስሞች ግን **-ዎች** ይወስዳሉ፡፡" በማለት መለሱ፡፡ መምህቷም ተማሪዎችን "በጣም ጎበዞች" ብለው በማድነቅ የተማሪዎችን ገለፃ አጠናከሩ፡፡

በመቀጠልም መምህርቷ የዕለቱ ትምህርት ሰዋስዋዊ ስህተትን መለየት መሆኑን አስተዋወቁ፡፡ ከዚያም "በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚታየውን ሰዋስዋዊ ጉድለት በመለየት ዓረፍተ ነገሩን አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡" የሚለውን ትዕዛዝ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ከዚያም ሶስት ዓረፍተ ነገሮቸ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ በሶስቱ ዓረፍተ ውስጥ ነገሮች የሚታዩትን ስህተቶች በመለየትና አስተካክለው በመፃፍ አስረዱ፡፡ የቀሩትን ደግሞ ተማሪዎች በየኔትወርካቸው እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም መወያየት ጀመሩ፡፡ ተማሪዎች ሲወያዩም መምህርቷ በየኔትወርኩ እየዞሩ ይከታተሉ ነበር፡፡ መምህርቷ ለሰጡዋቸው ጥያቄዎች የሰጡት ጊዜ ሲያበቃም ተማሪዎች የጥያቄዎችን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ እንዲመልሱ አደረጉ፡፡ ተማሪዎችም ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ መምህርቷም የተማሪዎችን ምላሽ በማጠናከር ተማሪዎች ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ እድል ሰጡ፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ጥያቄ እንደሌላቸው ገለፁ፡፡ በመጨረሻም መምህርቷ **ተማሪው** የሚለው ምንባብ በማንበብ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል ለመመለስ ተዘጋጅተው እንዲመጡ ተማሪዎችን በመንገር ተሰናብተው ወጡ፡፡

አባሪ-16፡- ለተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ**

**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

በሐወልቲ እና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

**ውድ ተማሪ**

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በሐወልቲ እና ዓይደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል የሰዋስው ይዘቶችን በመማር ማስተማር ሂደት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ከተማሪዎች መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ከመጠይቁ የሚገኘው ውጤት ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ ስላለው፤ አንተ/አንቺ በመጠይቁ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕግስትና በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ በመስጠት እንድትተባበረኝ/ እንድትተባበሪኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ውድ ጊዜህ/ሽን በመሰዋት መጠይቁን ለመሙላት ፍቃደኛ ስለሆንክ/ሽ በቅድሚያ አመሰግንሃ/ሻ/ለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም ፣ ክፍል እና ተራ ቁጥር መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ለ. መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላት፣ ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት ወይም ከጓደኛ አይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ አይፈቀድም፡፡

**አጠቃላይ መረጃ**

1. ዕድሜ---------------
2. ፆታ-----------------

**ክፍል አንድ፡-**

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ ከምርጫዎቹ አንዱ ብቻ በመምረጥ በመረጥከው/ሽው ቁጥር ትይዩ ይህን (✓) ምልክት በማስቀመጥ መልስህ/ሽን አመልክት/ቺ፡፡

**ምርጫዎቹ ፡-**

5. በጣም እስማማለሁ
4. እስማማለሁ
3. ለመወሰን ያስቸግረኛል
2. አልስማማም
1. ፈፅሞ አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የሰዋስው ጥያቄዎች በግል እንድንሰራ ይደረጋል | | | | | |
| 2. | የሰዋስው ጥያቄዎች በቡድን እንድንሰራ ይደረጋል | | | | | |
| 3. | በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በጥንድ እድሰራ ይደረጋል | | | | | |
| 4. | የሰዋስው ይዘቶች በክፍል ስራ መልክ አንድሰራ ይደረጋል | | | | | |
| 5. | የሰዋስው ትምህርት ስንማር ተማሪን እሚያሳትፉ ጥያቄዎች በቃልም ሆነ በፅሁፍ መልክ ይቀርባሉ | | | | | |
| 6. | ሰዋስውን ስንማር አብዛኛውን ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል | | | | | |
| 7. | መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ዓላማ ያስተዋውቃሉ | | | | | |
| 8. | መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ርእስ ለማስተዋወቅ የቅድመ ትምህርት ጥያቄ በማቅረብ ከዳራዊ እውቀታችን ጋር እንድናያይዝ ያደርጋሉ | | | | | |
| 9. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በክፍልና በቤት ስራ መልክ እንድንሰራ ያደርጋሉ | | | | | |
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች በቡድን<br>እየተወያየን እንድንሰራ ያደርጉናል፣እየተዛዋወሩም ከታተሉናል | | | | | |
| 11. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን የቡድን ውይይትም ሆነ የቡድን ስራ ሲሰጡ የቡድኑን መሪ፣ፀሐፊና ሌሎች አባላት ያደረጃሉ፤ ሁሉም የቡድኑ አባላት በየተራ የቡድን መሪነት ሚና እንዲደርሳቸው ያደርጋሉ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 12. | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በግልም ሆነ በቡድን ሆነን የምንሰራቸውን የተለያዩ ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች በማዘጋጀት ከቤተ መፃህፍትና ከሌሎች ምንጮች አፈላልገን እንድንሰራ ያደርጋሉ | | | | | |
| 13. | ሰዋስውን ስንማር መምህራችን ያልገባን እንድንጠይቅ ያደርጋሉ | | | | | |
| 14. | መምህራችን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ዘዴዎች በማቀላቀል ይጠቀማሉ | | | | | |
| 15. | ሰዋስውን ስንማር አንድን የሰዋስው ይዘት መምህሩ ከማስተማራቸው በፊት የምናውቀውን እንናገራለን | | | | | |
| 16. | የክፍላችን ተማሪዎች በግል፣ሆነ በቡድን እንድንሰራቸው የሚሰጡን የሰዋስው ይዘቶ ሀላፊነት በመውሰድ እሰራለን | | | | | |
| 17. | መምህራችን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ጥያቄችን በመጠየቅ ንቁ ተሳትፎ እናደርጋለን | | | | | |
| 18. | በመምህርም ሆነ በተማሪ ለተጠየቀው ጥያቄ በመለስ ንቁ ተሳትፎ እናደርጋለን | | | | | |
| 19. | የተሰጠንን ስራ ለማጠናቀቅ ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀማለን | | | | | |
| 20. | በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከናውኑ ተግባራት በጥንድ በጥንድ ሲሰጠን በአግባቡ እንሰራለን | | | | | |
| 21. | የመማሪያ ክፍላችን በቡድን የሚሰሩ የሚሰሩ የሰዋስው ጥያቄዎች ለመስራት የሚያመች ነው | | | | | |
| 22. | የመምህራንና የተማሪዎች ፍላጎት ማነስ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር ተፅእኖ ያሳድራል | | | | | |
| 23. | የቡድን ውይይቱ የሚከናወነው በጎበዝ ተማሪዎች ነው | | | | | |
| 24. | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር የጊዜ እጥረት ይታያል | | | | | |

አባሪ- 17፡- ከመምህር-ሀ- ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ክፍል አንድ

የመልስ ሰጪው አጠቃላይ መረጃ

- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም ሐወልቲ/ዓይደር
- የሰለጠኑበት ዓብይ አማርኛ እና ንኡስ እንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነት
- በማስተማር የቆዩበት ዓመት -13
- የትምህርት ደረጃ -ዲግሪ
- ፆታ- ወንድ
- ዕድሜ- 32

ክፍል ሁለት

ዝርዝር ጥያቄዎች

ጥያቄ፡- አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አለ? ምን?

መልስ፡- ኧ... አዎ! እጠቀማለሁ፡፡ የምጠቀመው የማስተማሪያ ዘዴ እንደ ርእስ ጉዳዩ የተለያየ ስለሆነ ሁሉንም የማስተማሪያ ዘዴዎች በማቀላቀል እጠቀማለሁ፡፡ ምክንያቱም "There is no best Method in teaching" የሚባል ነገር አለ፡፡ ይህ ማለት ማንኛውም የማስተማሪያ ዘዴ ለአንዱ ርእስ ጉዳይ ጥሩ ቢሆን ለሌላው ላያስኬድ ስለሚችል ይህኛው የማስተማሪያ ዘዴ ጥሩ ነው ብሎ መደምደም አለመቻልን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ እኔ አባዛኛውን ጊዜ የምጠቀመው (ተማሪ ተኮር) አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ሳይነጣጠሉ የሚማሩበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ጥያቄ፡-ሰዋስውን ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡት ምን ዓይነት ዘዴ ነው? ለምን?

መልስ፡-ሰዋስውን ሳስተምር የምጠቀመው ዘዴ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎችን ማገዝና ጥሩ እውቀት ማስጨበጥ ከተፈለገ መምህር ከተማሪ የሆነ ነገር መጠበቅ አለበት፡፡ ሁል ጊዜ መምህርን የሚጠብቁ ከሆነ ግን ተማሪዎች መምህር አምላኪ በመሆን መምህሩ የሰጠውን መምህሩ ይመልሰዋል የሚል አመለካከት ስለሚኖራቸው የመምህር ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ተማሪዎቹ እንዲሰሩ ከተደረገ ግን መምህሩ እነሱ ላይ የታየውን

ስህተት በማስተካከልና ንቁ ተሳታፊግ በማድረግ በመጨረሻ አይረሴ እውቀትና ውጤት ይዘው ይወጣሉ። ስለዚህ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ አብዛኛውን ስራ ተማሪዎች የሚሰሩበት፣ ከእኔ ጥገኛነት ነፃ የሚወጡበትና እኔ ደግሞ ተማሪዎቼን በመምራት (Guide) በማድረግ ወደ ማጠቃለያ አካባቢ የምሳተፍበት ነው። በመሆኑም የመማር ማስተማር ሂደቱ እኔ ጠቋሚ ተማሪዎቼ ተሳታፊ በመሆን የሚካሄድ ነው።

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምድዎ ምን ያህል ነው?

መልስ፡- በዚህ ላይ በጣም በጣም እሰራበታሁ። ምክንያቱም ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ጥሩ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ መጀመሪያ በሚማሩዋቸው ይዘቶች ተሳታፊ መሆን አለባቸው። ስለዚህ ሰዋስውን ሳስተምርም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት ተማሪዎቹ የጥያቄዎቹ ምላሽ ፈልገው ማግኘት አለባቸው። ለምሳሌ የሚሰጡዋቸው ጥያቄዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትና የተሳቢ አለመስማማት፣የቁጥር አለመስማማት፣ የፆታ አለመስማማት፣ የባለቤትና የግስ አለመስማማት ወዘተ. መለየት ሊሆን ይችላል። በዚህ ወቅት ችግሩን በመለየት ነቅሰው የሚያወጡት እርስ በርስ በመወያየት፣ በመከራከርና መፍትሄ በመፈለግ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ጥሩ የሰዋስው እውቀት ለማስጨበጥ በይዘቶቹ ላይ ራሳቸውን ማሳተፍ አስፈላጊ ስለሆነ ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪ ዘዴ የመጠቀም ልምዴ ከፍተኛ ነው።

ጥያቄ፡- ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር የመምህሩና የተማሪው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ? በዝርዝር ቢያስረዱኝ።

መልስ፡- የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች ጥያቄዎች ማቅረብ፣ ተማሪዎች ጥያቄዎቹን መረዳታቸውን ማረጋገጥ፣ ሁሉም ተማሪዎች እየተሳተፉ መሆናቸውን፣ የተሰጣቸውን ነገር በሚገባ እየሰሩ መሆናቸውን እና ምን ዓይነት መደምደሚያ ላይ እንደደረሱ እየዞሩ መከታተል፣ የሚሰጡትን መልስ መከታተል እና የውይይታቸውን ውጤት እንዲያንፀባርቁ ማድረግ በመጨረሻም የዕለቱ ዓላማ

ከግብ መድረሱንና አለመድረሱን ማረጋገጥ ናቸው። የተማሪዎች ሚና ደግሞ እርስ በርሳቸው በመወያየትና በመከራከር ተሳታፊ መሆን ነው።

ጥያቄ፡- የመምህሩም ሆነ የተማሪዎች ሚና ይህ ከሆነ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የራሳቸውን ሚና በአግባቡ ይወጣሉ ይላሉ? ምናልባት በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ቢገልፁልኝ።

መልስ፡- እንግዲህ በመምህራን ዙሪያ በተቻለን መጠን ሚናችንን ለመወጣት የተቻለን ያህል ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን። ምክንያቱም ድርሻችንን በአግባቡ የማንወጣ ከሆነ ተማሪዎቻችን ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። በተማሪዎች ዘንድም ለውይይትም ሆነ በግላቸው እንዲሰሩት የሚሰጣቸውን ስራ በሚገባ የሚይሰሩ ከሆነ ዝርዝሮ አሁንም ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ መምህሩ እውቀትን ለማስጨበጥና ተማሪዎች ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት ውጤታማ ለመሆን ሁለታችንም እጅና ጓንት ሆነን መጓዝ አለብን። በመሆኑም ሁለታችንም በአግባቡ እየተጋገዝን እየተማማርን እንገኛለን። ይሁን እንጂ ዘዴው ተግባራዊ ሲደረግ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸው ከመሆኑ የተነሳ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶች ሲፈፅሙ ይታያሉ። ለምሳሌ፡- የአፍ መፍቻ ቋንቋውን የዓረፍተ ነገር አወቃቀር ወደ አማርኛ በቀጥታ በማምጣት መጠቀም (ሽንት ቤት) በአማርኛ (ቤት ሽንቲ) በማለት መጠቀም፣ መደብ በሚገባ አለመለየት (የአማርኛ መምህራችን ክፍል ውስጥ አለ ከማለት ይልቅ ለሁለቱም ፆታዎች (አለሽ)፣ወዘተ የመሳሰሉት ችግሮች ይታያሉ። ይህም ከሁለተኛ ቋንቋ ተፅእኖ የመጣ ሲሆን ከዚህ ውጭ ግን መምህርና ተማሪዎች ሚናቸውን በሚገባ ሲወጡ ይታያሉ።

ጥያቄ፡- በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ሂደት አሉ የሚሉዋቸውን አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ቢገልፁልኝ?

መልስ፡-ኧ የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ አወንታዊ ገፅታዎች ብዙ ናቸው። በአጠቃላይ ግን መምህራን በዚህ ዘዴ ተጠቅመን ስናስተምር ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ። ከዚህም በተጨማሪ መምህሩ እያንዳንዱ ተማሪ ምን ላይ እንደደረሰ (ምን እንዳወቀ) ያውቅበታል፤ተማሪዎች ከጥገኛነት ነፃ ወጥተው እንዲማሩ ዕድል ይፈጥራል እና መምህሩ ደግሞ ይዞት የገባውን ዓላማ ከግብ መድረሱንና

አለመድረሱን ያረጋግጥበታል ወዘተ.ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ማንኛውም ዓይነት የማስተማሪያ ዘዴ አወንታዊ ገፅታ እንዳለው ሁሉ አሉታዊ ገፅታም አለው፡፡ ይህ ዘዴ ተግባራዊ ሲደረግ ውሱን መጠን ያላቸው ተማሪዎች ይፈልጋል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ግን የተማሪ ብዛት ራሱ አንድ ችግር ነው፡፡ ስለዚህ ዘዴው ተግባራዊ መደረግ አለበት ተብሎ መመሪያው ከወጣበት ወቅት ጀምሮ እንደመፍትሄ የወሰድነው ተማሪዎች በኔትወርክ (ቡድን) ማደራጀት ነው፡፡ ኔትወርክ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ኔትወርክ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ በቅርበት ከሚገናኙበት አንፃር እና በክፍል ውስጥ ያሉ ጎበዝ፣ መካከለኛና ደካማ ተማሪዎች በውጤታቸው የሚደራጁበት ነው፡፡ በአንድ ኔትወርክ የሚዋቀሩ ተማሪዎች ቁጥር ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሲሆን ለምሳሌ ስድስት ሲመደቡ ሁለት ጎበዝ፣ ሁለት መካከለኛ እና ሁለት ደካማ ተማሪ አንድ ላይ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተደራጁ በኋላ በክፍል ውስጥም ወንበራቸው በቁጥራቸው መሰረት ሶስት ወይም አራት ዲስክ በአንድ አቅጣጫ፤የሌላውን ቡድንም በተመሳሳይ በማደራጀት መጀመሪያ ሲገቡ የተዋቀረው ቡድን ዓመቱን ሙሉ ሳይቀያየሩ እንዲዘልቁ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎች ዓመቱን ሙሉ ሳይቀያየሩ መዝለቃቸውንና በቅርበት ከሚገናኙበት አንፃር በመመደባቸው ምክንያትም የአደረጃጀቱ ስም ኔትወርክ ተብሏል፡፡ በስራቸው ሂደት መምህሩ በቡዱን በቡድን እየዞረ ይከታተላል፡፡ ከመምህሩ ይልቅ ግን የሚሳተፍና የማይሳተፍ ተማሪ፣ የሚታዘዝና የማይታዘዝ በቅርብ የሚከታተሉት ሁለቱ ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን ብዛት በዚህ መልኩ በማስተካከል ለያንዳንዱ ተማሪ ከመቆጣጠር (ከመከታተል)ይልቅ በየኔትወርኩ እየዞርን እንከታተላለን፡፡

ሌላው ለዚህ ዘዴ ተብሎ የተዘጋጀ የመምህር መምሪያ አለመኖር ነው፡፡ ምክንያቱም ማነኛውንም ዓይነት ዘዴ ክፍል ውስጥ ለመተግበር ለዛ ዘዴ መምህሩ እያንዳንዱ ክሂሎች፣ ሰዋስውም ሆነ ስነፅሁፍ ለማስተማር የሚዘጋጁ ይዘቶች እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርገውና ከዘዴው ጋር አጣጥሞ እንዴት ማቅረብ እንዳለበት መንገድ የሚመራ የመምህር መምሪያ መኖር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ እኛ ማነኛውም ዓይነት ይዘት የምናስተምረው የመምህር መምሪያን መሰረት አድርገን ሳይሆን በራሳችን እውቀት ነው፡፡

ተማሪዎች በየኔትወርካቸው አለመቀመጥ፣ ተማሪዎቹ በየኔትወርካቸው ካልተቀመጡ ደግሞ አስተካክሎ ለማስቀመጥ የሚጠፋው ጊዜ በሳምንት ካሉት ሁለት ክፍለ ጊዜያት ምንም ሳላስተምር ጊዜው ያልቃል፡፡ ስለዚህ የጊዜ እጥረትም ሌላው ችግር ነው፡፡ እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ወንበሮች በአንድ ዴስክ ሶስት ተማሪዎች የሚቀመጡበት ነው፡፡ ይህም ዴስኩን እንደፈገለግክ በማንቀሳቀስ ተማሪዎችን መመደብ አትችልም፡፡ ስለዚህ የወንበሮቹ ክብደት በቀላሉ እንዳይቀያየሩ ስለሚያደርግ ሌላው ተጨማሪ ችግር ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም በአንድ ኔትወርክ ውስጥ የሚመደቡ ተማሪዎች አመቱን ሙሉ ባሉበት ቡድን ይዘልቃሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን እነዚህን ችግሮች በተቻለን መጠን ተቋቁመን ዘዴውን እየተገበርን እንገኛለን፡፡

ጥያቄ፡- የሚያስተምሩበት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ናቸው ይላሉ? መልስዎ አዎ (አይደሉም) ከሆነ ምክንያትዎ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡-መፅሀፍ ላይ ያሉት የሰዋስው ይዘቶች ተማሪዎችን ለማሰራት ምንም ችግር የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም የተካተቱትን የሰዋስው ይዘቶች ተማሪዎችን በማሳተፍ ማስተማር ከተፈለገ የሚያግዱ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ምቹ ናቸው፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ የሆኑ ይዘቶችን እንዴት ማስተማር እንዳለባችሁ የመምህር መምሪያ ላይ የተገለፀ ነገር አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- እንግዲህ የመምህር መመሪያው በእጃችን ስለሌለ እንዲህ ይላል ማለት ይከብዳል፡፡ ምክንያቱም ሰዋስውን ለማስተማር ይህን ዘዴ ተጠቀም፣ በዚህ መልኩ ተማሪዎችን እርዳቸው የሚል ነገር የለንም፡፡ ስለዚህ ሰዋስውን በዚህ መልኩ ብናስተምር ውጤታማ እንሆናለን የሚለውን ጉዳይ ተነጋግረን መወሰን ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን የመምህር መምሪያ የለንም፡፡ አሁን ግን ከአዲስ አበባ በሲዲ እያስመጣን እንገኛለን፡፡

ጥያቄ፡- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የወሰዱት ስልጠና አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- ኧ...ስልጠናን በተመለከተ በዩኒበርሲቲ ውስጥ ከተማርኳቸው የስነ ዘዴ ኮርሶች ያገኘሁት እውቀት ካልሆነ በስተቀር በትምህርት ቤቱ ስለ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የወሰዱኩት ስልጠና የለኝም፡፡ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን እርስ በርሳችን በመነጋገር ነው የምንወስነው፡፡

ጥያቄ፡- በአጠቃላይ አሳተፊ የማስተማሪ ዘዴን በተመለከተ የሚሰጡኝ አስተያየት ካለ?

መልስ፡-እንግዲህ ማስተማር ውጤታማ እንዲሆን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መኖር ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም መምህሩ አሳታፊ በመሆን ተማሪዎች ደግሞ እንዲሳተፉ፣ እውቀት ከውስጣቸው እንዲያፈልቁ፣ ሀሳባቸውን እንዲለዋወጡና ከመምህር ጥገኛነት ነፃ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም እኛም እየተጠቀምንበት እንገኛለን፤ ለወደፊትም ጥሩ ዜጋ ለማፍራት ከተፈለገ ይህን ዘዴ መጠቀም ተመራጭነት አለው ብዬ አምናለሁ፡፡

ጠያቂ፡- እሺ ጥያቄዎቹን ጨርሻለሁ፡፡ ስለ ሰጡኝ ማብራሪያ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

መላሽ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**አባሪ -18 ፡- ከመምህር-ለ- ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ**

**ክፍል አንድ**

**የመረጃ ሰጪው አጠቃላይ መረጃ**

የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ሐወልቲ/ዓይደር

- የሰለጠኑበት ዓብይ አማርኛ እና ንሱስ እንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነት
- በማስተማር የቆዩበት ዓመት- 34
- የትምህርት ደረጃ- ዲግሪ
- ፆታ- ሴት
- ዕድሜ- 54

**ክፍል ሁለት**

**ዝርዝር ጥያቄዎች**

ጥያቄ፡- አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አለ?ምን?

መልስ፡- እሺ. አማርኛን ሳስተምር የምከተለው ዘዴ አለ ወይ? ለሚለው ጥያቄ አዎ አለ ነው፡፡ እሱም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም የቋንቋን የማስተማር ዋና ዓላማ ተማሪዎች ራሳቸው ትግበራ ውስጥ ገብተው ከትግበራው ያገኙትን እውቀት ደግሞ ይዘውት እንዲዘልቁ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ለማሳካት ተማሪዎች የሚነገራቸውን በማዳመጥ ሳይሆን እነሱ ራሳቸው ተግባር ውስጥ ገብተው ተጠያይቀው፣ ተነጋግረው፣ ተከራክረውና ሀሳባቸውን ተለዋውጠው እውቀት ሲጨብጡ ነው፡፡ ስለዚህ መጠቀሙ አስፈላጊ ነው፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስውን ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡት ዘዴ ምን ዓይነት ዘዴ ነው? ለምን?

መልስ፡-ኧ... ጥሩ! ሰዋስውን ለማስተማር አብዛኛው ጊዜ የምጠቀመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች የሰዋስው እውቀታቸው ዝቅተኛ ስለሆነ ለማስተምረው ርእስ ጉዳይ ምንነት መጀመሪያ ተማሪዎችን ጠይቄ መልስ ከሰጡኝ በኋላ በነሱ ሀሳብ ላይ ማጠናከሪያ ገለፃ በመስጠት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የማስተምረው ስለ ቅጥያ፣ የቃል ክፍሎች፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀርና በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን ስህተት መለየት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት ስለነዚህ ጉዳዮች ምንነት ተማሪዎች የሚያውቁት ከነገሩኝ በኋላ ገለፃ በመስጠት ማጠናከሪያ እሰጣለሁ፡፡ ስለምንነቱ ከተነጋገርን በኋላ በመፅሀፍ ያሉትን መልመጀዎች በየኔትወርካቸው እንዲወያዩ አድርጋለሁ፡፡ ከወይይቱ ያገኙት ሀሳብም እንደአስፈላጊነቱ እየወጡ እንዲፅፉ ወይም እንዲናገሩ በማድረግ ስለማስተምር የምጠቀመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው ማለት ነው፡፡ እየወጡ እንዲጽፉ የሚደረግበት ምክንያትም ሰዋስው ስለሆነ የአፃፃፍ ስልታቸውን፣ የቃላት አቀነጃጀታቸውን ወዘተ. ለመፈተሽ ነው፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምድዎ ምን ያህል ነው?

መልስ፡- ቀደም ብለን እንደተነጋገርነው ሰዋስው ህግ (መመሪያ) ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ተናጋሪና ፀሀፊ እንደሆኑ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጥረት ደግሞ ለተማሪዎች መንገር ሳይሆን በንግግሩ ላይ

ተማሪዎችን ተናጋሪ ማድረግ ነው። ስለዚህ እኔም ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚሰራውን ስራ አብዛኛውን ጊዜ ለተማሪዎች በመስጠት እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ ከውይይቱ ያገኙትን ውጤት እንዲያንፀባርቁ በማድረግና በማበረታታት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ስለማስተምር ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ እጠቀምበታለሁ።

ጥያቄ፡- ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር የመምህሩና የተማሪው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ? በዝርዝር ቢያስረዱኝ።

መልስ፡- የመምህሩ ሚና ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ መስጠት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ርእሰ ጉዳይ እንዴት እየተወያዩ እንዳለ እየዞሩ መከታተል፣ የተሰጣቸውን ርእሰ ጉዳይ ከብዷቸው መሆኑንና ቀሏቸው መሆኑን እየዞሩ መጠየቅ፣ ተማሪዎች የሚወያዩት ስለ ርእሰ ጉዳዩ መሆኑን በማያውቁት መንገድ መከታተል፣ ሌላ ስራ የሚሰሩ (ወሬ የሚያወሩ ከሆነ ምክር መስጠት) መምህሩ መጫወት ያለበት ሚናዎች ናቸው። የተማሪዎቹን ሚና በተመለከተ ተማሪዎች በተሰጣቸው ርእሰ ጉዳይ መወያየት፣ መከራከር፣ ከውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው ማንፀባረቅ ፣ያልገባቸውን መጠየቅና የተጠየቁትን መመለስ ናቸው።

ጥያቄ፡- የመምህሩም ሆነ የተማሪዎች ሚና ይህ ከሆነ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የራሳቸውን ሚና በአግባቡ ይወጣሉ ይላሉ? ምናልባት በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ቢገልፁልኝ።

መልስ፡-እ... በመምህራን ዘንድ የራስ ድርሻ ያለመወጣት ችግር ብዙም አይታይም። በተማሪዎች ዘንድም አንዳንድ ጎበዝ ተማሪዎች ራሳቸውንና የኔትወርካቸውን አባላት በማሳተፍ፤ የከበዳቸውን ይዘት ደግሞ ለመምህራቸው በመጠየቅ ለመስራት ሲጣጣሩ ይታያሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች የመሰልቸት ባህሪ ያሳያሉ። በተለይ ይዘቱ የሚከብዳቸው ከሆነ ያልገባቸውን ለመምህሩ ወይም ለጓደኞቻቸው ከመጠየቅ ይልቅ መስራቱን ትተው ይተኛሉ፣ ሌላ ወሬ ያወራሉ፣ይቀላለዳሉ ወዘተ.። ስለዚህ ተማሪዎች ሀላፊነትን የመወጣት ችግር ይታይባቸዋል። ከዚህ አንፃርም ተማሪዎች ድርሻቸውን በአግባቡ

እየተወጡ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህ መንስኤው ግን ተማሪዎቹ ጠቀሜታውን የሚያውቁት አይመስለኝም፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ራሷ እንዳትደክም እኛን ታስቸግራለች የሚሉ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ አሁን አሁን ግን በሁሉም ትምህርት ቤትና በሁሉም መምህራን ሲተገበር ስለሚያዩት ጠቀሜታው እየገባቸው መጥቷል፡፡ ይህም ስለ ዘዴው በቂ እውቀት ካለመኖር የተነሳ ስለሆነ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሚመለከተው አካል መፍትሄ ቢፈልግ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

ጥያቄ፡- በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ሂደት ላይ አሉ የሚሉዋቸውን አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎችን ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- አወንታዊ ገፅታዎቹ በተለይ ቋንቋን ለመተግበር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ቋንቋን በደንብ እንዲጠቀሙበት ማለትም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲያነቡ፣ እንዲፅፉና የፃፉትን ደግሞ ሰወስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ መሆኑን አለመሆኑን የሚረጋገጥበት እነሱ ሲሳተፉ ነው፡፡ ስለዚህ እውቀት ከተግባር ጋር እንዲተሳሳር (እንዲቀናጅ) ስለሚያደርግ 99% እደግፈዋለሁ፡፡

ወደ አሉታዊ ገፅታዎቹ ስንሄድ ቀደም ብዬ እንደነገርኩሽ ተማሪዎች እየወጡ እንዲፅፉ፣ እየወጡ እንዲናገሩ፣ ጮህ ብለው እንዲያነቡ በሚደረግበት ወቅት በጥሩ ሁኔታ ይተገብሩታል፡፡ ነገር ግን  በኔትወርክ ተወያዩ፣ ተከራከሩ፣ሀሳብ ተለዋወቱ ሲባሉ  የተሰጣቸውን መወያያ (መከራከሪያ) ርእስ ትተው ስለራሳቸው ጉዳይ ያወራሉ፡፡ በዛ ወቅት እየዞርክ ስለምትከታተል ሌላ ወሬ ማወራታቸውን ስትሰማ ደግሞ በመምከር ጊዜህን ታጠፋለህ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከተሰጣቸው ርእሰ ጉዳይ ወጥተው (መማር ትተው) ሌላ ወሬ እንዲያወሩ ዕድል ይሰጣል፡፡

ሌላው ለቋንቋ ትምህርት መሳካት መተግበር ያስፈልጋል እስካልን ድረስ ለትግበራው የሚያስፈልጉ መማሪያ መሳሪያዎች ማሟላት ያስፈልጋል፡፡ ዘዴውን ለመተግበር በዚህ ዙሪያ ከሚታዩ ችግሮች አንዱ ተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ይዘው አለመምጣት ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉት

የተፈለገውን ነገር መፅሀፋቸው ላይ አንብበው እንዲሰሩ ከማድረግ ውጪ የሚሰሩትን ነገር በመናገርና በመፃፍ ጊዜ ይጠፋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ በቂ ቢሆንም እንኳ የክፍለ ጊዜ እጥረት ላይ ግን ችግር ይታያል፡፡ ለምሳሌ፡- አማርኛ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ ተሰጥቶታል፤ ይሁን እንጂ በመፅሀፉ ያሉ ይዘቶች በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ በማስተማር የሚያልቁ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ባሉት ሁለት ክፍለ ጊዜያት መተላለፍ ያለበት ጉዳይ በሚገባ እየተላለፈ ነው ማለት አልችልም፡፡ ምክንያቱም መፅሀፉ ሳይጨረስ ዓመቱ ሊያልቅ ይችላል፡፡ የጥንድ ስራም ማሰራት አንችልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ጊዜ የተመደበ ቡድን ስላለ፡፡ በአጠቃላይ ግን ይህ ዘዴ ተማሪዎች ቋንቋን ለመተግበር በቡድን፣ በግል (የክፍልና የቤት ስራ)፣ የቡድን ስራ ወዘተ. በመስጠት ተሳታፊ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ከአሉታዊ ገፅታው አወንታዊ ገፅታው ያመዝናል፡፡

ጥያቄ፡- የሚያስተምሩበት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ናቸው ይላሉ? መልስዎ አዎ (አይደለም) ከሆነ ምክንያትዎን ቢያብራሩልኝ፡፡

መልስ፡- በአጠቃላይ የተማሪ መማሪያ መፅሀፍ አዘገጃጀት በበኩሌ ደስ ይለኛል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች መቼ መፃፍ፣ ማንበብ፣ መናገር፣ ማዳመጥና የሰዋስውና የስነ ፅሁፍ ይዘቶችን መስራት እንዳለባቸው ተለያይቶ የቀረበ ነው፡፡ ስለዚህ የክፍለ ጊዜ እጥረት ካልሆነ በስተቀር በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር ምንም ችግር የለባቸውም፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ የሆኑ ይዘቶችን እንዴት ማስተማር እንዳለባችሁ የመምህር መመሪያ ላይ የተገለፀ ነገር አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- እኔ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር የመምህር መምሪያ የለንም፡፡ ከዚህም የተነሳ ኧ… የሰዋስው ይዘቶችንም ሆነ ሌሎች ክሂሎችን የምናስተምረው የራሳችንን መፅሀፍ ገዝተን በማንበብ እና የሌላ ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዴት እንደሚያስተምሩ በመጠየቅ ነው፡፡ ከዛ ከነዚህ በሙሉ ያገኘነውን እውቀት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተሰብስበን በመወያየት ብቻ ነው የምናስተምረው፡፡

ስለዚህ ራሳችንን በመወያየት መምሪያ እናወጣለን እንጂ በትምህርት ቤቱም ሆነ በክልሉ የተዘጋጀ የመምህር መምሪያ የለንም፡፡

ጥያቄ፡- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የወሰዱት ስልጠና አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- የስልጠና ጉዳይ በተመለከተ በእርግጥ ይህ ዘዴ ተግባራዊ መደረግ አለበት ከተባለበት ወቅት ጀምሮ አልፎ አልፎ በሚሰጡ ስልጠናዎች ተሳትፌ አውቃለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በሁለትና በሶስት አመት ለአንድ ሳምንት የሚሰጠኝ ስልጠና በቂ እውቀት አስጨብጦኛል ማለት አልችልም፡፡ የነበረኝን እውቀት ግን ሊያጠናክርልኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ እኔ አሁን ያለሁበትን የትምህርት ደረጃ ያገኘሁት መጀመሪያ በቲቲ አይ ተመርቄ ለብዙ አመታት ሰራሁኝ፣ በመቀጠል አዲስ አበባ መምህራን ኮሌጅ ተመርቄ በዲፕሎማ 9 ዓመት ሰራሁኝ፣ በመጨረሻ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ዲግሪየን ተመርቄ እስከ ዛሬ በዲግሪ ለ 17 ዓመታት በድምር 34 ዓመት ማስተማር ላይ እገኛለሁኝ፡፡ ስለዚህ ስለ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በተመለከተ በትምህርት ጉዞየ በተለይ ደግሞ በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በቂ እውቀት አግኝቻለሁ፡፡ ያንን እውቀትም ተግባራዊ እያደረግኩት እገኛለሁ፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በትምህርት ቤቱ ዘዴውን በተመለከተ በቂ እውቀት የምጨብጥበት ስልጠና ተሰጥቶኝ አያውቅም፡፡

ጥያቄ፡- በአጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የሚሰጡኝ አስተያየት ካለ?

መልስ፡- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እኔ እስከማውቀው ድረስ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዘዴ ተማሪዎች የሚማሩትን ነገር እየተገበሩት እንዲያልፉ፣ ተዘጋጅተው እንዲመጡ፣ ጥሩ ተናጋሪና ፀሀፊ እንዲሆኑ፣ ሀላፊነት እንዲወስዱና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይ ለሴቶች ሀፍረትን እንዲያስወግዱ ስለሚረዳ መቀጠል ያለበት አካሄድ ነው፡፡

ጠያቂ፡- ስለ ተሰጠኝ ማብራሪያ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

መላሽ፡- ምንም ማለት አይደለም፡፡

**አባሪ-19፡- ከመምህር-ሐ- ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ**

**ክፍል አንድ**

**የመረጃ ሰጪው አጠቃላይ መረጃ**

- የሚያስተምሩበት ስም፡ ሐወልቲ/ ዓይደር
- የሰለጠኑበት ዓብይ አማርኛ ንኡስ እንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነት
- በማስተማር የቆዩበት ዓመት- 4
- የትምህርት ደረጃ- BA
- ፆታ- ወንድ
- ዕድሜ- 28

**ዝርዝር ጥያቄዎች፡-**

ጥያቄ ፡- አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አለ? ምን?

መልስ፡- እንግዲህ አማርኛም ሆነ ማንኛውንም የትምህርት ዓይነት ስናስተምር የማስተማሪያ ዘዴ እንደምንጠቀም የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ እኔም እንደ መምህርነቴ መጠን እንደየ ርእሱ አስፈላጊነት የተለያዩ ዘዴዎችን እጠቀማለሁ፡፡ ከዚህ በፊት ስንጠቀመው የነበረው መምህር ተኮር (ገለፃ ) በመስጠት ነው፡፡ ተማሪ በመማር ማስተማር ሂደት ተሳታፊ መሆን አለበት የሚል መመሪያ ከወጣ በኂላ ግን ተማሪን የሚያሳትፉ ዘዴዎች እንደ ቡድን ውይይት፣ የቡድን ስራ፣ አሳይመንት፣ የጥንድ ስራና የግል ስራ የመሳሰሉትን በክፍል ውስጥ ስጠቀምባቸው እገኛለሁ፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስውን ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡት ምን ዓይነት ዘዴ ነው? ለምን?

መልስ፡-እንግዲህ ሰዋስውን ሳስተምር የምጠቀመው ዘዴ አብዛኛውን ጊዜ የተለመደውንና እስከ ቅርብ ጊዜ ሲተገበር የነበረውን ገለፃ ነበር፡፡ ይህም ለምሳሌ፡- ስለ ቃል ክፍሎች ለማስተማር ስም ማለት እንዲህ ማለት ነው ፣ቅፅል ማለት እንዲህ ማለት እያሉ በመንገር ነበር፡፡ አሁን ግን የስም፣ ግስ፣ ቅፅል ወዘተ. ምንነት የሚነገረው በመምህር ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ተማሪዎቹ እየተወያዩ እንዲገልፁት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ሰዋስውን ሳስተምር አብዛኛውን ጊዜ ተማሪ አሳታፊ በሆነ መልኩ አስተምራለሁኝ፡፡ ለምሳሌ፡- ደስ የሚሉዋቸውን

ቀለሞች እንዲዘረዝሩ፣ ወዴት መሄድ እንደሚፈልጉ እንዲገልፁ፣ የሚወዱዋቸው የምግብ ዓይነቶችን እንዲዘረዝሩ በማድረግ መጨረሻ በቃል ክፍላቸው እዲፈርጇቸው ይደረጋል። ይህም ደግሞ ሰዋስውን በቀላሉ እንዲገነዘቡት ያደርጋል።

ይህን ዘዴ የመረጥኩበት ምክንያት ለምሳሌ ከሰዋስው ስር የስም ምንነትን በተመለከተ ራሴ ገለፃ ብሰጥ ነገሩ በኔ ያልቃል። ተማሪዎች መረዳታቸውን እንኳ ማረጋገጥ አልችልም። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ተማሪዎች የስምን ምንነትን የሚያውቁት እኔ የነገርኳቸውን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ስለ ስም የሚኖራቸውን ዘላቂ እውቀት ከኔ ባገኙት ብቻ እንዲገደብ ያደርጋል። ይህ እንዳይሆን ግን ተማሪን የምያሳትፍ ዘዴ (አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ) እመርጠዋለሁኝ።

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምድዎ ምን ያህል ነው?

መልስ፡- ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ይህ ዘዴ ተግባራዊ መደረግ አለበት ከተባለበት ወቅት ጀምሮ ዘዴውን የመተግበር ልምዴ ከፍተኛ ነው ማለት እችላለሁኝ። ምክንያቱም ተማሪዎች በተቀመጡበት ኔትወርክ መሰረት እንዲሰሩ እያደረግኩኝ አገኛለሁ።

ጥያቄ፡- ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ሲተገበር የመምህሩና የተማሪው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ? በዝርዝር ቢያስረዱኝ።

መልስ፡-እ... ይህ ዘዴ ሲተገበር የመምህሩ ተግባር ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሲሰሩ እየዞሩ መከታተል፣ ሁሉም መሳተፋቸውን መቆጣጠር እና ማበረታታት ነው። የተማሪዎቹ ተግባር ደግሞ ነፃ ሆነው በመወያየትና በመከራከር የተሰጣቸውን ስራ መስራት፣ የመሰላቸውን ሀሳብ መግለፅ፣ያልገባቸውን መጠየቅ እና የተጠየቀውን መመለስ ሲሆኑ የተሳሳቱትን እርመት መስጠት ደግሞ የመምህሩ ድርሻ ይሆናል።

ጥያቄ፡- የመምህሩም ሆነ የተማሪዎች ሚና ይህ ከሆነ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የራሳቸውን ሚና በአግባቡ ይወጣሉ ይላሉ? ምናልባት በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮ ካሉ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- እንግዲህ ኧ… እኔ በማስተምራቸው ክፍሎች በተቻለኝ መጠን የየራሳችንን ሚና በአግባቡ እንድንወጣ እጥራለሁኝ፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪ ብዛት፣ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉ ዴስኮች፣ የመማሪያ ክፍሉ አቀማመጥ የመሳሰሉት ችግሮች ተማሪዎች በኔትወርካቸው ተወያይተው የውይይቱን ውጤት እንዲያንፀባርቁ ለማድረግ ትንሽ ያስቸግራሉ፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች አቀማመጥ በኔትወርክ ሆነው እንዲሰሩ ቢደረግም ሚናቸውን በሚገባ እንዲወጡ የሚደረገው ጥረት ግን ትንሽ ይቀረዋል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ አበዛኞቹ ተማሪዎች ሚናቸውን እየተወጡ ነው ቢባልም የተወሰኑ ተማሪዎች ግን ስራ ሲፈቱ ይታያሉ፡፡

ጥያቄ፡- በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ሂደት አሉ የሚሉዋቸውን አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ቢገልፁልኝ?

መልስ፡- እንግዲህ ሁሉም ማስተማሪያ ዘዴ የራሱ የሆነ አወንታዊ እና አሉታዊ ገፅታ አለው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በስራ እንዲጠመዱ ማድረጉ አወንታዊ ገፅታ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የሚማሩትን ጉዳይ ሀሳብ እንዲለዋወጡበት፣ እንዲሰሩት፣ እንዲገልፁት እና እንዲፅፉት ከተደረገ መምህሩ ያቀደውን ዓላማ ከግብ መድረሱንና አለመድረሱን ያረጋግጥበታል፡፡ ተማሪዎች ደግሞ ፈጣሪዎች እንዲሆኑ፣ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ ችግር እንዲፈቱና አራቱን ክሂሎችና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች በአግባቡ እንዲከወኑዋቸው ይረዳል፡፡

ወደ አሉታዊ ጎኑ ስንሄድ በክፍል ውስጥ ያሉት ጎበዝ፣ መካከለኛና ደካማ ተማሪዎች ሁሉም እኩል ተሳታፊዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በጎበዝ ተማሪዎች ብቻ የሚሸፈንበት አጋጣሚ ስላለ መቆጣጠሩ ይከብዳል፡፡ ስለዚህ ጎበዝ (Top Learners) የምንላቸው በአግባቡ በመሳተፍ ንቁ ተሳትፎ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ደካማ (Slow) ተማሪዎች የምንላቸው ደግሞ ላይሳተፉ ይችላሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ካለው ተማሪ ብዛት አንፃር፣ የወንበሩ

አቀማመጥ ወዘተ. መቆጣጠሩ ስለሚያስቸግር የመማር ማስተማር ሂደቱ በጎበዝ ተማሪዎች ተሳትፎ ብቻ የሚሽፈንበት አጋጣሚ ያፈጥራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመማሪያ ክፍሉ አቀማመጥ በተለይ በስተደቡብ ያሉት የመማሪያ ክፍሎች ከሰዓት በኋላ ሲሆን በመስኮት ሀይለኛ የፀሀይ ብርሃን ይገባል፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ ተማሪዎች ወደ ጥላ መሆን ይፈልጋሉ፡፡ ቦታ እንዳይቀይሩም ዴስኮቹ በቀላሉ አይንቀሳቀሱም፣ ጊዜም ይቃጠላል፡፡ ሌላ ክፍለ ጊዜ ይካካሳል እንዳይባል ደግሞ አማርኛ ያለው ክፍለ ጊዜ በሳምንት ሁለት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የግዜ እጠረት አለ ብየነው የምገምተው፡፡ ይህ ችግር በመኖሩ ግን መተግበር አልቻልንም የሚያስብል አይደለም፡፡ ሌላ የተጋነነ ችግር ግን የለም፤ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ባሉበትም እየተገበርን ነው፡፡

ጥያቄ፡- የሚያስተምሩበት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ናቸው ይላሉ? መልስዎ አዎ (አይደለም) ከሆነ ምክንያትዎን ቢያብራሩልኝ፡፡

መልስ፡- አመቺ የሆኑም ሊኖሩ ይችላሉ፣ አመቺ ያልሆኑም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አብዛኞቹ ግን ለተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያስቸግሩ ናቸው ብዬ አላስቀምጣቸውም፡፡ ስለዚህ ከተጠቀምንበት ሊያሳትፉ ይችላሉ ካልተጠቀምንበት ደግሞ ላያሳትፉ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ ግን ይዘቶቹ ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ናቸው፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ የሆኑ ይዘቶችን እንዴት ማስተማር እንዳለባችሁ የመምህር መምሪያ ላይ የተገለፀ ነገር አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡-ኧ... የመምህር መምሪያ ጭራሽ የለንም፡፡ ስለዚህ ለሰዋስው ለብቻው ሊኖረው አይችልም፡፡ ነገር ግን እኛ ራሳችን እንዴት ማስተማር እንዳለብን በመነጋገር፣ ከራሳችን ልምድ በመነሳትና የተለያዩ ምሁራን የሚሉትን በማንበብ እናስተምራለን፡፡ ሰዋስውን በዚህ መልኩ ማስተማር አለበት የሚል መምሪያ ግን የለንም፡፡

ጥያቄ፡- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በተመለከተ የወሰዱት ስልጠና አለ? ካለ ቢያብራሩልኝ፡፡

መልስ፡- በትምህርት ቤታችን ውስጥ የአማርኛ፣ እንግሊዝኛና ትግርኛ መምህራን አንድ ላይ በመሆን የተሞክሮ ልውውጥ አለ፡፡ ይህም ዘዴውን በምን መልኩ መተግበር እንዳለበት ሀሳብ ለመለዋወጥ ስብሰባ አድርገን እንወስናለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በግሌ በዩኒቨርስቲ ያገኘሁት ልምድ ካልሆነ በስተቀር በትምህርት ቤቱ ዘዴውን በተመለከተ የወሰዱኩት ስልጠና የለኝም፡፡

ጥያቄ፡-በአጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የሚሰጡኝ አስተያየት ካለ?

መልስ፡- እንግዲህ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር (መጠቀም) በእኔ እምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም እኛ የምንፈልገው ተማሪዎች ተምረው ነገ ራሳቸው በራስ መተማመን የሚናገሩ፣ የሚፅፉ፣ የሚያነቡና የሚያስረዱ እንዲሆኑ ነው፡፡ ይህም ስኬታማ የሚሆነው በክፍል ውስጥ ተሳታፊ በመሆን መሰረት ይዘው ሲወጡ ነው፡፡ ስለዚህ ነገ አገርን የሚመሩ፣ ችግር የሚፈቱ ተማሪዎች ለማፍራት የግድ በክፍል ውስጥ መለማመድ አለባቸው፡፡ በመሆኑም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በክፍል ውስጥ መጠቀሙ ተማሪዎች በቂ እውቀት እንዲያካብቱ ከማድረግ አንፃር ተወዳዳሪ እንደሌለው በራሴ እምነት እገልፀዋለሁ፡፡

ጠያቂ፡- ስለተሰጠኝ ማብሪሪያ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

መላሽ፡- ምንም ማለት አይደለም፡፡

አባሪ-20፡- ከመምህር-መ- ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ክፍል አንድ

**የመረጃ ሰጪው አጠቃላይ መረጃ**

- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም ሐወልቲ/ ዓይደር
- የሰለጠኑበት ዓብይ አማርኛ ንኡስ እንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነት
- በማስተማር የቆዩበት ዓመት- 22
- የትምህርት ደረጃ- BA
- ፆታ- ሴት
- ዕድሜ- 42

ጥያቄ፡- አማርኛን ሲያስተምሩ የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አለ? ምን

መልስ፡- አዎ አለ፡፡ ለምሳሌ ኢ. መደበኛ ገለፃ፣ የቡድን ውይይት፣ ጥያቄና መልስ ወዘተ እጠቀማለሁኝ፡፡

ጥያቄ፡- ሰወስውን ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡት ዘዴ ምን ዓይነት ዘዴ ነው? ለምን?

መልስ፡- ኸ... ቀደም ሲል የነበረ የማስተማሪያ ዘዴ መምህርን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዘዴ ተማሪዎች ካዳመጡት ውጪ ብዙ እውቀት ሊያካብቱ አይችሉም፡፡ ስለዚህ የኛ አቀማመጥ በኔትወርክነው፡፡ ይህም የኔትወርኩ አደረጃጀት ሁለት (ሶስት) ጎበዝ ተማሪዎች ሌሎችን እንዲያነሳሱ (እንደያወያዩ) ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዋስውን ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የምመርጠው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በግላቸው የክፍልና የቤት ስራ፣ በቡድን ደግሞ የቡድን ውይይት፣ የቡድን ስራ እንዲሰሩ አደርጋለሁኝ፡፡ ይህ የሚደርግበት ምክንያት ተማሪዎች በግላቸው ሲሰሩ ያላቸውን እውቀት እንዲያፈልቁ፣ በቡድን ሲሰሩ ደግሞ እርስበርሳቸው ሀሳብ በመለዋወጥና፣ በመመራመር፣ በመከራከር ብዙ በማሰብ ሰዋስወን በሚገባ እንዲረዱት ለማድረግ ነው፡፡

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ በሆኑ ይዘቶች ላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የመጠቀም ልምድዎ ምን ያህል ነው?

መልስ፡- ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁኝ፡፡ ምናልባት አልፎ አልፎ ጊዜ የሚሻማብኝ ከሆነ በቃል ጥያቄና መልስ እንዲሸፈን አደርገዋለሁኝ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን ተማሪዎች እንዲወያዩ ከማድረግ አልፎ እየወጡ እንዲሰሩ በማድረግ ነው ሰዋስውን የማስተምረው፡፡ ስለዚህ በከፍተኛ ደረጃ እጠቀማለሁኝ፡፡

ጥያቄ፡- ይህ የማስተማሪ ዘዴ ሲተገበር የመምህሩና የተማሪው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ? በዝርዝር ቢያስረዱኝ፡፡

መልስ፡- የመምህሩ ሚናን በተመለከተ መጀመሪያ የሚያስተምረውን ነገር ጠንቅቆ ማወቅና በቂ ዝግጅት ማድረግ፣ ተማሪዎችን እንዲሰሩ ሲያዝዝ ግልፅና የማያሻማ መመሪያ መስጠት፣ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ደግሞ እየዞረ መከታተልና የማይሳተፉትን መቀስቀስ አለበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁል ጊዜ የሚሳተፉትን ደጋግሞ ዕድል ከመስጠት ይልቅ ለማይሳተፉት ማሳተፍና ሀላፊነት በመውሰድ እንዲማሩ ማድረግ ከመምህሩ የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው፡፡ ተማሪዎቹ ደግሞ መምህራቸው በከፈተላቸው መንገድ በመማር ማስተማር ሂደቱ ንቁ ተሳታፊ መሆን ነው፡፡

ጥያቄ፡- የመምህሩም ሆነ የተማሪው ሚና ይህ ከሆነ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የራሳቸውን ሚና በአግባቡ ይወጣሉ ይላሉ? ምናልባት በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- በመምህራን ዙሪያ ግዴታችን እስከ ሆነ ድረስ ሚናችንን በአግባቡ ከመወጣት ወደ ኋላ አንልም ብዬ አምናለሁ፡፡ በተማሪዎች ዙሪያ ግን በመማር ማስተማር ሂደቱ ንቁ ተሳታፊ ቢሆኑም እንኳ አንዳንድ ግዜ ግን ለምሳሌ፡- በቡድን ሲወያዩ የመረበሽ ባህሪ ያሳያሉ፡፡

ጥያቄ፡- በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አሉ የሚሉዋቸው አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች ሁሉ ቢገልፁልኝ?

መልስ፡- እንግዲህ የአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አወንታዊ ገፅታ ተማሪ በራስ የመተማመን አቅምን ያጎለብታል፣ ተማሪዎች የተለያዩ መፃህፍት በመፈተሽና በማንበብ ብዙ እውቀት እንዲጨብጡ ያደርጋል። በአጠቃላይ ተማሪው ራሱን በስራው ላይ በመሳተፍ ስለሚማር በእውቀት የተገነባ ዜጋ እንዲፈራ (እንዲፈጠር) ይረዳል። አሉታዊ ገፅታዎች ደግሞ ቀደም ብዬ እንዲገለፅኩት አንዳንድ ረባሽ ተማሪዎች ውይይቱን ወደ ረብሻ ለመቀየር ስለሚረዳቸው ከፍተኛ ጫጫታ ይታያል። ይህ ደግሞ የተማሪም ሆነ የመምህር ጊዜ አለ አግባብ ያባክናል፣ ለሌሎች ክፍሎችም ይረብሻል።

ከዚህም በተጨማሪ የቡድን ውይይትም ይሁን የቡድን ስራ ሲሰጥ በተወሰኑ ተማሪዎች እንዲሰራና ሌሎች ተማሪዎች ስራውን በሰሩት ተማሪዎች አእምሮ እንዲጓዙ ያደርጋል። ሌላው የምንሰራው ነገር መምህሩ ይሰጠናል በማለት መማሪያ መፅሀፍ ይዘው አለመምጣት፣ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎች ቁጥር ትንሽ መሆን ይፈልጋል፤ በትምህርት ቤታችን ግን በአንድ ክፍል ከ50 በላይ እያስተማርን ዘዴውን መተግበር አስቸጋሪ ነው። እንዲሁም ዘዴውጊዜ ይፈልጋል ለአማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ግን በሳምንት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ከመማሪያ መፅሀፉ ይዘት ጋር ጭራሽ አይመጣጠንም። ስለዚህ የክፍለ ጊዜው ማነስ ራሱ ትልቅ ተፅእኖ አሳድሯል። ይሁን እንጂ እነዚህን ችግሮ ተቋቁመን እየተገበርን እንገኛለን።

ጥያቄ፡- የሚያስተምሩበት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ዘዴውን ለመተግበር አመቺ ናቸው?

መልስ፡- አ... ስለዚህ ጉዳይ እኛ ካለን ጊዜ አንፃር፣ ከተማሪዎች ብዛት፣ ዘዴውን ለመተግበር የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ካለመሟላት ውጪ ይዘቶቹ ዘዴውን ለመተግበር ምንም ችግር የለባቸውም። ስለዚህ አመቺ ናቸው።

ጥያቄ፡- ሰዋስዋዊ የሆኑ ይዘቶችን እንዴት ማስተማር እንዳለባችሁ የመምህር መምሪያ ላይ የተገለፀ ነገር አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- እህ አይደለም ሰዋስው ብቻ ለማስተማር የሚያገለግል የመምህር መምሪያ በአጠቃላይ አማርኛን ለማስተማር የሚያገለግል መምሪያም የለንም፡፡ የተሞክሮ ልውውጥ በማድረግ ብቻ እናስተምራለን፡፡

ጥያቄ፡- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የወሰዱት ስልጠና አለ? ካለ ቢገልፁልኝ፡፡

መልስ፡- ዘዴውን የምተገብረው ራሴ ከማውቀው ልምድ በመነሳት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ዘዴውን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት በትምህርት ቤቱ የተሰጠኝ ልዩ ስልጠና የለም፡፡


ጥያቄ፡- በአጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ የሚሰጡኝ አስተያየት ካለ?


መልስ፡- በአጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ሂደቱ ስኬታማ የሚሆነው የተማሪዎቹ ቁጥር አነስ ብሎ፣ በቂ መሳሪያዎች ተሟልተውና በቂ ክፍለ ጊዜ ሲኖር ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተማሪዎች ጥሩ የቋንቋ እውቀት አግኝተው ያልፋሉ ብዬ አምናለሁ፡፡


ጠያቂ፡- እሺ ጥያቄዎቼን ጨርሻለሁ፡፡ ስለሰጡኝ ማብራሪያ በጣም አመሰግናለሁ፡፡


መላሽ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

አባሪ-21 የመምህራንና የተማሪዎች ተሳትፎ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ


















DEC 22 2011


























# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬን ያስቀመጥኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎችና ምንጮች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም- ህልፍተ ተካ

ፊርማ-------------------------

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

ግንቦት 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ